Addis Ababa University
አዲስ፡አበባ፡ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ-ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሐግብር

# በስልጥኛ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው የስህተት ዓይነቶችና የስህተት ምንጮች ትንተና (በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)

ለአማርኛ ማስተማር "ኤም.ኤ" ድግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ

በ

በተከተል መንታ

መስከረም /2016 ዓ/ም

አዲስ አበባ

Addis Ababa University
አዲስ፡አበባ፡ዩኒቨርሲቲ

# በስልጥኛ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው የስህተት ዓይነቶችና የስህተት ምንጮች ትንተና (በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)


በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ-ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሐ-ግብር


ለአማርኛ ማስተማር "ኤም.ኤ" ድግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናታዊ ጽሁፍ


በ

በተከተል መንታ

አማካሪ፡- ዳዊት ፍሬህይወት



መስከረም/2016 ዓ/ም

አዲስ አበባ

# በስልጥኛ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው የስህተት ዓይነቶችና የስህተት ምንጮች ትንተና
(በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ጆርናሊዝምና ኮሙኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነ-ጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል
የድህረ ምረቃ መርሐ-ግብር

ለአማርኛ ማስተማር "ኤም.ኤ" ድግሪ በከፊል ማሟያነት
የቀረበ ጥናታዊ ጽህፍ

በ
በተከተል መንታ

| **የአማካሪ ስም** | **ፊርማ** | **ቀን** |
|---|---|---|
| <u>ዳዊት ፍሬህይወት (ዶ/ር)</u> | ____________________ | ______________________ |
| **የፈታኞች ስም** | | |
| ____________________ | ____________________ | ______________________ |
| ____________________ | ____________________ | ______________________ |

መስከረም/2016 ዓ/ም
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## ምስጋና

የሆነውን ሁሉ ያደረገው፤ ከአዕምሮዬ በላይ የሆነውን የእሱነቱን ትዕዛዛት በአዕምሮዬ ያኖረው ያ… ኃያል ኀይል ምስጋናዬን በሙሉ ይውሰድ። ምናልባት የተረፈ ሙጣጭ ምስጋና ካለም፡- የጥናቴን ርዕስ አቅጣጫ ከማስያዝ ጀምሮ እስከ ጥናታዊ ጽሁፌ መጨረሻው ድረስ በዕቅዳቸው ብቻም ሳይሆን የእኔንም ጣልቃ ገብ ዕቅድ በማስተናገድ ምሁራዊ አስተያየት በመስጠት ጥናቴ ይህን መልክ እንዲይዝ ከማድረግም ባሻገር የጥናታዊ ጽሁፍ ዕውቀት እንድጨብጥ ላደረጉኝ ለአማካሪዬ ለዶክተር ዳዊት ፍሬህይወት ምስጋናዬ ከታላቅ አክብሮት ጋር ይድረስልኝ። በመቀጠል ጥናቴ እንዲስተጓጎል ሊያደርጉ ለሚችሉት፡- ለቤተሰባዊ፣ ለማህበራዊና ለዕኮኖሚያዊ ጋሬጣዎች ግንባሯን በመስጠት ለጥናቱ መወለድ ከእኔ በላይ ላማጠችው ለባለቤቴ መምህርት ጸደለ አበበ እንዲሁም ጥቃቅን ነገር ግን እጅግ ሊያሳስቡኝ የሚገቡ የቤት ውስጥ ጉዳዮችን በራሷዋ በመቅረፍና ወደ እኔ እንዳይመጡ በማድረግ ከፍተኛውን ድርሻ ለተወጣችው መለኮታዊት እህቴ ገነት ኣበበ ምስጋና ይገባቸዋል። ስራዬ ይቀላጠፍ ዘንድ የማተሪያል ድጋፍ ላደረገልኝ፣ የህትመትና የጥረዛ ኃላፊነት ወስደው ለዚህ እንድበቃ እገዛ ላደረገልኝ ለውዱ ጓደኛዬ አብዱል ከሪም ጀማል እንዲሁም በትምህርት ቤታችን የስራ ባልደረቦቼ የሆኑና የተጠኚዎቼን ፈተናዎች በማረም ከፍተኛ የሆነውን ሸክሜን ላቃለሉልኝ ለመምህራን ከተማ ገበየሁ፣ ብሩ ለገሰና እንግዳወርቅ ሽጉጤ እንዲሁም ለስልጥኛው ትርጉም መ/ር በደዊ አብራር ልባዊ ምስጋናዬ ካክብሮት ጋር ይድረሳቸው። በመጨረሻም ለእኔ መኖር ምክንያት ለሆኑት ለእናቴ ፈጣሪ ረጅም ዕድሜ እንዲሰጣት እመኛለሁ። ለአባቴም ይህ ስራ መታሰቢያው ይሁንልኝ። አበቃሁ!!!

# የይዘት ማውጫ

**ይዘት** **ገጽ**

ምስጋና ........ i

የይዘት ማውጫ ........ ii

አጠቃሎ ........ vi

ምዕራፍ አንድ ........ 1

መግቢያ ........ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 1

**1.1.1 የጥናቱ አሳሳቢ ጉዳዮች ........ 2**

**1.1.2 የጥናቱ ዓላማ ........ 3**

**1.1.3 የጥናቱ ወሰን ........ 4**

ምዕራፍ ሁለት ........ 5

2.1 ተዛማጅ ጽሁፎች ንድፈ ሀሳባዊ ክለሳዎች ........ 5

**2.1.1 የጽሁፍ ክሂል ምን ........ 5**

**2.1.2. የጽሁፍ ክሂልን ማስተማር ........ 6**

**2.1.3. የጽሀፍት ክሂል ተጽዕኖዎች ........ 7**

**2.1.4. የስህተት ምንነትና ዓይነት ........ 11**

**2.1.5. የስህተት ትንተና አስፈላጊነት ........ 13**

**2.1.6. ስህተትን በተመለከተ የሚንፀባረቁ አመለካከቶች ........ 14**

**2.1.7 በስህተት ትንተና ዙሪያ የሚታዩ ችግሮች ........ 15**

**2.1.8 የስህተት ትንተና ዘዴዎች (Identflcatlon of Errors) ........ 16**

**2.1.9 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........ 17**

ምዕራፍ ሶስት ........ 20

3.1 የጥናቱ ዓይነት ........ 20

**3.1.2 ጥናቱ የተካሄደበት ቦታና ተሳታፊዎች ........ 20**

**3.1.3 የናሙና አመራረጥ ........ 21**

3.1.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ........ 22
3.1.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ ........ 24
ምዕራፍ አራት ........ 28
4.1 የጥናቱ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ ........ 28
4.1.1 በተማሪዎች ድርሰት አተገባበር ወቅት የነበረ ሂደት መረጃ ትንተና ........ 28
4.1.2 በድርሰቶች ውስጥ የተገኙ አጠቃላይ የስህተቶች ብዛት ........ 29
4.1.3 በድርሰቶች ውስጥ የተገኙ ዋና ዋና የስህተት ዓይነቶች፡- ........ 31
ሰንጠረዥ አራት:- በቋንቋ አጠቃቀም ምድብ የተፈጸሙ ነውሳን ስህተቶች መመዝገቢያ ቅጽ:- ........ 34
ሰንጠረዥ አምስት:- በቋንቋ አወቃቀር ምድብ የተፈጸሙ ነውሳን ስህተቶች መመዝገቢያ ቅጽ:- ........ 52
4.1.4 ከተማሪዎች ጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ማብራሪያና ውጤት ትንተና፡- ........ 63
4.1.5 ከመምህራን ቃለ-መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ማብራሪያና ውጤት ትንተና፡- 77
ምዕራፍ አምስት ........ 84
5.1 ማጠቃለያ፣መደምደሚያና የመፍትሄ ሃሳብ ........ 84
5.1.1 ማጠቃለያ ........ 84
5.1.2 መደምደሚያ ........ 86
5.1.3 የመፍትሄ ሀሳብ ........ 87
ዋቢ መጽሃፍት ........ 88
አባሪዎች ........ 93
አራሚ ዘለል የተማሪዎች ናሙና ድርሰቶች ........ 93
አባሪ 1፡- ኮድ A-36 ........ 93
አባሪ 2፡- ኮድ E-34 ........ 94
........ 94
አባሪ 3፡- ኮድ F-3 ........ 95
አባሪ 4፡- ኮድ A-43 ........ 96
........ 96
አባሪ 5፡- ኮድ B-48 ........ 97

አባሪ 6፡- ኮድ F-45 ........ 98
አባሪ 7፡- ኮድ C-3 ........ 99
አባሪ 8፡- ኮድ D-52 ........ 100
አባሪ 9፡- ኮድ C-47 ........ 101
አባሪ 10፡- ኮድ E-2 ........ 102
አባሪ 11፡- ኮድ F-21 ........ 103
አባሪ 12፡- ኮድ E-42 ........ 104
አባሪ 13፡- ኮድ B-35 ........ 105
አባሪ 14፡- ኮድ A-14 ........ 106
አባሪ 15፡- ለተጠኚ ተማሪዎች የቀረበ አማራጭ የድርሰት ርዕሶች ........ 107
አባሪ 16፡- ለተጠኚ ተማሪዎች የቀረበ የጽሁፍ መጠይቆች ........ 108
አባሪ 17፡- ለተማሪዎች የቀረቡ የጽሁፍ-መጠይቆችና ለመጠይቆቹ የሰጧቸው የአማራጮች ብዛት፣ ........ 111
አባሪ 18፡- ለመምህራን የቀረቡ ቃለ-መጠይቆች ........ 114
1. ተማሪዎችዎ እርስዎ ለሚያስተምሩት ትምህርት ያላቸው ተነሳሽነት ምን ይመስላል? ከክሂል ትምህርቶችስ አንጻር በየትኛው ላይ የተሻለ ተሳትፎ ያሳያሉ ብለው ያስባሉ? ........ 114
አባሪ 19፡- መምህራን ለቀረቡላቸው ቃለ-መጠይቆች የሰጧቸው ምላሾች፡- ........ 114
አባሪ 20፡- የተጠኚ ተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቆች ምላሾች ........ 119
አባሪ 22፡- የክንውን ጊዜ ቆይታ የሚገልጽ ደብዳቤ ........ 132
የሰንጠረዥ ማውጫ ........ 133
ሰንጠረዥ አንድ:- የድርሰት ትግበራ የዕቅድ አተገባበር ሂደቶች መመዝገቢያ ቅጽ ........ 133
ሰንጠረዥ ሁለት:- የድርሰት አይነቶች መረጃ መመዝገቢያ ቅጽ:- ........ 133
ሰንጠረዥ ሶስት:- ዋና ዋና የስህተት ዓይነቶችን መመዘገቢያ ቅጽ:- ........ 134
መግለጫ: - በሰንጠረዡ ውስጥ (1) የሚገልጸው (የስህተት ብዛት)፤ (2) የሚገልጸው (በመቶኛ ሲሰላ)፤ (3) የሚገልጸው (አማካይ ስህተት) እና (4) የሚገልጸው (የስህተት ድግግሞሽ) ነው:: ........ 134
ሰንጠረዥ አራት:- በቋንቋ አጠቃቀም የተፈጸሙ ነዑሳን ስህተቶች መመዝገቢያ ቅጽ :- ........ 134
ሰንጠረዥ አምስት:- በቋንቋ አወቃቀር ምድብ የተፈጸሙ ነዑሳን ስህተቶች መመዝገቢያ ቅጽ:- ........ 135
የሰንጠረዥ ማውጫ ........ 133

ሰንጠረዥ አንድ:- የድርሰት ትግበራ የዕቅድ አተገባበር ሂደቶች መመዝገቢያ ቅጽ . 133

ሰንጠረዥ ሁለት:- የድርሰት አይነቶች መረጃ መመዝገቢያ ቅጽ:- .................. 133

ሰንጠረዥ ሶስት:- ዋና ዋና የስህተት ዓይነቶችን መመዝገቢያ ቅጽ:- ................ 134

ሰንጠረዥ አራት:- በቋንቋ አጠቃቀም የተፈጸሙ ነውሳን ስህተቶች መመዝገቢያ ቅጽ :- ........................................................................................ 134

ሰንጠረዥ አምስት:- በቋንቋ አወቃቀር የተፈጸሙ ነውሳን ስህተቶች መመዝገቢያ ቅጽ:- ........................................................................................ 135

## አጠቃሎ

የጥናቱ ዋና ዓላማ አፋቸውን በስልጥኛ ቋንቋ የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ ሚፈጽሙትን የስህተት ዓይነቶችንና የስህተት ምንጮችን መፈተሽ ነው። በመሆኑም ተማሪዎቹ የሚፈጽሟቸው ዋና ዋና የስህተት ዓይነቶች የትኞቹ ናቸው? ለስህተት የሚዳርጋቸው ዋና ዋና የተጽዕኖ ምንጮችስ ምን ምን ናቸው? ችግሩን ለመቀነስ የሚቻለውስ እንዴት ነው? የሚሉትን የጥናቱን ጥያቄዎች ለመመለስ ነው። ለዚህም በ2015 ዓ/ም በስልጤ ዞን ሌራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመማር ላይ ከነበሩ ከሁለት መቶ ስምንት (208) በስልጥኛ ቋንቋ አፈ-ፈት ከሆኑ ተማሪዎች ውስጥ በአንድ መቶ አራት (104) ተማሪዎች ላይ ትኩረት በማድረግ ጥናቱ ተካሂዷል። እነዚህም ተማሪዎች እኩል እድል ሰጪ ንሞና የሆንውን የእጣ ንሞናን ዘዴ በመጠቀም የተመረጡ ናቸው። ለጥናቱ መረጃዎችን ለመሰብሰብ በዋናነት አገልግሎት ላይ የዋለው የተማሪዎች የድርሰት ፈተና ነው። በተለያዩ መንገዶች የተገኙትን መረጃዎች ዓይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ በመጠቀም ገለፃዊ በሆነ መልኩና የስህተቶች መጠን፤ በጽህፍ መጠይቅ፣ በቃለ-መጠይቅና በድርሰት ጽህፍ ፈተና የተሰበሰቡትን ውጤቶች አሀዛዊ በሆነ መልኩ መጠናዊ የምርምር ዘዴ አተናተን በመጠቀም የተተነተነ ነው። በዚህ አተናተን ዘዴም ለጥናቱ መሰረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ተሞክሯል። ከድርሰት ትንተናው በተገኘው መረጃ መሰረት አራት አብይ የስህተት አይነቶች ተለይተዋል። በነዚህም ውስጥ ከተቆጠሩት ከአጠቃላይ አራት ሽህ አምስት መቶ ሃምሳ ስምንት (4558) ስህተቶች መካከል ሶስት ሽህ ስድስት መቶ ስልሳ (3660) ወይም (80.3%) በቋንቋ አጠቃቀም ስህተቶች ምድብ፣ ስድስት መቶ ስልሳ ሁለት (662) ወይም (14.5%) በቋንቋ አወቃቀር ስህተቶች ምድብ፣ ሁለት መቶ አስራ ሶስት (213) ወይም (4.67%) በስርዓተ-ነጥቦች ስህተቶች ምድብ እና ሀያ ሶስት (23) ወይም (0.5%) መለየት ባልተቻሉ ስህተቶች ምድብ እንደተፈጸሙ ለማወቅ ተችሏል። በተጨማሪም ለተማሪዎች በቀረበው ጽሁፍ መጠየቅና ለመምህራን በቀረበው ቃለ-መጠየቅ ጭምር በተሰበሰበው መረጃ መሰረት የተለያዩውጤቶች ተገኝተዋል። ከድርሰት ጽሁፍ በተሰበሰበው መረጃ የተገኙ አብይ ውጤቶች፤ በቋንቋ አጠቃቀም ሂደት የተመዘገቡ ስህተት ስርጭቶች ናቸው።

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ጽሁፍ የድምጽ ወካይ ምልክቶችን በመጠቀም መልዕክትን ወደ ተደራሲ ለማስተላለፍ የምንገለገልበት እና ሰዎች በቦታ ተራርቀውም ይሁን በተወሰነ ጊዜ በአንድ የተወሰነ ቦታ መገኘት ባልቻሉ ጊዜ ሀሳብን የሚለዋወጡበት መሳሪያ ነው። እንዲሁም የተለዋወጡት ሀሳብ በመረጃነት እንዲያገለግል በፈለጉ ጊዜ በመረጃ ማቆያነት የሚገለገሉበት ዓይነተኛና አስተማማኝ ክሂል ነው። Richards (1974) ጽሁፍ ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች አንዱና ከሌሎች ክሂሎች አንፃር ውስብስብነት የሚታይበት ክሂል ነው:: ውስብስብና ከባድ የሚያደርገውም የክሂሉን:- የአፃፃፍ ሥርዓቱን መረዳትና መተግበር፣ ሀሳብን ማፍላቅና ማደራጀት እንዲሁም የፈለቁ ሃሳቦችን በተገቢው መልክ እንዲነበቡ አድርጎ በመፃፍ ሀሳብንና እውቀትን ማስተላለፍ ሂደቱን ውስብስብ ያደርገዋል:: ጽሁፍ እንደማዳመጥና መናገር ክሂሎች ለቋንቋ ተጋላጭ በመሆን ብቻ የሚገኝ ካለመሆኑም በላይ አፍ-ፈት ተናጋሪም ሆኑ ሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች በሚያደርጉት ተደጋጋሚ ልምምድና ትምህርት ብቻ ይዳብራል። ከዚህም የተነሳ የጽሁፍ ክሂልን የሚማሩ ተማሪዎች በርካታ ስህተቶችን መፈጸማቸው አይቀሬ ነው። ይህንን ሀሳብ ደብሬ (1990) በዚህ ክሂል ሀሳብን ለማስተላለፍ ሲታሰብ በፊደልና በስርዓተ-ነጥብ የተዋቀረ መልዕክትን ማድረስ እንጂ እንደመናገርና ማዳመጥ ክሂሎች አጋዥ ስሜታዊ፤ አካላዊ መግለጫዎችና የመሳሰሉት ነገሮችን መጠቀም አይቻልም።

በዚህም ምክንያት ጽሁፍ ለቋንቋ ከሚኖረው ተጋላጭነት ባሻገር በትምህርት የሚገኝና በልምምድ የሚዳብር በመሆኑ በአፍ-ፈትነት ማህበራዊ መነሻ አይወስነውም (እስጢፋኖስ ተረፈ 2012፤11):: ጽሁፍ ሰዎች ሀሳባቸውን ለሌሎች የሚያካፍሉበት ወይም የሚያጋሩበት መንገድ ነው። አንድ ሰው ማለት ያለበትን ነገር በጽሁፍ ይገልፃል። ሌሎች ሰዎችም የተገለጸውን ሀሳብ በመረዳት እውቀታቸውን የሚያዳብሩበት /የሚያካብቱበት/ ይሆናል። የጽሁፍ ክሂል በትምህርትነት የሚሰጠው ተማሪዎች በተገቢው መንገድ የአፃፃፍ ህግንና መመሪያን ተከትለው ሀሳባቸውን ለሌሎች በጽሁፍ መግለጽ እንዲችሉ ለማስቻል ነው። ከአጥኚው ሀሳብ መረዳት የሚቻለው ጽሁፍ ሰዎች ለመሰሎቻቸው ሀሳባቸውን ወይም መልዕክቶቻቸውን ለማስተላለፍ ወይም ከጊዜ ውጭ ለትውልድ ለማቆየት የሚገለገሉበት እንዲሁም ሌሎቹ የተላለፈላቸውን ሀሳብና መልዕክት በመረዳት ዕውቀታቸውን የሚያዳብሩበት ክሂል መሆኑን ነው:: ለዚህም አገልግሎት እንዲውል የአጻጻፍ ህግንና መመሪያ የጠበቀ እንዲሆን በትምህርትነት የሚሰጥ ክሂል ነው:: (2010፣26) እንደገለፁት

የጽሁፍ ክሂል መማር የተለያዩ የጽሁፍ ንዑሳን ክሂሎችን (ተገቢነት ያላቸውን ዓረፍተነገሮች፣ ስርዓተነጥቦችን በተገቢው ቦታ ላይ የመጠቀም፣ ተቀባይነት ያለው ሀሳብ የመምረጥ፣ የማመንጨትና አስፋፍቶ የመግለጽ፣ ተፈላጊ የሆነውን ሀሳብ ለማስተላለፍ ተገቢ የሆኑ የአፃፃፍ ስልቶችን የመምረጥ፣ የአረፍተነገርንና የአንቀጽ አወቃቀር ስርዓትን ጠብቆ የመፃፍ እንዲሁም መደበኛ የሆነ የቋንቋ አጠቃቀም) የመለየት ተግባርን ይጠይቃል።

የቋንቋ ትምህርት ምዘና መስክ ላይ የተደረጉ ጥናቶች የምዘና ሥርዓቶቻቸው በውጫዊ ዓላማ ላይ የተመሠረቱ ናቸው:: ለዚህም አገልግሎት ላይ የሚውሉት መመዘኛ መንገዶች ከ80% በላይ መደበኛ ምዘና (Standardized Test) የሆነውን ልማዳዊ የምዘና ሥርዓት ያልተላቀቁ መሆናቸው በጽሁፍ ክሂልም ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ማሳደሩን የተለያዩ ምህራን በጥናታቸው አረጋግጠዋል። (ለምሳሌ፡- ለይላ፣ 2003፤ በለጠ፣ 2006፤ Wubshet, H., and Men uta, F. (2015)፤ ኃይላይ፣ 2017):: በነዚህም ምህራን የተገኘውን ውጤት:- ኃይላይ ተስፋይ፣ ማረው ዓለሙና ሙሉጌታ ተካ (2017) "የአማራጭ ምዘናዎች የተማሪዎችን ድርሰት የመጻፍ ችሎታ የማሻሻል ሚና" በሚለው ጥናታዊ ስራቸው ላይ አረጋግጠዋል::

በአጠቃላይ ከምሁራኑ መረዳት የሚቻለው የጽሁፍ ክሂል ከሌሎች ክሂል ዓይነቶች ውስብስብነትና ክብደት ያለው መሆኑን ነው። ለዚህም ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉት ጉዳዮች ክሂሉ እንደመናገርና ማዳመጥ ክሂሎች ለቋንቋ ተጋላጭ በመሆን ብቻ የሚገኝ አለመሆኑ፤ ለክሂሉ አጋዥ ስሜታዊ፣ አካላዊ መግለጫዎችንና የመሳሰሉት ነገሮች መጠቀም አለመቻል፤ በመማር ማስተማር ሂደት የመመዘኛው መንገድ ከልማዳዊ የምዘና ስርዓት ያልተላቀቀና ለውጤት የሚያበቃ አለመሆን ጭምር ከሌሎቹ ክሂሎች የበለጠ ውስብስብና ለስህተቶች ተጋላጭ መሆኑን ነው:

### 1.1.1 የጥናቱ አሳሳቢ ጉዳዮች

የስህተት ትንተና ስለቋንቋ ባህሪ በጥልቀት ለማስተዋል ከመርዳቱም በተጨማሪ አንድ ጥናት አድራጊ ስለመማርና ማስተማር ስልት በጥልቀት እንዲረዳና የቀደመ ዕውቀቱንም እንዲያሻሽል ይረዳል (Corder 1967፥161):: Wilkins (1976:204) "ሰህተት ትንተና የማስተማሪያ መሳሪያ ለመገምገም ይረዳል።" በማለት ይገልጻሉ:: አጥኚውም የምሁራኑን ሀሳብ በመደገፍ፤ በመማር ማስተማሩ ሂደቶች ላይ እየገጠሙት ያሉትን ችግሮች ለመቀነስ ብሎም ለመቅረፍ ይፈልጋል:: በመሆኑም አጥኚውን ይህንን ጥናት ለማከናወን እንዲነሳሳ ያደረገው ዋነኛ ምክንያት በስልጤ ዞን ምዕራብ አዘርነት በርበሬ ወረዳ ሌራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ለረጅም አመታት በአማርኛ ቋንቋ መምህርነት ሲያገለግል በቆየባቸው ጊዜያት የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች በተለይ በስልጥኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ ከፍተኛ የሆነ ሰዋስዋዊ ስህተት ሲፈጽሙና በስህተቶቹም መከሰት ምክንያት ለማስተላለፍ የፈለጉትን ሀሳብ በፈለጉት ልክ ለማስተላለፍ ሲቸገሩ

ማየቱ፤ ይህ ጥናትም ትኩረት ባደረገው ክፍል ደረጃ ላይ የሚገኙ በስልጥኛ ቋንቋ አፍ-ፈት ተማሪዎችም በአማርኛ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በመማር ማስተማር ሂደት አጥኚው የተለያዩ የጽሁፍ መልመጃዎችን እንዲለማመዱ በሚያደርግበት ወቅት በተለማመዱት ጽሁፋቸው ውስጥ:- የሰዋሰው፣ የመዋቅር አደረጃጀት፣ የሀሳብ አገላለጽ ችግሮች በስፋት የሚታዩበት መሆኑን በተደጋጋሚ የታዘበ መሆኑ፤በትምህርት ቤቱም ቢሆን በዘርፉ መምህራን ይህ ጥናት ትኩረት እስካደረገበት ጊዜ ድረስ በዚህ ርዕስ ዙሪያ የተሰሩ ጥናቶች አለመኖራቸው የመማር ማስተማር ሂደቶችን የሚያደናቅፉ እንዲሁም በትምህርትነት የሚሰጠውን የጽሁፍ ክሂል ትምህርት ዓላማ ከግብ እንዳይደርስ እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ መሆናቸው አጥኚውን አሳሳቢ አድርጎታል::

በነዚህ አሳሳቢ ጉዳዮች መነሻነት ጥናቱ ትኩረት ያደረጋቸው ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ዋና ዋና የስህተት ዓይነቶች እንዲሁም ስህተቶቹን እንዲፈጽሙ ምንጭ ወይም ምክንያት የሆኑ ጉዳዮች ምን ምን እንደሆኑ በመፈተሽ ለይቶ ያወጣል: ተለይተው የወጡትንም ስህተቶችና የስህተት ዓይነቶች እንዲሁም ለስህተቶቹ መፈጠር ምክንያት የሆኑ ጉዳዮች ከተተኳሪ ተማሪዎች ከጽሁፍ ክሂል አንፃር ምን እንደሚመስሉ ትንታኔ ይሰጣል:

### 1.1.2 የጥናቱ ዓላማ

የጥናቱ ዋና ዓላማ በስልጤ ዞን ምዕራብ አዘርነት በርበሬ ወረዳ ሌራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2015 ዓ.ም በስልጥኛ ቋንቋ አፍ-ፈት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በድርሰት ጽሁፋቸው ውስጥ የሚፈጽሙትን ስህተት ዓይነቶችና የስህተቶቹን ምንጮች ተንትኖ ማቅረብ ነው:

በተጨማሪም ከዋናው ዓላማ ውስጥ የሚወጡ ሌሎች ዝርዝር ዓላማዎችም አሉት: እነሱም: -

- በስልጥኛ ቋንቋ አፍ-ፈት የሆኑ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶችን ለይቶ በማውጣት በየምድባቸው በመመደብ መተንተን: -
- በስልጥኛ ቋንቋ አፍ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ ለሚፈጽሟቸው ስህተቶች የስህተቶቹ ምንጮች ምን እንደሆኑ ማሳየት: -
- በድርሰት ውስጥ የሚገኙ ስህተቶች ዓይነትና መጠን እንዲሁም የድግግሞሹን መጠን መፈተሽ የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች ይሆናሉ:

የመፃፍ ክሂል በትምህርትነት የሚሰጠው ዋና ዓላማ ተማሪዎች በተገቢው መንገድ የአፃፃፍ ህግንና መመሪያን ተከትለው ሀሳባቸውን ለሌሎች በጽሁፍ መግለጽ እንዲችሉ ማስቻል ነው፡ ፡ ይህ ጥናታዊ ስራም ይህንኑ ዓላማ ለማሳካት ማገዝ ነው። በጥናቱ ዓላማ መሳካት ሂደትም የሚከተሉት ማኅበራዊ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡-

- ተማሪዎች በጽሁፍ ክሂል ላይ ያለባቸውን የስህተት መጠን ቀንሰው ሀሳባቸውን ለመሰሎቻቸው በጽሁፍ እንዲገልጹና ቀርፀውም እንዲያስቀምጡ ያስችላቸዋል:

- ተማሪዎች በጽህፍ ክሂል ውስጥ ባሉ ሌሎች ንዑሳን ክፍሎች እና በሌሎች ትምህርት ዘርፎች ጭምር ብቁ እንዲሆኑ ትልቅ እገዛ ያደርጋል፡
- ከጥናቱ ተተኳሪ ትምህርት ቤት ባሻገር ለሌሎች አጎራባች ትምህርት ቤቶችም መሰል ችግሮችን ለመቅረፍ እንዲችሉ ተሞክሮ በመሆን ያገለግላል፡
- በአማርኛ ቋንቋ ለሚያስተምሩ መምህራን ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶችና የስህተት ምንጮቹ ምን ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ በመለየት ለተማሪዎቻቸው እገዛ እንዲያደርጉላቸው ፍንጭ ይሰጣል፡
- በአከባቢው በርዕሱ ዙሪያ ላይ ቀደምት ስራዎች ባለመሰራታቸው ለወደፊቱ በዚሁ ርዕሰ ጉዳይ ጥናት ማካሄድ ለሚፈልጉ አጥኚዎች መነሻ ሀሳብ ወይም አቅጣጫ ጠቋሚ በመሆን ከማገልገሉም በተጨማሪ እንደሀገርም በክሂሉ ዕድገት ላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡

### 1.1.3 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በስልጤ ዞን አዘርነት በርበሬ ወረዳ ሌራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የተገደበ ነው፡ ከይዘት አንፃር በ2015 ዓመተ-ምህረት በትምህርት ቤቱ ከሚማሩ ተማሪዎች ውስጥ በስልጥኛ ቋንቋ አፍ-ፈት ዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ በሚፈጽሟቸው ስህተት ዓይነቶችና በስህተቶቹ ምንጮች ላይ ትንታኔ መስጠት ላይ ብቻ ያተኮረ ነው:: በመሆኑም ከተጠቃሹ ትምህርት ቤትም ሆነ በሌሎቹ ቋንቋ ክሂሎች ላይ ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት የለውም::

# ምዕራፍ ሁለት

## 2.1 ተዛማጅ ጽሁፎች ንድፈ ሀሳባዊ ክለሳዎች

### 2.1.1 የጽሁፍ ክሂል ምን

የጽሁፍ የንግግር ድምፆች በተወካይ ምልክቶች አማካይነት የቋንቋው ስርዓተጽሁፍ በሚፈቅደው መልኩ በወረቀት አሊያም ዝርግ በሆኑ ነገሮች ላይ በመቅረጽ ሀሳባችንን ለአንባቢያን የሚናቀርብበት መንገድ ነው: እንደ ማረው (2005) አገላለጽ: - የመፃፍ ክሂል የግልም ሆነ የመስሪያ ቤት ደብዳቤዎችን፣ ቃለ-ጉባኤና ማመልከቻዎችን፣ ዘገባዎችን፣ የግለሰብና የራስ የህይወት ታሪክን ጽፎ ለትውልድ ለማስተላለፍ የሚያገለግል ዘርፈ-ብዙ ክሂል ነው። በመሆኑም ክሂሉ ርዕስ የመምረጥና የማጥበብ፣ የቃላት አጠቃቀም፣ የአረፍተነገር አወቃቀር፣ የሀሳብ አፈላለግና አደረጃጀት፣ የአንቀጽ ግንባታ ብሎም ሙሉ ድርሰት የመፃፍ ውስብስብ ተግባራትን የሚጠይቅ ክሂል ነው:

አዲስዓለም (2012) የመፃፍ ተግባር በአዕምሮኣችን ውስጥ ያለን ሀሳብ በቃላት አማካኝነት ከማስፈር ባሻገር በአንባቢና በጸሀፊው መካከል ተራክቦ የሚመሰረትበት ተግባቦታዊ መሳሪያ ነው። በተመሳሳይ መልኩ ተመስገን ፈቀደ (2001) ጽሁፍ በስሜት የሚከናወንና በአጭር ጊዜ የማይጠናቀቅ በአንጻሩ ጊዜ የሚፈጅ፣ ከፍተኛ ጥረትን የሚጠይቅ፣ ሀሳብን መቀበል፣ መጠየቅና መመርመር በትኩረት ማሰብም የሚያሻው የአዕምሮና የአካል ስራ ነው ይላሉ:: እስጢፋኖስ (2012) ጽሁፍ የድምጽ ወካይ ምልክቶችን በመጠቀም መልዕክትን ወደ ተደራሲ ለማስተላለፍ የምንገለገልበት መሳሪያ ነው። ጽሁፍ ሰዎች በቦታ ተራርቀውም ይሁን በተወሰነ ጊዜ በአንድ የተወሰነ ቦታ መገኘት ባልቻሉ ጊዜ ሀሳብን የሚለዋወጡበት መሳሪያ ነው። እንዲሁም የተለዋወጡት ሃሳብ በመረጃነት እንዲያገለግል በፈለጉ ጊዜ በመረጃ ማቆያነት የሚገለገሉበት ዓይነተኛና አስተማማኝ ክሂል ነው በማለት ያስረዳሉ:: Nacira (2010) መጻፍ እንደማዳመጥና መናገር ያሉ ክሂሎች በአካላዊ እንቅስቃሴ የሚደገፍና በዕለት ተዕለት ተፈጥሮአዊ ተግባቦት የሚከወን ሳይሆን በተወሰነ የመማሪያ አውድ በመደበኛ ትምህርት የሚገኝ ከመሆኑ በተጨማሪ ብርቱ የዕለት ተዕለት ልምምድ የሚጠይቅ ክሂል እንደሆነ ይገልጻሉ:: አንድ ማህበረሰብ የቋንቋው ስርዓት በሚፈቅደው መልኩ ሀሳቡን ለመሰሎቹ በንግግር እንደሚገልጸው ሁሉ በጽሁፍም የቋንቋውን ስርዓተ-ጽሁፍ ጠብቆ ስርዓታዊ የንግግር ድምጾችን በሚወክሉ ምልክቶች አማካይነት ሀሳቡን ለሌሎች አንባቢያን ለመግለጽ የሚያስችለው ዘርፈ-ብዙ ተግባራትን የሚጠይቅ ክሂል ነው:: (ማረው፥2005፣ አዲስዓለም፣2012)

በአጠቃላይ ከምሁራን ስለጽሁፍ ምንነት መረዳት የሚቻለው ጽሁፍ የቋንቋ ስርዓተጽሁፍ በሚፈቅደው መሰረት ሰዎች ሀሳባቸውን ለአንባቢያን የሚያቀርቡበት፣ ከርዕስ መምረጥና

ማጥበብ፣ ከቃላት እስከ ትልቁ መዋቅር አጠቃቀምን እንዲሁም የሀሳብ አፈላለግና አደረጃጀትን የሚጠይቅ ውስብስብ ተግባራት ያሉትና ረጅም ጊዜ የሚፈጅ በትኩረት ማሰብና መመራመር የሚጠይቅ የአዕምሮና የአካል ስራ ነው:

በተለያዩ አጋጣሚዎች ተራርቀው የሚገኙ ሰዎች በመካከላቸው የሚኖረውን የሀሳብና የመልዕክት የቦታና የጊዜ ውስንነት ለመቅረፍ እንዲሁም መረጃዎችን ለትውልድ ለማቆየት የሚያገለግል እንደ ሌሎች ክሂሎች በአካላዊ እንቅስቃሴ የማይደገፍና በዕለት ተዕለት ተፈጥሮአዊ ተግባቦት የማይከወን ክሂል እንደሆነ መረዳት ይቻላለ:

### 2.1.2. የጽሁፍ ክሂልን ማስተማር

አዲስዓለም (2012) ስለ ጽሁፍ ክሂል ማስተማር የተለያዩ የቋንቋ ምሁራን አንድ ወጥና ምርጥ ዘዴው ይህ ነው ብሎ ለመበየን አስቸጋሪ መሆኑን ይጠቁማሉ:: ይህንንም Weigle (2002) ሲያብራሩ የጽሁፍ ክሂል ለማስተማር ትምህርቱ እንደሚሰጥበት አውድ የተለያዩ ግለሰባዊ፤ ማህበራዊ፤ ባህላዊ፤ እኮኖሚያዊ፤ ስነልቦናዊ፤ ፖለቲካዊ በተጨማሪም አካባቢያዊ ሁኔታዎችና ዳራዎች የየራሳቸው ተጽዕኖና ሚና ያላቸው ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ይህን ዘዴ ብቸኛ እና ተመራጭ ያደርገዋል ለማለት ያስቸግራል። ነገር ግን ጽሁፍን ለማስተማር ጥቅም ላይ ከዋሉትና በተለያዩ ምሁራን ከቀረቡት ሀሳቦች መካከል በአንጻራዊነት ሲቃኝ የቅርብ ጊዜያት ሊባሉ የሚችሉት አራት የጽሁፍ ማስተማሪያ የአቀራረብ ሂደቶች እንዳሉ Weigle ን ይጠቁማሉ። እነሱም:- ውጤት ተኮር የጽሁፍ ማስተማሪያ ዘዴ (product focused approach)፤ ሂደት ተኮር የጽሁፍ የማስተማሪያ ዘዴ (process focused approach)፤ ዘርፋዊ አቀራረብ (Genre approach) እና ሂደታዊ የዘርፍ አቀራረብ (process genre approach) የሚባሉ ናቸው። እነሱም ቢሆኑ በምንነታቸው፤ በአተገባበር ሂደታቸው እንዲሁም በጥንካሬዎቻቸው እና ባሉባቸው እጥረቶች ላይ በተለያዩ ምሁራን አስተያየቶች የተሰነዘሩባቸው መሆኑን ጭምር ያስገነዝባሉ::

በአጠቃላይ ከምሁራን ከተሰነዘሩት ሀሳቦች መረዳት የሚቻለው የጽሁፍ ክሂል ለማስተማር አንድ ወጥና ምርጥ ዘዴ 'ይህ ነው' ብሎ ለመበየን አስቸጋሪ መሆኑን፤ ለዚህም ትምህርቱ እንደሚሰጥበት አውድ የተለያየ መሆኑን ነገር ግን የቅርብ ጊዜያት የተባሉት ውጤት ተኮር፣ ሂደት ተኮር፣ ዘርፍ አቀራረብና ሂደታዊ የዘርፍ አቀራረብ የተሻሉ ቢሆኑም እንኳን ከትችት ያላመለጡና ፍጹም ያልሆኑ መሆናቸውን እንዲሁም የጽሁፍ ክሂል ለሌሎች ቋንቋ ክሂሎች መዳበር ወሳኝ ስለመሆኑ ነው:

### 2.1.3. የጽህፍት ክሂል ተጽዕኖዎች

እንደ Fareed (2016) አገላለጽ የዳበረ የቋንቋ አጠቃቀም ለጽሁፍ ክሂል መጎልበት አዎንታዊ ተጽዕኖ ያበረክታል። ዝቅተኛ የቋንቋ አጠቃቀም ችሎታ ደግሞ በተቃራኒው አሉታዊ ተጽዕኖ ይኖረዋል። የውጤታማ ሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ ጽሁፍም ተገቢነት፣ ግልጽነት፣ ግጥምጥምነት ያለው፣ በቃላት ምርጫና በተገቢ ስርዓተ-ነጥቦች አጠቃቀም የጎለበተ እንዲሁም ሳቢነት ያለው ሊሆን ይገባል። እንደ ምሁሩ አገላለጽ ለጽህፍት ክሂል አሉታዊ ተጽዕኖ ከሚያሳድሩ ጉዳዮች አንዱ በጽህፍ ውስጥ ተገቢነት፤ ግልጽነት፤ ግጥምጥምነት የጎደለ መሆን፤ የቃላት ምርጫና ተገቢ የሆኑ ስርዓተ-ነጥቦች ያለመጠቀም ለጽሁፍ ክሂል አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ መሆናቸውን ነው:

በአጠቃላይ በአንድ ጽህፍ ውስጥ ዝቅተኛ የቋንቋ አጠቃቀም ለጽሁፍ ክሂል አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል። ስህተቶች በተግባራዊ እንቅስቃሴ ላይ የሚፈጠሩ የየራሳቸውም መከሰቻና መንስኤ ያላቸው ክንዋኔዎች ናቸው። ጽሁፍም ተግባር እንደመሆኑ በዚህ ተግባር ልምምድ ላይ የሚከሰቱ ስህተቶች ይኖሩታል። የጽሁፍ ትምህርት ብዙ ልምምድን ስለሚጠይቅ በልምምድ ሂደት ከፊደላት ቅርጽ ጀምሮ እስከ ቃላት አጠቃቀም ድረስ የተለያዩ ስህተቶች ይፈጠራሉ። የጽሁፍ ስህተት ማስተላለፍ የፈለግነውን መልዕክት በፈለግነው ልክ እንዳናስተላልፍ እንቅፋት ይፈጥርብናል። "የንጥረ ድምጽና ዘረ ድምጽ እንዲሁም የሰዋስው ስህተትና የፊደል ግድፈት ሰዎች ጸሀፊው ማስተላለፍ የሚፈልገውን እንዳይረዱት እንቅፋት ይፈጥራሉ። ብዙ የፊደል ግድፈት አሊያም የንጥረ ድምጽና ዘረ ድምጽ ስህተት በተፈጠረ ቁጥር አንባቢያን ጸሀፊው ከፊደል ግድፈትና ሰዋስዋዊ ስህተት ባለፈ የአጠቃላይ ዕውቀትና የትምህርት ክህሎት ችግር እንዳለበት ይደመድማሉ" (Jagal School, J 2002)።Norrish (1993፡12-15) ስህተቶች ለትምህርት ከሚቀርቡት ነገሮች ምርጫ፣ ከትምህርቱ የአቀራረብ ቅደም ተከተል፣ በተወሰነ ቅደም ተከተል ከሚቀርበው የማስተማር ትኩረት፣ በቋንቋውትምህርት ከሚሰጡ ምሳሌዎች፣

በምሳሌዎች አማካይነት ከሚደረገው የልምምድ ውጤት ወይም ተማሪዎቹ እነዚህን የትምህርት መረጃዎች ሲጠቀሙ ከሚኖራቸው የአጠቃቀም ሂደት ሊመጡ ይችላሉ ሲሉ ገልጸዋል።

በሁለተኛ ቋንቋ በጽህፍት ክሂል ችሎታ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ ችግሮችን በሶስት ዋና ዋና ክፍሎች ከፍሎ ማየት ይቻላል፤ እነሱም:- የመማር ማስተማር ተጽዕኖ (under prepairdness ESL)፤ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ (Inter-lingual factors) እና ውስጠ-ቋንቋ ተጽዕኖ (Intra-lingual factors) ናቸው (Chokwe 2013)። የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ፤ በጽሁፍ ወቅት የመጀመሪያ ቋንቋቸው በታላሚው ቋንቋ መሃልጣልቃ ገብ እየሆነ ወይም የተሳሳተ የቋንቋ ሽግግር (Language transfer) ተጽዕኖ የማሳደር ሁኔታን

ይመለከታል። ውስጠ-ቋንቋ ተጽዕኖ ግን የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት ሳይኖር በታላሚው ቋንቋ በቂ ግንዛቤ ባለመኖሩ ምክንያት የሚከሰት መሆኑን Chokwe (2013) ያብራራሉ። የመማር ማስተማር ተጽዕኖው፤ መምህሩ የታላሚውን ቋንቋ ህግጋት ለተማሪዎች ተገቢ በሆነ መንገድ ባለማስረጽ የሚከሰት ችግር መሆኑን ገልጸዋል። Mohammed (2008) በበኩላቸው የሁለተኛ ቋንቋ ጽህፍት ክሂል ተጽዕኖዎችን በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች በመክፈል የአፍ-መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ (Inter-lingual factors) እና ውስጠ-ቋንቋ ተጽዕኖ (Intra-lingual factors) በማለት ገልጸዋቸዋል።

በአጠቃላይ በቋንቋ መማር ሂደት ተማሪዎች በጽሁፍ ልምምድ ጊዜ ለሚፈጽሟቸው ስህተቶች ምክንያት ይሆናሉ ተብለው የተገመቱ ነጥቦች በተለያዩ ምሁራን ተገልጸዋል። ከተገለጹት ምክንያቶች አብዛኞቹ ምሁራን የሚጋሩዋቸው የሚከተሉት ናቸው:

#### 2.1.3.1. የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ

ይህ የስህተት ምክንያት እንደ ዋና ይቆጠር የነበረው ከ1970ዎቹ በፊት በነበሩ በንጽጽራዊያን የቋንቋ ጥናት አራማጆች ነበር። በንጽጽራዊ ጥናት አራማጆች እምነት "ተማሪዎች ለሚፈጽሟቸው ስህተቶች ዋና ምክንያት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት ነው" የሚል ማጠቃለያ የነበረ ቢሆንም ከ1970ዎቹ አጋማሽ ወዲህ ተማሪዎች ስህተት የሚፈጽሙት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ጣልቃ ገብነት ብቻ አለመሆኑ የተረጋገጠው አፍ-ፈት ተማሪዎች ተመሳሳይ ስህተት ፈጽመው መገኘታቸውን Brown (1994) አረጋግጠዋል። እንደ Brown (1994፡263-264) አገላለጽ፤ ‹‹የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት የመጀመሪያ ደረጃ መለያ ባህሪው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ሽግግር ወይም ጣልቃ ገብነት ነው። የአፍ መፍቻ ቋንቋ ሽግግር ለሁሉም ተማሪዎች ዋነኛ የስህተት ምንጭ ነው። ተማሪዎች ከሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ጋር ከመላመዳቸው በፊት የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሰዋስዋዊ ባህሪ በአዕምሯቸው ተቀርጾ ይገኛል። የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪው ጽሁፍ ላይ በድምጽ፣ በቃላት፣ በሀረግ እና በዓረፍተ-ነገር አወቃቀር ውስጥ ሊታይ የሚችል ቢሆንም ስህተቱ በይበልጥ ጎልቶ የሚታየው ግን በንበት (pronunciation) ላይ ነው›› በማለት ሁሉም ስህተቶች በአፍ-መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ ብቻ የማይከሰቱ መሆናቸውን አረጋግጠዋል። እንደ አጥኚው አገላለጽ በአሁኑ ወቅት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ብቸኛ የስህተት ምንጭ አለመሆኑን ይልቁኑም ከሌሎች የስህተት ምንጮች አኳያ ሲታይ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት የሚፈጠሩ ስህተቶች እጅግ በጣም ዝቅተኛ እንደሆኑ ነው:: በመሆኑም የአፍ መፍቻ ቋንቋ በሁለተኛ ቋንቋ መማር ሂደት ውስጥ አንዱ የስህትት ምንጭ መሆኑንና በተጨማሪ ሌሎች የስህተት ምንጮች መኖራቸውን መረዳት ይቻላል።

### 2.1.3.2. ውስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ

እንደ ስህተት ትንተና አራማጆች እምነት ሌላው የስህተት ምንጭ ነው ተብሎ የተጠቀሰው አሉታዊ ውስጠ-ቋንቋ ሽግግር /negative counterpart of intra-lingual transfer/ የሚባለው ነው። ይህም ተማሪው የቋንቋውን አዲስ ሥርዓት ከተማረ በኋላ ወደ አጠቃቀም ሲሄድ ውስብስብ በሆነ ውስጣዊ የቋንቋው ባህሪ የተነሳ የሚፈጠረው ስህተት ነው። Brown (1994፡214) እና Littlewood (1986፡23) ሲገልጹ፤ በውስጠ-ቋንቋ ተጽእኖ የሚፈጠሩ ስህተቶች የምንላቸው የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በሚማሩት ቋንቋ ውስጥ ባሉ የተለያዩ ባህሪያት የተነሳ የሚፈጠሩ ስህተቶችን ነው። እነዚህ ስህተቶች ምንጫቸው አፍ መፍቻ ቋንቋ አይደለም፤ ታላሚው ቋንቋ እንጂ። ተማሪዎቹ ለታላሚው ቋንቋ በከፊል ከመጋለጣቸው የተነሳ ለስህተት ሊጋለጡ ይችላሉ። ተማሪዎቹ የአንድን ቋንቋ ህግ በሚገባ ከተረዱ በኋላ ወደ አጠቃቀም ሲመጡ የተሳሳተ ማጠቃለያ በመስጠት ሊሳሳቱ ይችላሉ። የተሳሳተ ማጠቃለያ ሲባል ተማሪዎች ታላሚውን ቋንቋ እየለመዱ ሲመጡ የተማሩትን አዲስ ሥርዓት መሰረት አድርገው በቋንቋው ለመጠቀም ሲሞክሩ ቋንቋው የሚጠቀምበት መዋቅር ለሁሉም ሊጠቀሙበት ሲሞክሩ የሚፈጠረውን ስህተት ያሳያል። Brown (1994:214) አገላለጽ የቋንቋ ተማሪዎችን ለውስጠ-ቋንቋ ስህተቶች የሚያጋልጣቸው የተሳሳተ ማጠቃለያ ብቻ አይደለም፤ ያልተሟላ ትምህርት፣ የተሳሳተ ተዛምዶ እና ቃላትን አላግባብ መጠቀም በውስጠ-ቋንቋ ተጽዕኖ ለሚፈጠሩ ስህተቶች ምክንያቶች ናቸው። ሌላው ባልተሟለ ትምህርት የሚፈጠሩ ስህተቶች ናቸው:: ይህ ማለት የቋንቋ ተማሪው የቋንቋውን መዋቅር፣ ቃላት፣ የአገላለጽ ስልት ወይም ሌሎች የቋንቋውን ባህሪያት በከፊል በመማሩ የተነሳ በቋንቋ የሚገኙትን ፈሊጣዊ አነጋገሮች እና ምሳሌያዊ አነጋገሮች እንዲሁም ሰዋስዋዊ ሥርዓቶች በከፊል በትክክል፣ በከፊል ደግሞ በስህተት ሲያፈልቅ ይስተዋላል። ለምሳሌ:- ያልተሟላ ሰዋስዋዊ ህግ (ባለቤትና ግስ አለመጣጣም)፣ ያልተሟላ የመስተዋድዳዊ ሀረጎች ትምህርት እና ያልተሟላ የስነ-አገባብ ትምህርት ብሎ መክፈል ይቻላል። ይህ ስህተት በቋንቋው ውስብስብ ባህሪና የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ህግ በከፊል በመረዳት የሚፈጠሩ ስህተቶች ናችው ሲሉ ልዑል ሰገድ (1997) ይገልጻሉ::

### 2.1.3.3. የማስተማሪያ መሳሪያዎችና የማስተማሪያ ዘዴዎች ድክመት ተጽዕኖ

Norrish (1992:32) በስህተት ትንተና ዙሪያ ባደረጉት ጥናታቸው አንድን ቋንቋ ለማስተማር የሚዘጋጁ የማስተማሪያ መሳሪያዎች (መጽሀፍ፣ መርሃ ትምህርት፣ መርጃ መሳሪያዎች…) እና መምህራን የሚከተሏቸው የማስተማሪያ ዘዴዎች የስህተት ምንጭ ሊሆኑ እንደሚችሉ ያስረዳሉ። ከዚህ ጎን ለጎንም መምህሩ የሚከተለው የማስተማሪያ ዘዴ እና በክፍል ውስጥ የሚያቀርባቸው መልመጃዎች የስህተት ምንጮች ሊሆኑ ይችላሉ።

Norrish (1993፣2-16) በቋንቋ ማስተማር ሂደት ውስጥ የመምህሩ የማስተማር ችሎታ ሊለካባቸው ከሚችልባቸው መስፈርቶች መካከል የቋንቋ ትምህርትን ሳቢና ማራኪ አድርጎ ማቅረብ እና የሚጠቀምባቸውን የማስተማሪያ ዘዴዎች ውጤታማ ማድረግ የሚሉት ተጠቃሾች ናቸው። የመምህሩ የትምህርት አቀራረብ ውጤታማ ካልሆነ ተማሪዎች ለስህተት የመጋለጥ እድላቸው የሰፋእንደሚሆን ያስረዳሉ። እንዲሁም የቋንቋ መርሀ-ትምህርት የይዘት አደረጃጀት እና አቀራረብ የቋንቋን ይዘቶች ሙሉ በሙሉ ማካተት ወይም አለማካተት አንድ ቋንቋ የሚማር ተማሪ ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ ቀላል አይደለም።

በአጠቃላይ የማስተማሪያ መሳሪያዎች በአግባቡ አለመደራጀትና ደረጃ መጣኝና ሳቢ ይዘቶችን ያልያዘ መሆን በክፍል ውስጥ የሚለማመዷቸው መልመጃዎች አቀራረብ ስልቶች ትኩረት ያልተሰጠባቸው መሆን፣ መምህራንም የቋንቋ ትምህርቱን አውዱን ጠብቀው ሳቢና ማራኪ አድርገው አለማቅረብ በተማሪዎች ድርሰት ጽሁፍ ላይ ለሚፈጠረው ስህተት ምንጮች ሊሆኑ እንደሚችሉ ምሁሩ በስህተት ትንተና ዙሪያ ካደረጉት ጥናት መረዳት ይቻላል:

### 2.1.3.4. የስነ ልቦናዊ ሁኔታዎች ተጽዕኖ

ተማሪዎች በጽሁፍ ላይ ስህተት እንዲፈጽሙ ከሚያደርጋቸው ነገር አንዱ ማህበራዊና ስነ ልቦናዊ ሁኔታ ነው። በቋንቋ መማር ሂደት ላይ ተማሪው ለሚማረው ቋንቋ ያለው በጎ አመለካከት ትምህርቱን በሚገባ እንዲከታተል የመርዳቱን ያህል፣ በቋንቋውና በቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ ላይ ያለው አመለካከት አሉታዊ መሆን ደግሞ ለመማር ያለው ፍላጎት ዝቅተኛ እንዲሆን ያደርገዋል። ተማሪዎች ለሚማሩት ቋንቋ የሚኖራቸው ማህበራዊና ስነ-ልቦናዊ ሁኔታ ከቤተሰባቸው፣ ከአካባቢያቸው ከጓደኞቻቸውና ከተለያዩ ተላውጦዎች ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነት ያለው ነው።

በዚህም ምክንያት ተማሪዎች ለሚጽፉት ጽሁፍ ያላቸው ትኩረት ይቀንሳል፤ ስህተቱም በአንጻሩ ይጨምራል (Norrish 1992:18)። ስነልቦናዊ ጉዳይ ሲባል የሚያያዘው ከተማሪዎቹ የግል ጉዳዮች ጋር ሲሆን፤ ተማሪዎቹ ከክፍል ውጭ ስላለው ሁኔታ በአዕምሯቸው ውስጥ ይዘውት የሚመጡት ነገር በክፍል ውስጥ የሚሰጠውን ትምህርት በደንብ እንዳይከታተሉ ስለሚያደርጋቸው ነው (Norrish 1992፣19)። Dubin and Olshtain (1986፣15) እንደጻፉት ለትምህርት በቀረበው ቋንቋ ላይ አሉታዊ አተያይን ከሚፈጥሩ ምክንያቶች አንዱ ከቋንቋው የሚገኘው ጥቅም ነው። በመሆኑም ተማሪው ከቋንቋ ትምህርቱ ጥቅም አገኝበታለሁ ብሎ ካሰበ ለቋንቋው አዎንታዊ አመለካከት በማዳበር ቋንቋውን ለመማር ያለው ፍላጎት ይጨምራል፤ በዚህም የተነሳ በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት ውስጥ የሚፈጽማቸው ስህተቶች ይቀንሳሉ። በአንጻሩ ተማሪው ቋንቋውን ከተማረ በኋላ ምንም ዓይነት ተጨባጭ

የሆነ ጥቅም እንደማያገኝ ከተገነዘበ ለቋንቋው ያለው አመለካከት ዝቅተኛ ሊሆን ይችላል፤ በጽሁፍ ውስጥ የሚፈጽማቸው ስህተቶችም ሊጨምሩ ይችላሉ።

በአጠቃላይ ተማሪው ለሚማረው ቋንቋ አሉታዊ አተያይ ካለው ወጥነት እና ተከታታይነት ያለው የቋንቋ አጠቃቀም ከሌለው፤ ከቋንቋው ማህበረሰብ ባህል እና ልምድ ጋር የራሱ ባህል እና ልምድ የሚጋጭ ከሆነ፤ ለመማር ውስጣዊ ተነሳሽነት ከሌለው በጽሁፉ እና በንግግሩ ውስጥ ስህተቶች እየጨመሩ መሄዳቸውን መረዳት ይቻላል።

ይህ ጥናትም በነዚህ በስህተት ምንጭነት በተተለሙ መላምቶች ላይ ትኩረት በማድረግ የተማሪዎቹን የድርሰት ላይ ስህተት ዓይነቶችና ምንጮቻቸውን ለይቶ መተንተን ላይ ያተኩራል:

### 2.1.4. የስህተት ምንነትና ዓይነት

የስህተት ምንነትና ዓይነት በተመለከተ በተለያዩ ምሁራን በተለያዩ ጊዜያት የተሰጡ ብያኔዎችና ሀሳቦች ከዚህ በታች ይቀርባሉ: ይህ ጥናትም ከተነሳበት ዓላማ ጋር ሊዛመዱ በሚችሉት ሀሳቦችና ብያኔዎች ላይ ትኩረት ያደርጋል:

#### 2.1.4.1 የስህተት ምንነት

ስህተት በተለይ በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የሚከሰት እንዲሁም ስህተት ስህተትነቱ በተማሪው በራሱ የማይታይና የማይስተካከል መሆኑን እንረዳለን። ይህን ሀሳብ Brown (1994:257-258) ሲያብራሩ "ስህተት የሚከሰተው በአብዛኛው በልጅነት የአፍ መፍቻ ቋንቋ መልመጃ ጊዜያቸው የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ለምደውና የቋንቋ ልምምድ ጊዜያቸው ካለፈ በኋላ ሁለተኛ ቋንቋን በሚለምዱ ተማሪዎች ላይ ነው።" Norish (1992) ስህተት የሚባለው ከዘወትራዊ የቋንቋ አጠቃቀም በማፈንገጥ የሚቀርብ የቋንቋ ቅርጽ ነው። እንዲሁም James (1998:77) "ስህተት ስልታዊ የሆነና ሁለተኛ ቋንቋን በሚማሩ ተማሪዎች ላይ የታላሚውን ቋንቋ ስርዓት በአግባቡ ካለመረዳት የሚከሰት እንዲሁም በተማሪው ከተከሰተ በኋላ ራሱ ተማሪው ጽህፍን አንብቦ ስህተቱን በመረዳት ማረም የሚችለው አይደለም።" ይላሉ።

በአጠቃላይ ስህተት ማለት በአብዛኛው በትምህርት ሂደት በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የሚከሰት እና ስህተት

መሆኑ በራሱ በተማሪው /በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ/ የማይለይ እና የማይታረም ክስተት ነው።

#### 2.1.4.2 የስህተት ዓይነቶች

የጽሁፍ ስህተት ዓይነቶች ከሚከሰቱባቸው ሂደቶች አንጻር ስንመለከታቸው:- በውስጠ ቋንቋ ችግር የሚከሰቱ የስህተት ዓይነቶች እና በቋንቋዎች መካከል በሚታይ ጣልቃ ገብነት የሚከሰቱ የስህተት ዓይነቶች ብለን በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ልንከፍላቸው እንችላለን። መሰረት (2003) የስህተት ዓይነቶች በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ሊመደቡ ይችላሉ::

የመጀመሪያው የአጠቃቀም ወይም የአፈጻጸም ስህተት ሲሆን ሁለተኛው የዕውቀት ማነስ ስህተት ናቸው። የአጠቃቀም ወይም የአፈጻፀም ስህተት የሚባለው የቃላት ወይም የሆሄያት ግድፈት፣ ድግግሞሽ፣ የሆሄያት ጭመራ እና የመሳሰሉት ሲሆኑ ስህተቶቹ የሚፈጸሙት ግን ቋንቋውን ካለማወቅ ሳይሆን በችኮላ እና ትኩረት በማጣት ምክንያት የሚፈጠሩ ናቸው:: የእውቀት ማነስ ስህተት የሚባሉት ስህተቶች በተማሪው በተደጋጋሚ የሚፈጸሙና ተማሪው ዕገዛ ካላገኘ በቀር በራሱ ብቻ ሊያስተካክላቸው የማይችላቸው የስህተት ዓይነቶች ናቸው በማለት ያስረዳሉ። Brown (1980:160) ደግሞ የተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋ ጽሁፍ ጊዜ የሚከሰት ስህተት እንደ ተማሪዎች የሁለተኛ ቋንቋ አጻጻፍ ሥርዓት ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ጋር ተመሳሳይ ነው ብለው ስለሚያስቡ ነው። /በቋንቋዎች መካከል ያለ ስህተት/ እና በታላሚው ቋንቋ የተሳሰተ የቅርጾች አተረጓጎም (የውስጠ-ቋንቋ ስህተት) የሚከሰት ነው::
እንደቋንቋ ተለምዱዊ አጠቃቀም አንጻር ከተለምዱዊ ቋንቋ አጠቃቀም ወጣ ያለ ወይም ያፈነገጠ እንደሆነ የቋንቋ ስህተት (Error)፣ የቋንቋ ግድፈት (Mistake) እና የቋንቋ ማዳጥ (Lapse) ሊፈጠር የሚችል እንደሆነ ምሁራን ያስረዳሉ: ይህንንም ከተለምዱዊ ቋንቋ አጠቃቀም በማፈንገጥ የሚፈጠሩትን እክሎች ምንነት እንደሚከተለው ያስረዳሉ:
የቋንቋ ስህተት (Error): - ለስህተት መፈጠር ከበስተ ጀርባው ስርዓታዊ ምክንያት ያለውና የአንዱ ስህተት ሌላውን ሊያሳስት የሚችል የቋንቋ እክል ነው: ይህ ማለት በቋንቋ ተማሪዎች የሚታዩ ስህተቶች ከተማሪዎቹ የቋንቋው ችሎታ ማነስ ምክንያት የሚፈጠሩ ሳይሆን በቋንቋው ስርዓታዊ ቅርጽ መነሻነት የሚፈጠሩ ናቸው ማለት ነው:
የቋንቋ ግድፈት (Mistake):- ስርዓታዊ ያልሆነና አንዱ የሚገድፈውን ሌላው ላይገድፈው የሚችል የቋንቋ አጠቃቀም እክል ዓይነት ነው:: ይህም ከግንዛቤ ችግር፣ ከድካም፣ ከጭንቀት፣ ከችኮላና ከመሳሰሉት ምክንያቶች ሊፈጠር የሚችል የቋንቋ እክል ነው:: ይህ እክል ዓይነት በቋንቋው ተማሪዎች ላይ የሚከሰት ቢሆንም ተማሪዎቹ ከነበሩበት ሁኔታና ስሜት ሲወጡ የፈጠሩትን ግድፈት ያለ አጋዥ በራሳቸው ማረም የሚችሉት መሆኑን መረዳት ይቻላል:: የቋንቋ ማዳጥ (Lapse):- ከስህተትም ከግድፈትም ጎራ ሊመደቡ የማይችሉ የቋንቋ አጠቃቀም እክሎች ናቸው:: ምክንያቶቹ በርካታ ሲሆኑ ከእነዚህም መካከል አካላዊ ወይም አዕምሮአዊ ድካም፣ ትኩረት ማጣት የትውስታ ማነስ እንዲሁም ብስጭትና መጠጥ ሊሆኑ ይችላሉ:: የዚህ የቋንቋ አጠቃቀም እክል በቋንቋው ተማሪዎች የሚፈጠር ቢሆንም የፈጠሩትን የቋንቋ አጠቃቀም እክል መልሰው ራሳቸው ማረም የምችሉት መሆኑ ነው:: በአጠቃላይ በተማሪዎች ድርሰት ጽሁፍ ውስጥ የሚታዩ ስህተቶች ተማሪዎቹ ለታላሚው ቋንቋ ካላቸው ዕውቀት ማነስ ምክንያት የሚፈጠሩና በተማሪው በራሱ ሊታረሙ የማይችሉ ነገር ግን አጋዥ አካል የሚፈልጉ እንዲሁም በቋንቋው አጠቃቀም ሂደት ላይ በሚኖሩ በተለያዩ ሁኔቶች ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉ ነገር ግን በተማሪው በራሱ ሊታረሙ

የሚችሉ የስህተት ዓይነቶች እንዳሉና እንደየመፈጠሪያ ምንጫቸው አንጻር: - የቋንቋ ስህተት (Error)፣የቋንቋ ግድፈት (Mistake) እና የቋንቋ ማዳጥ (Lapse) ተብለው የሚጠሩ የስህተት ዓይነቶች እንዳሉ መረዳት ይቻላል:

ይህ ጥናታዊ ጽሁፍም በተማሪዎች ጽሁፍ ልምምድ ሂደት የሚፈጸሙ ነገር ግን ያለ አጋዥ ሊታረሙ በማይችሉ በቋንቋው ስህተቶች/Errors/ ላይ ትኩረት በማድረግ ስህተቶቹን መለየትና መተንተን እንዲሁም ለስህተቶቹ መከሰት ምንጭ የሆኑትን ጉዳዮች መጠቆም ላይ ትኩረት ያደርጋል:

### 2.1.5. የስህተት ትንተና አስፈላጊነት

በመማር ማስተማር ሂደት በተማሪዎች የሚፈጸሙ ስህተቶችን መተንተን አስፈላጊነትና ፈይዳ ላይ ምሁራን ብዙ ብለዋል: እንደ Sompong (2014) አገላለጽ "የስህተት ትንተና የቋንቋ ስህተቶችን ባህሪያት ለማጥናት፣ የተማሪዎችን የስህተት ዓይነቶች ለመለየትና በአግባቡ ለመተንተን ጠቀሜታው ከፍተኛ ነው።" በመሆኑም በመማር ማስተማር ሂደት ላይ በተማሪዎች የሚፈጸሙ የቋንቋ ስህተቶች መተንተናቸው ፈይዳ አለው: ለዚህም

ተማሪዎቹ ተደጋጋሚ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች መምህራን በመከታተልና በመለየት እንዲሁም በዓይነት አይነታቸው በመመደብ የተማሪዎቻቸውን የቋንቋ ላይ ስህተቶች ለማረም እንዲሁም ለመፈጠራቸውም ምክንያት

የሆኑትን ምንጮች ለመድረስ ጭምር ፈይዳው የጎላ ነው: Norish (1992) የስህተት ትንተና የተለያዩ ጠቀሜታዎች እንዳሉት ይገልፃሉ። ከነዚህ መካከልም መምህራን ስለሚያጋጥሟቸው አዳዲስ ተማሪዎች ዳራዊ እውቀት ለማወቅና ለማገዝ፤ መምህራን ለማስተማር አዲስ ክፍል በገቡ ቁጥር የስህተት ትንተና ለማድረግ ከቻሉ ስለተማሪዎቻቸው ዳራዊ እውቀት መረጃዎችን በማግኘት የትኛውን ይዘት በምን ዓይነት መልኩ እና ለምን ያህል ጊዜ ማስተማር እንዳለበቸው እንዲወስኑ ያግዛል። በሌላ

መልኩ የስህተት ትንተና በአንድ ክፍል ውስጥ በተለያዩ ቋንቋዎች አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ካሉ በሁለተኛ ቋንቋ በመማር ሂደታቸው ላይ ለየትኞቹ ተማሪዎች የትኛው የቋንቋ ክሂል አስቸጋሪ እንደሆነባቸው ለመረዳት ያግዛል በማለት ይገልፃሉ: ስለስህተት ትንተና ምሁሩ ከሰጡት ሀሳብ መርዳት የሚቻለው የስህተት ትንተና ማድረግ በተማሪዎች ላይ ሊኖር የሚችለውን የክሂል ችግር እንዲሁም በታላሚው ቋንቋ ማስተማር ሂደት በየትኛው ቋንቋ አፍ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች የትኛው ክሂል እንደሚቸግራቸው ለይቶ ለመርዳት ለመምህሩ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው: በሌላ መልኩ ለትምህርት ይዘት ምጣኔና የተደራጀ የማስተማር ሂደት እንዲኖር የሚያስችል መሆኑ ነው።

በአጠቃላይ ከምሁሩ አገላለጽ መረዳት የሚቻለው የስህተት ትንተና የተማሪዎችን ዳራዊ ዕውቀት መረጃዎችን ለማግኘት የትምህርት ይዘቶችን ለመለየትና በምን ያህል ጊዜ

ማስተማር እንደሚገባ ለመወሰን፣ የተማሪዎችን ችግር ለመፍታት የሚያስችል የማስተማር ሂደት እንዲኖር፣ የተለያዩ የቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎች ከታላሚው ቋንቋ ክሂል ውስጥ በየትኛው ክሂል ላይ ችግር እንዳለባቸው ለይቶ ለመርዳት እንዲሁም የቋንቋ ትምህርቱ ከመጀመሩና ከተጠናቀቀ በኋላ ትንተና መካሄድ እንዳለበት ይህም አቀራረቡን ለመመዘን፣ ማሻሻያ ለማድረግና የመፍትሄ ሀሳብ ለማፈላለግ የስህተት ትንተና አስፈላጊ ስለመሆኑ ነው:

### 2.1.6. ስህተትን በተመለከተ የሚንፀባረቁ አመለካከቶች

በመማር መስተማር ታሪካዊ ሂደት ውስጥ የሰው ልጅ የግድፈት እርማት ስነ ባህሪውን እየለወጠ ስለመሄዱ ምሁራን ያወሳሉ: በ1960ዎቹ መገባደጃ የሰው ልጅ የመማር ማስተማር ሂደት በባህሪያውያን አተያይ (Behaviorist Approach) ተጽዕኖ ስር ወድቆ እንደነበርና ፍልስፍናውም ግድፈት መስራትን ፈጽሞ የማይፈቅድ፣ ሁሌም ትክክለኛ የሆነ ነገር ላይ የሚያተኩር እንደነበር (Asres 2005) ይገልፃሉ: ምክንቱም በተማሪዎች የሚሰሩ ግድፈቶች ቢኖሩ እንኳን ወዲያውኑ በመምህሩ መታረም አለባቸው የሚል አተያይ የነበረው ፍልስፍና ነበር: የ1960ዎቹ ባህሪያዊያን አተያይ ከስሞ በ1970ዎቹ ብቅ ያለው የአዕምሯዊያን አተያይ (Cognitive approach) ፍልስፍና ደግሞ ስህተትን የሰው ልጅ ባህሪ አድርጎ የሚቆጥርና ለእርማት ትኩረት የሚሰጥ ለመማር ማስተማር የስህተት አመለካከቶችን በተመለከተ "ፍጹማዊ የማስተማር ዘዴ መጠቀም ባለመቻል የሚፈጠር ነው" የሚሉና "በጭራሽ በፍጹማዊ ዘዴ ባለመጠቀም ሳይሆን በተለያዩ ምክንያቶች ስህተቶች ሊፈጠሩ ይችላሉ፤ ፍጹማዊ የሚባል የማስተማር ዘዴም የለም መቅረጽም አይቻልም:" በሚሉ ሁለት ጎራዎች የሚንጸባረቁ አመለካከቶችን ይዞ የመጣ የአዕምሯዊያን አተያይ ነው በማለት በመማር ማስተማር ሂደት ለሚፈጠሩ ስህተቶች የነበራቸውን አተያይ የተለያዩ ምህራን ይገልጻሉ። ይህን የአመለካከት ጎራዎችን Norish (1992) ስገልፁት:- ስህተት የተማሪውን የቋንቋ ችሎታ አመላካችና ተማሪው እንዴት ባለ መንገድ ታላሚውን ቋንቋ እየተለማመደ እንደሆነ ጠቋሚ በመሆኑ ስህተት እንደማያስፈልግ ክስተትና እንደ ነውር የሚቆጠር ሳይሆን በቋንቋ መማር ሂደት አቢይ አካል ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባው ጉዳይ ነው። በተጨማሪም ስህተት ሁልጊዜ የሚፈጠርና ፍጹም ልናቆመው የማንችለው የቋንቋ ትምህርት አንዱ አካል መሆኑን መረዳትና መቀበል ያለብን ጉዳይ ነው በማለት ገልጸዋል: እንደኤፍሬም (2000) ተማሪዎች በሚጽፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የሚፈጠሩ ስህተቶች የትምህርት አካል እንደሆኑና የሚከሰቱትም ስህትቶች መታረም እንዳለባቸው ያስገነዚባሉ። Maarof et al. (2011) በበኩላቸው መምህሩ የሚሰጠው እርማት የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ችሎታ በማጎልበት በኩል መሰረታዊ ጉዳይ እንደሆነና ከግልና ብጤ የእርማት ስልቶች ይልቅ፣ የመምህሩ እርማት የተሻለ እንዲሁም ተማሪዎቹ ለመምህር እርማት ከፍተኛ ቦታ ይሰጣሉ በማለት ይገልፃሉ: የመጀመሪያው አመለካከት ወይም የአስተሳሰብ ጎራ ፍጹም የሆነ የማስተማሪያ

ዘዴን መጠቀም ቢቻል ኖሮ ስህተት አይከሰትም የሚል ነው: የስህተት ምንጩ ከማስተማሪያ ዘዴዎች ድክመት የመነጨ እንደሆነ ከሚገልፁት ወገኖች ሲሆኑ ሁለተኛው በስህተት ላይ የሚያንጸባርቀው አመለካከት ስህተት ሊከሰት የሚችለው በተለያዩ ምክንያቶች እንደሆነና ወደፊትም ሊከሰት የሚችል ፍጹምነት የሌለው እንደሆነ የሚገልጹ ወገኖች እንዳሉ መረዳት ይቻላል: በአጠቃላይ የቋንቋ መማር ሂደት ሙሉ በሙሉ ከስህተት የጸዳ አለመሆኑና በተለያዩ ውስጣዊና ውጫዊ ተጽኖዎች የተጋለጡ ናቸው። በዚህም በመማር ማስተማር ሊፈጸሙ የሚችሉትን የተማሪዎች የተለያዩ ስህተቶች ተከታታይና ቀጣይነት ባለው መልኩ መተንተን ጠቃሚና ተገቢ እንደሆነ ነው። ይህ ጥናትም በመማር ማስተማር ሂደት በተማሪዎች የሚፈጸሙ ስህተቶች ትናንት፣ ዛሬና ነገም የሚኖሩ መሆናቸውን በመገንዘብ ዛሬ ላይ የታዩት ስህተቶች ነገ ላይ እንዳይደገሙ ወይም እንዲቀንሱ ለማስቻል ይጥራል:

### 2.1.7 በስህተት ትንተና ዙሪያ የሚታዩ ችግሮች

Norish (1992) እንደሚገልጹት በስህተት ትንተና ላይ በአንድ ወቅት በስህተትነት የተተነተኑት ወይም የተፈረጁት ጉዳዮች በሌላ ጊዜ ደግሞ ስህተት አይደለም ተብሎ መቅረባቸው ትንተናውን በአግባቡ ለማካሄድ እንቅፋት ፈጥረዋል። የዚህም ምክንያቱ ቋንቋ በማያቋርጥ የለውጥና የእድገት ሂደት ውስጥ የሚያልፍ በመሆኑ <<ዛሬ>> ላይ ሆኖ ትክክል ነው ያሉት ነገር <<ነገ>> ተቀባይነት ላይኖረውና ስህተት ሊሆን ይችላል። በስህተት ትንተና በተለይ አፍ-ፈት የሆኑ በሁለተኛ ቋንቋ የመማር ሂደት አጠቃቀም ላይ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ከሌሎች ጋር በማያያዝ ለማየትና ለመተንተን ከመሞከር አንጻር ከቋንቋ ትምህርት ጥናት በርካታ አስተዋፆኦ እንዳደረገ ምሁራን ይገልፃሉ።

ንጽጽራዊ ትንተና የጥናት ዘዴ በቋንቋ የመማር ሂደት ውስጥ የሚከሰተው ስህተት ምንጩ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት አሉታዊ ሽግግር ብቻ እንደሆነ የሚገልጽ የጥናት መስክ ነበር። እንደ Brown (1994) ገለፃ የስህተት ትንተና ማለት የተማሪዎችን ተግባራዊ እንቅስቃሴ ለመግለጽ ሲባል በበርካታ ሰዎች ዘንድ ተማሪዎቹ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች የሚታዩበት፣ የታዩት ስህተቶች የሚተነተኑበት እና የተተነተኑትም የስህተት ዓይነቶች በተለያዩ ምድብ ዓይነቶች የሚቀመጡበት ስልት እንደሆነ ይገልጻሉ።

በተጨማሪም ስለ ስህተት ያለውን አሉታዊ አመለካከት በማስቀረት ስህተትን እንደ አንድ የትምህርት ሂደት ይቆጠራል። ከዚህም በመነሳት ለሥርዓተ ትምህርት ቀረጻ፣ ለማስተማሪያ መሳሪያዎች ዝግጅት እንዲሁም ተማሪዎች ያሉበትን የዕውቀት ደረጃ ለማመልከት ያገለግላል። በስህተት ትንተና ዙሪያ ከሚታዩ ችግሮች ወይም ድክመቶች ውስጥ የሚከተሉት ተጠቃሾች ናቸው። የመጀመሪያው በስህተት ትንተናው ሂደት ላይ ስህተቶችን እንዲህ ናቸው ብሎ በግልጽ ማስቀመጥ አለመቻል እና ምንጫቸውን በተገቢ ሁኔታ አለመግለጽ፣ ሁለተኛው የስህተት ክፍሎችን ግልጽ በሆነ ሁኔታ አለማስፈር እና ሦስተኛው ተማሪዎች

የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች ቀላል በሆነ መንገድ መከፋፈል አለመቻል ናቸው።ይህ ጥናትም የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች በየዓይነታቸው በመመደብ የሚተነትን እንዲሁም የስህተቶቹ ምክንያት ምን እንደሆነ የሚለይ በመሆኑ ይህንኑ የስህተት ትንተና ድክመቶች በመቅረፍ ረገድ አጋዥ ሊሆን እንደሚችል አጥኚው ያስባል።

### 2.1.8 የስህተት ትንተና ዘዴዎች (Identflcatlon of Errors)

የስህተት ትንተና ምንጮች አከፋፈል ዘዴዎች አንድ ወጥ በሆነ መጠን የሚታወቁ አይደለም፡፡ Lott (1983) እንደሚገልጹት የስህተት ትንተና አከፋፈል ዘዴዎች ዓይነታቸው እጅግ በጣም ብዙ ነው። ከዚህም የተነሳ ወጥነት ያለውና ሁሉም ምሁራን የሚያምኑበትን የስህተት ትንተና አከፋፈል ዘዴን ለይቶ ለማውጣት አልተቻለም። በብዙ ባለሙያዎች በመጠኑም ቢሆን ችግሩን ለመቅረፍ በሚያስችል መልኩ የተሰራባቸውና ለብዙዎች ጥናቶች የመተንተኛ ዘዴዎች ናቸው የተባሉት አራቱ ከዚህ በታች ተብራርተው ቀርበዋል።

#### 2.1.8.1 የስነ ልሳን ቋንቋን መሰረት ያደረገ የስህተት ትንተና ክፍፍል (Linguistic Category Taxonomy)

በዘርፉ በተሰማሩት ባለሙያዎች ጥናትና ምርምር ሲሰራበት የቆየ ነው። ጥናታቸውን ለማካሄድ የፈለጉ ተመራማሪዎች በመጀመሪያ ስህተቶችን በዓይነት በአይነታቸው ከፋፍሎ ማስቀመጥ አለባቸው ከዚያም በመነሳት የቋንቋውን ስነ-መዋቅራዊ ክፍሉን ማስፈር በመቀጠል ለስነ-ልሳናዊ ክፍሎች መሠረት የሆኑ ስነ-ድምጾች፣ ስነ-ምዕላዶች፣ ቃላትና ሀረጋት አጠቃቀማቸውን፣ ስነ-አገባብና ስነ-ፍቺ አመላካች መሆናቸውን ማሳየት። በመጨረሻም ስህተቶቹን ዓይነት በአይነታቸው ከተለየ በኋላ በስ-ነልሳን ቦታቸው በማስቀመጥ መተንተን ነው።

#### 2.1.8.2 በዐረፍተነገር ላዕላይ መዋቅር ላይ የተመሰረተ የስህተት ትንተና ክፍፍል (Surface StrategyTaxonomy)

በቋንቋ በመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች በሚጽፋቸው ወይም በሚያሰፈራቸው ዐረፍተ-ነገሮች ውስጥ የተለያዩ ስህተቶች ሊታዩ ይችላሉ። ተማሪዎች በሚጽፏቸው ወይም የሚያሰፍሯቸው ዐረፍተ-ነገሮች ውስጥ ቃላትን ሊገድፉ ወይም የማያስፈልገውን ሊጨምሩ ይችላሉ። በዚህም የተነሳ ዐረፍተ-ነገሩ በትክክል ላይዋቀር ይችላል። የዚህ ዋነኛ ምክንያትም በዐረፍተ-ነገር ውስጥ ያሉት ቃላት ወይም ሀረጋት ያለቦታቸው መግባት ወይም መስፈርና በተገቢው ቦታ አስፈላጊውን ሥርዐተ-ነጥብ ያለመጠቀምን ያመለክታል። የዚህ ዓይነት የስህተት አከፋፈል ዘዴ በዐረፍተ-ነገር ውስጥ ውጫዊ መዋቅር ላይ የሚታዩ ስህተቶችን መሰረት የሚያደርግ በመሆኑ ተማሪው ቋንቋውን ምን ዓይነት ዘዴ ተጠቅሞ እየተማረ እንዳለ መረጃ በመስጠት ያገለግላል።

### 2.1.8.3 በንጽጽራዊ ትንተና ላይ የተመሰረተ የስህተት ትንተና ክፍፍል (Comparative Taxonomy)

በአፍ መፍቻ ቋንቋ አፉን የፈታ ተማሪ በመማር ማስተማር ሂደት በታላሚው ቋንቋ ስህተት መፈጸሙ አይቀሬ ነው። በነዚህ ሁለት አካላት መካከል የሚደረገውን ስህተቶች አፍ-ፈት ሆኑ ኢ-አፍ-ፈት ተማሪዎች በቋንቋ ለመዳ በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ ስህተት መፈፀማቸው አይቀሬ ነው። ቋንቋውን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች አፍ-ፈት ከሆኑ ተማሪዎች ከሚፈጽሟቸው ስህተቶች ጋር በምን እንደሚመሳሰልና እንደሚለያይ አነጻጽሮ ለማቅረብ የሚያገለግል የስህተት ትንተና አከፋፈል መንገድ ነው። (አንድን ታላሚ ቋንቋ በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች የቋንቋው አፍ-ፈት ከሆኑ ተማሪዎች ከሚፈጽሟቸው ስህተቶች ጋር በምን እንደሚመሳሰልና እንደሚለያይ አነጻጽሮ ለማቅረብ የሚያገለግል የስህተት ትንተና አከፋፈል መንገድ ነው: :)

### 2.1.8.4 ተግባቦታዊ ተጽዕኖን መሰረት ያደረገ የስህተት ትንተና ክፍፍል (Communicative Effect Taxonomy)

የስህተት ክፍፍሉ መሰረት የሚያደርገው ወይም የሚያተኩረው ተግባቦትን መሰረት ያደረገ ስህተቶች አንባቢው መልዕክቱን በትክክል ከመረዳት ወይም ካለመረዳት አንፃር ነው። ይሄውም ተናጋሪው የሚናገራቸው ወይም የሚጽፏቸው ጽሁፎች ለአድማጭ የማይደመጡና ምን ለማለት እንደተፈለገ መልዕክቱን በትክክል በማዳመጥና በማንበብ የማይረዱ ከሆነ ተግባቦታዊ ሂደቱን የሚያስተጓጉሉ ስህተቶች አሉ ማለት ነው። ለነዚህ ስህተቶች መከሰት መነሻ የሚሆኑ ነገሮችን በመለየት ለተግባቦቱ እንቅፋት የሆኑትን ለይቶ በማውጣትና ትክክለኛ የሆነ ተግባቦት እንዲካሄድ የሚያደርግ የስህተት ትንተና ክፍፍል ነው።ይህ ጥናታዊ ስራ ከተጠቀሱት ከአራቱ ስህተት መተንተኛ ዘዴዎች መካከል የስነ ልሳን ቋንቋንመሰረት ያደረገ የስህተት ትንተናና በዐረፍተነገር ላዕላይ መዋቅር ላይ የተመሰረተ የስህተት ትንተና ክፍፍል ላይ ይበልጥ የሚያተኩር ይሆናል።

### 2.1.9 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በተለያዩ በሀገር ውስጥና በውጭ አጥኝዎች ተማሪዎች በድርሰት ጽሁፍ ወቅት በሚፈጽሟቸው ስህተቶች ላይ በርካታ ጥናቶች ተደርጉዋል። እነዚህ ጥናቶችም ተጠኚዎችን በጥቅል በታላሚው ቋንቋ እንዲሁም ተጠኚዎችን በንጥል በታላሚው ቋንቋ በማድረግ የተጠኑ ናቸው።በዚህ ጥናታዊ ስራም አማርኛን ቋንቋ ታላሚ በማድረግ የሌላ ቋንቋ አፍ-ፈት በሆኑ እንዲሁም በአማርኛም ሆነ በሌላ ቋንቋ አፍ-ፈት በሆኑ በሀገር ውስጥ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ በሚፈጽሟቸው ስህተቶች ላይ የተደረጉ ጥናቶች ተዳሰዋል። ከነዚህም አጥኚዎች መካከል አፍ መፍቻ ቋንቋቸው ተለይቶ ያልታወቁ ጥቅል ተማሪዎች በአማርኛ ጽሁፍ ጊዜ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች ያጠኑ:- ገነት (2011)፣ አብይ(1997)

እና ቻላቸው (1998) ሲሆኑ በተለያዩ አገር በቀል ቋንቋዎች አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ በሚፈጽሟቸው ስህተቶች ላይ ጥናት ያደረጉት አጥኚዎች ደግሞ:- በደብሬ (1990)፣ አማረ (1996)፣ ልዑልሰገድ(1997)፣ ምህረት (1998) እና ግርማ (2000) ናቸው::ከዚህ በላይ የተጠቀሱትና ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ በሚፈጽሟቸው ስህተቶች ላይ ጥናታቸውን ያደረጉና ለዚህ ጥናታዊ ስራ መተማመኛ እንዲሆኑ የተመረጡ አጥኚዎች ናቸው። አጥኚዎቹ በተናጥል ስራዎቻቸው የደረሱበትን ውጤት እንደሚከተለው በማቅረብ ከዚህ ጥናታዊ ስራ ጋር ያለሁን ተዛምዶ ለማመሳከር ተሞክሯል። በዚህም መሰረት ደብሬ (1990) እና መሰረት (2003) በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የ11ኛ እና የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች አጥንተዋል። በውጤቱም የስህተት ዓይነቶቹ የቋንቋ አጠቃቀም፣ የቋንቋ አወቃቀር፣ የሥርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም እና የጽንሰ ሀሳብ ግንዛቤ ስህተቶች እንደሆኑ ተጠቅሰዋል። አማረ (1996) አፋቸውን በትግርኛ ቋንቋ የፈቱ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ስነ-ልሳናዊ ስህተቶች ማለትም ስነ ድምፃዊ፣ ስነ-ምዕለዳዊ፣ ስነ-አገባባዊና ስነ-ፍቺያዊ መሆናቸውን አረጋግጠዋል። የስህተት ምንጮቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ፣ የታላሚው ቋንቋ እና የማስተማሪያ መሳሪያዎች ተጽዕኖ መሆኑ ተገልጿል። ልዑልሰገድ (1997) በወላይትኛና በሲዳምኛ ቋንቋዎች አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የፈጸሟቸውን ስህተቶች በድምጽ ደረጃ፣ በቃላት ደረጃ፣ በሀረግ ደረጃ እና በዓረፍተነገር ደረጃ የተፈጸሙ ስህተቶች መሆናቸውን አስቀምጠዋል። ምህረት (1998) በሀድይኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች የቋንቋ አጠቃቀም ስህተቶች፣ የቋንቋ አወቃቀር (የሰዋስው) ስህተቶች፣ የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች እና ከጽንሰ ሀሳብ ጋር የተያያዙ ስህተቶች ናቸው በማለት ገልጸዋል። ግርማ (2000) በጌድኦኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች የቋንቋ አጠቃቀም፣ የቋንቋ አወቃቀር፣ የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም፣ እና የጽንሰ ሀሳብ ግንዛቤ ስህተቶች መሆናቸውን ለይተው አሳይተዋል። ከተጠቀሱት ጥናቶች በተጨማሪ አፍ-መፍቻ ቋንቋቸው ሳይለይ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ በሚፈጽሟቸው ስህተቶች ላይ የተሰሩት ደግሞ የሚከተሉት ናቸው። በገነት (2011) ፣ በአብይ (1997) እና በቻላቸው (1998) የተሰሩ ሲሆኑ የጥናት ግኝታቸውም ዋና ዋናዎቹየተባሉት የሆሄያት ግድፈት እና የቅርጽ ስህተት፣ የቃላት ግድፈት ስህተት፣ የቃላት አመራረጥ እና አጠቃቀም ስህተት፣ የዓረፍተ ነገር አወቃቀር ስህተትና የተጠየቃዊ (የሀሳብ ፍሰት) ስህተት ናቸው በማለት አስቀምጠዋል፡ ፡ በአጠቃላይ ከላይ የተዳሰሱት ጥናታዊ ጽሁፎች በተለያዩ ሀገር በቀል ቋንቋዎች አፋቸውን የፈቱ እና አፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሳይለይ ተማሪዎች በአማርኛ ጽሁፍ ጊዜ ስለሚፈጽሟቸው

ስህተቶች ያጠኑ ናቸው። ጥናቶቹ ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስላቸው ዋና ጉዳይ የስህተት ትንተና (Error Analysis) ጥናት ማድረጋቸው ሲሆን ለጥናቱም መነሻ በመሆን የየበኩላቸውን ቀጥተኛ አስተዋጽኦ አድርገዋል። ይሁን እንጂ ከጥናቶቹ መካከል በገነት (2011) ፣ በአብይ (1997) ፣ በቻላቸው (1998) ፣ በአማረ (1996) ና በምህረት (1998) የተሰሩት ጥናታዊ ስራዎች የስህተት ዓይነቶችን ብቻ በመለየት ትንተና የተሰጠባቸው ነገር ግን ለስህተቶቹ ምንጮች ስለሆኑ ጉዳዮች ያልዳሰሱ ናቸው። ከሀገር ውጭም በዘርፉ የተጠኑ ጥናቶች ተዳሰዋል። Jang (1995) ባደረገው ምርምር የታይዋንን ተማሪዎች የእንግሊዝኛ ቋንቋ የተመለከተ ነበር:: በዚህ ጥናቱ በርካታ ስህተቶች የሚፈጠሩት ከአፍ መፍቻ ቋንቋ አጠቃቀም ጣልቃ ገብነት የመጣ መሆኑንን ማረጋገጥ ችሏል። አጥኚው በዚህ ጥናቱ ያረጋገጠው የታይዋን ተማሪዎች ከእንግሊዝኛ ተናጋሪ ተማሪዎች ጋር ሲነጻጸሩ በእንግሊዝኛ ጽህፍ አጠቃቀማቸው ላይ ከፍተኛ ችግር እንዳለባቸው መድረሱን ነው። በተጨማሪም Chen, L.L (2006) የተባሉ ተመራማሪ በ80 የታይዋን ተማሪዎች ላይ ስለ እንግሊዝኛ ቋንቋ አጻጻፋቸው ላይ ጥናት እና ምርምር ባደረጉት መሰረት በተለይም በአንቀጾች አጠቃቀም ላይ የታዩት ስህተቶች በ11% ከፍተኛ እንደነበሩ አሳይተዋል። በግሶች አጠቃቀም ላይም ያልተናነሱ ስህተቶች እንደነበሩ እና እነኚህንም በ9% ገልጿቸዋል። በተመሳሳይ መንገድ Liu, C.K. Sung, C.S. , and Chien, S. C. (1998) ባደረጉት ምርምር የመጀመሪያ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት በተማሪዎች የጽህፍ ስራ ውስጥ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖ እንደነበረ ያረጋገጡ ሲሆን በተለይም ጀማሪ ተማሪዎች የመጀመሪያ ቋንቋቸውን የመጠቀም ሁኔታቸው ከፍተኛ በመሆኑ ይኸው ለስህተቶቹ ምንጭ እንደሆነ አረጋግጠዋል። በዚህ ጥናታዊ ምርምራቸው ተመራማሪዎቹ ተማሪዎችን በምን መልኩ ማስታወሻ እንደሚጽፉ እንዲያስቡና እንዲገልጹ በማድረግ ተማሪዎቹ በከፍተኛ ሁኔታ ወደ መጀመሪያ አፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንደሚያደሉ አረጋግጠዋል። በአጠቃላይ የተጠቀሱት ጥናቶች ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስላቸው ዋና ጉዳይ የስህተት ትንተና (Error Analysis) ጥናት ማድረጋቸው እንዲሁም ለጽሁፍ ክሂል ዕድገትና የስህተት ትንተናን አስፈላግነት ከማስረጽ አንጻር አንድነታቸው የጎላ መሆን ነው: ጥናቶቹ ለዚህ ጥናት መነሻ በመሆን የየበኩላቸውን አስተዋጽኦ አድርገዋል። ይሁን እንጂ ጥናቶቹ ከስህተት ትንተና ባሻገር እንደዚህ ጥናት የስህተቶቹን ምንጮች አካተው ያላጠኑ ናቸው: ሌሎቹም ቢሆኑ ቋንቋን በጥቅል ማጥናታቸውና በስልጥኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ ስለሚፈጥሯቸው ስህተት ዓይነቶችና ምንጮቻቸው ላይ የተሰሩ አለመሆናቸው እንዲሁም በአብዛኞቹ አጥኚዎች የተጠኑት የኦሞቲክ እና የኩሽትክ ቋንቋዎች ቤተሰብ የሆኑ ቋንቋዎች መሆናቸውና በዚህ ጥናት የሚጠናው ቋንቋ የሴማቲክ ቋንቋ ቤተሰብ በሆነው በስልጥኛ ቋንቋ መሆኑ የተለየ ያደርጋቸዋል።

# ምዕራፍ ሶስት

## 3.1 የጥናቱ ዓይነት

ለዚህ ለታለመው ጥናታዊ ጽህፍ አይነታዊ እና መጠናዊ የምርምር ዘዴን መከተል ተመራጭ ሆኗል:: በመሆኑም ተማሪዎቹ የሚፈጽሟቸውን ስህተት ዓይነቶችና ምንጮች ከአይነታዊ የምርምር ዘዴዎች መካከል በገለጻ መልክ ለማቅረብ ተችሏል:: እንዲሁም የስህተቶቹን መጠንና ድግግሞሽ አሀዛዊ በሆነ መልኩ ለመተንተን መጠናዊ የምርምር ዘዴ አገልግሎት ላይ ውሏል።

### 3.1.2 ጥናቱ የተካሄደበት ቦታና ተሳታፊዎች

#### 3.1.2.1 ጥናቱ የተካሄደበት ቦታ

ይህ ጥናት የተካሄደው በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል በስልጤ ዞን ምዕራብ አዘርነት በርበሬ ወረዳ ሌራ ከተማ ውስጥ በሚገኘው ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ነው:: ለዚህም በዚህ ትምህርት ቤት አጥኚው በመማር ማስተማር ስራ ለብዙ ዓመታት የቆየበት ትምህርት ቤት በመሆኑና በትምህርት ቤቱ ተማሪዎች የድርሰት ጽሁፍ ችግር መኖሩን የታዘበበት በመሆኑ ቦታውን አጥኚው ተመራጭ በማድረግ ጥናቱን ከላይ በተገለጸው ቦታ አድርጓል:: ጥናቱ የተካሄደበት ቦታና አቅጣጫ የሚያሳይ የአየር ላይ ካርታ (በአባሪ ሃያ አንድ ላይ ይመልከቱ)

#### 3.1.2.2 የጥናቱ ተሳታፊዎች

በዚህ ጥናት ውስጥ የተሳተፉት የሌራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በስልጥኛ ቋንቋ አፍ-ፈት ሆነው ዘጠነኛ ክፍል በመማር ላይ ያሉ ተማሪዎች ናቸው:: ለዚህም ምክንያቱ በ2015 ዓ.ም የትምህርት ዘመን በትምህርት ቤቱ በመማር ሂደት ውስጥ ያሉ በመሆናቸው እና የተሻለ መረጃም ይሰጣሉ ተብሎ በመታመኑ ነው። በ2015 ዓ/ም የትምህርት ዘመን በትምህርት ቤቱ በ6 (ስድት) መማሪያ ክፍሎች በአማካይ 55 በአጠቃላይ 330 (169 ወንድ እና 161 ሴት) የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በመማር ላይ ይገኛሉ። በዚህ ጥናት የተሳተፉ ተማሪዎችን ለመምረጥ ቀደምት መሰል ጥናት አይናቶች ባለመኖራቸው ምክንያት በቅድሚያ የጥናቱን ወካይ ቁጥር መወሰን ስለሚያስፈልግ ይኸው ተከናውኗል።

በመጀመሪያ በእያንዳንዱ ዘጠነኛ ክፍል ከሚማሩ ተማሪዎች መካከል በቋንቋው አፍ የፈቱ ተማሪዎች ተለይተው እንዲታወቁ ተደርጓል። በዚህም መሰረት ከአጠቃላዩ 330 ዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ውስጥ 208 ያህሉ በስልጥኛ ቋንቋ አፍ-ፈት መሆናቸው አጥኚው ባደረገው ቀጥተኛ ዳሰሳ በተጨባጭ ተረጋገጠ። ይህ ማለት ደግሞ በጥናቱ ተተኳሪ በሆነው ክፍል ደረጃ ካሉት ተማሪዎች ውስጥ 63% ያህሉ ተማሪዎች በስልጥኛ ቋንቋ አፍ-ፈት ናቸው ማለት

ነው: በመሆኑም በቋንቋው አፍ-ፈት ሆነው ከተለዩት መካከል በቀጥታ በጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት 50%ቱ ወይም (104) ተማሪዎች ናቸው።

### 3.1.3 የናሙና አመራረጥ

እንደ ኃይሉና አላምሮው (2003፣21-26) የጥናቱ አካል የሆነውን ስብስብ በሙሉ /100%/ መውሰድ በማይችልበት ሁኔታ ናሙና እንጠቀማለን። ናሙና ከአጠቃላይ ስብስብ(Population) ውስጥ ስብስቡን ለመወከል በሚመች መልክ ለጥናታዊ ምርምር የሚወሰድ የመረጃ ማግኛ ክፍል ነው። አብዛኛውን ጊዜ ናሙና የሚወሰደው በአጠቃላይ ስብስቡ ውስጥ ያሉ ጥናቱ የሚነካቸው ሰዎች ወይም ሁኔታዎች ብዛትና ስፋት ሲኖራቸውናከጊዜ፣ ከገንዘብና ከሰው ኃይል አንፃር አንድ ላይ ለመጠናት የማይችሉ ሲሆን ነው።ይህ ጥናትም በነዚህ በጥናታዊ ጽሁፍ ቅርጽ /ማኑዋል/ አዘገጃጀት ሊቅ ከሆኑ ምሁራን በተሰነዘረው የናሙና አመራረጥ መሰረት በማድረግ ከሚከተሉት አካላት የናሙና አመራረጥ ተደርጓል።

#### 3.1.3.1 የትምህርት ቤት አመራረጥ

ይህ ጥናት የተካሄደው በስልጤ ዞን ምዕራብ አዘርነት በርበሬ ወረዳ ሌራ ከተማ ውስጥ ሆኖ በከተማዋ ውስጥ በሚገኘው ሌራ ሁለተኛ ደርጃ ትምህርት ቤት የተከሄደ ነው። ይህ ትምህርት ቤት በአመቺ ናሙና አመራረጥ ስልት ተመርጧል: ምክንያቱም አጥኚው በመማር ማስተማር ስራ ለብዙ ዓመታት የቆየበት ትምህርት ቤት በመሆኑና ጥናቱን የሚያካሂደው በትምህርት ቤቱ ከመማር ማስተማር ስራ ጎን ለጎን መሆኑ እንዲሁም ከወጪ፣ ከጊዜና ከድካም መቀነስ አንጻር አመቺ በመሆኑ ጭምር ነው።

#### 3.1.3.2 የክፍል ደረጃ አመራረጥ

ይህ የክፍል ደረጃ በአመቺ የናሙና አመራረጥ ስልት ተመርጧል። ለዚህም ዋናው ምክንያት አጥኚው በዚህ ትምህርት ቤት በመማር ማስተማሩ ስራ ላይ ያለና የክፍል ደረጃውንም የማስተማር ዕድሉ ያለው በመሆኑ፤ በሚመረጠው ክፍል ደረጃ ላይ ያሉ ተማሪዎችም ለጥናቱ የሚሆን መረጃ መስጠት የሚችሉ መሆናቸው በመታመኑ ጭምር ነው። ለዚህ ክፍል ደረጃ መመረጥ አጥኚው በዚው ትምህርት ቤት በመማር ማስተማር ስራ በቆየባቸው ረጅም ዓመታት ውስጥ በተመራጩ ክፍል ደረጃ ላይ ባሉት ተማሪዎች ላይ የድርሰት ጽሁፍ ችግር በጎላ መልኩ መኖሩን መታዘቡ ነው። ከዚህ በተጨማሪ አጥኚው የጥናት ስራውን በዚያው ትምህርት ከመማር ማስተማር ስራ ጎን ለጎን ለማሰኬድ የሚያስችለው በመሆኑ የክፍል ደረጃውን በአመቺ ናሙና መርጧል።

#### 3.1.3.3 የመምህራን አመራረጥ

ለመምህራን ናሙና አመራረጥ ደግሞ አላማ ተኮር ናሙና አመራረጥ ዘዴን ተጠቅሟል። ምክንያቱም የትምህርት ቤቱ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ተተኳሪውን የክፍል ደረጃ

የማስተማር እድሉ ያላቸው በመሆኑ፤ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ሁሉም በአላማ ተኮር ናሙና አመራረጥ የተካተቱ በመሆናቸው ነው: ስለዚህም ከሶስት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ሶስቱም መምህራን ተወስደዋል።

### 3.1.3.4 የተማሪዎች አመራረጥ

በሌራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ በ2015 ዓመተ-ምህረት በስድስት መማሪያ ክፍሎች ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ የሚገኙ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች አጠቃላይ 330 ናቸው። ከነዚህ ውስጥ ጥናቱ ያረፈው በስልጥኛ ቋንቋ አፍ-ፈት ተማሪዎች በመሆኑ በመጀመሪያ በእያንዳንዱ ዘጠነኛ ክፍል ከሚማሩ ተማሪዎች ውስጥ በቋንቋው አፍ የፈቱ ተማሪዎች በአላማ ተኮር ንሞና አወሳሰድ ዘዴ ተለይተው እንዲታወቁ ተደርጓል። በልየተውም 208 ያህሉ በስልጥኛ ቋንቋ አፍ-ፈት መሆናቸው በተጨባጭ ተረጋግጧል። ከነኚህም ውስጥ 50%ቱ ወይም (104) ተማሪዎች በቀጥታ በጥናቱ ተተኳሪ ሆነዋል። እነኚህንም ለመምረጥ ዕኩል ዕድል ሰጪ የንሞና ዘዴ የሆነው የዕጣ ንሞና ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን ይህንንም በመጠቀም ሁሉንም በስልጥኛ አፍ የፈቱ ወካይ ተጠኝዎች እንዲኖራቸውና በጥናቱ ውስጥ እንዲካተቱ አስችሏል።

### 3.1.4 የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

ለዚህ ጥናት መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተመረጡት፤ ተማሪዎች የጻፉት ድርሰቶች፣ የተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቆችና የመምህራን ቃለ-መጠይቆች ናቸው። የመረጃ መሰብሰቢያዎቹ የጥናቱ ዓላማ የሆኑትን በተማሪዎች ድርሰት ውስጥ የሚታዩ ስህተቶችን፣ የስህተት ዓይነቶችንና የስህተት ምንጮች መለየት፣ መፈተሽና መመርመር የሚያስችሉ መረጃዎችን ማስገኘት ነው።

### 3.1.4.1 የተማሪዎች የድርሰት አጻጻፍ መመሪያና ሂደት

የጥናቱን ዋና ዓላማ ለማሳካት በመረጃ መሰብሰቢያነት ያገለገለው በተማሪዎች የተጻፉ ድርሰቶች ናቸው:: አጥኚው ይህን የመረጃ መሰብሰቢያ የመረጠበት ምክንያት በስልጥኛ ቋንቋ አፍ-ፈት የሆኑ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶችና ለስህተቶቹ ምንጮች ሊሆኑ ስለሚችሉ ጉዳዮች ለመለየት የሚያስችል በመሆኑ ነው። ጥናቱን ለማካሄድ በ2015 ዓ.ም በሌራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመማር ላይ ከሚገኙ ከዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በናሙናነት ለተመረጡ ለአንድ መቶ አራት (104) ተማሪዎች አስራ አራት (14) አማራጭ የድርሰት መጻፊያ ርዕሶች ቀርቦላቸዋል:: ርዕሶቹ የተመረጡት ተማሪዎቹ ሀሳብ ያገኙባቸዋል ተብለው የታሰቡና በዘርፉ መምህራን የተገመገሙ ናቸው:: ከቀረቡላቸው አስራ አራት አማራጭ ርዕሶች ውስጥ እያንዳንዱ ተጠኚ ተማሪ 'ያጽፈኛል' ብሎ ያለውን ወይም ብላ ያለችውን ሁለት ርዕሶችን እንዲመርጡ ተደርገዋል:: ወደ መጻፍ ሂደት ከመግባታችው በፊትም ስለአጻጻፍ መመሪያና

ጥንቃቄ በአጥኚውና በደጋፊ መምህራን ግንዛቤ ተሰጥቷቸዋል:: በተሰጣቸው መመሪያና ጥንቃቄ መሰረትም በመረጧቸው ርዕሶች በክፍል ውስጥ እንዲጽፉ ተደርገዋል:: እያንዳንዱ ተጠኚ ተማሪ ሁለት ሁለት ዙር የጻፉት ድርሰቶች በጥናቱ ከታለመለት ዓላማ አንጻር ተፈትሸውና ተለይተው ቀርበዋል:: በዚህ መልኩ የተገኙ መረጃዎችም በመረጃ አተናተን ዘዴ ርዕስ ስር ተተንትነው ቀርበዋል::

### 3.1.4.1.1 የተማሪዎች ድርሰት ቅድመ እርማት ሂደት

በተማሪዎች የተጻፉ ድርሰቶች የእርማት ሂደት ከመከናወኑ በፊት ከዚህ በታች የቀረቡት አተገባበሮች ተግባራዊ ተደርገዋል። በመጀመሪያ ተማሪዎች በድርሰት ጽህፈታቸው የሚፈጽሟቸው ስህተቶች በየምድባቸው ተመድበው ሊተነተኑ የታቀደው የስህተት ዓይነት ክፍል በትምህርት ቤቱ በመረጃ ማሰባሰብ ሂደት ላይ ፈቃደኛ በሆኑ በአማርኛ ቋንቋ መምህራኑ መታወቅ አለበት። ስለዚህም ተማሪዎች የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ክፍፍል መምህራን ተረድተው ሥራቸውን እንዲሰሩ በቅድሚያ ውይይት ተደርጓል። በዚህም መሰረት ቅድመ-ግንዛቤ ስህተት ምድብ በሆኑት ውስጥ የትኛው በየትኛው የስህተት ዓይነት እደሚካተት ከስምምነት ላይ ተደርሷል። ከዚያም ድርሰቶቹ በሦስት ምድብ ተለይተው ለያንዳንዱ ድርሰት መለያ ቁጥር ተሰጥቷቸው ለሶስቱም አራሚ መምህራን ተዳርሷል። አስተራረሙን በተመለከተ አጥኚው ለአራሚ መምህራን አዘጋጅቶ ባቀረበው መመሪያ ላይ ገለፃ ካደረገ በኋላ የጋራ ውይይት ተካሄዷል። በዚህ መሰረት ተማሪዎች የጻፏቸው ድርሰቶች በሦስት ምድብ እንዲለዩ ከተደረገ ቡሁዋላ ለየድርሰቶቹ መለያ ቁጥር ተሰጥቷቸው ለሦስት አራሚ መምህራን እንዲደርሱ ተደርገዋል። በዚህ ሂደት አንድ ተማሪ ለፃፈው አንድ ድርሰት፤ የተማሪውን የክፍሉን ምድብና መለያ ቁጥሩን እንዲሁም ዙሩን ለመለየት የሚያስችሉ መለያ የሚሆኑ ምልክቶችን በመጠቀም ለመለየት ጥረት ተደርጓል።ከዚያም የማረሚያ ምልክቶች መመሪያ ከተሰጣቸው በኋላ የስህተት ዓይነቶች ከተቀመጡ መሰረታዊ የስህተት ዓይነቶችና ሌሎች ስህተቶች አንፃር መምህራን በማየት የተማሪዎችን የድርሰት ውስጥ ስህተቶች በየፈርጁ እንዲለዩና እንዲያርሙ ተደርጓል። እርማቱን ካጠናቀቁ በኋላ በያንዳንዱ የድርሰት መግለጫ ወረቀት ገጽ ላይ ስህተቶቹን በየምድቦቻቸው ለቅመው መዝግበዋል። በመጨረሻም ስህተቶቹ በአጥኚው በፈርጅ በፈርጁ ተጠቃለው ተተንትነዋል።

### 3.1.4.1.2 የጽሁፍ መጠይቅ

የጽሁፍ መጠይቁ ከጥናቱ ዓላማ አንዱ በመሆኑ፤ ተማሪዎች በጽሁፍ ጊዜ ለሚፈጽሟቸው ስህተቶች ምክንያት የሚሆኑ ነገሮች ምን እንደሆኑና የተማሪዎቹም ፍላጎት ምን እንደሚመስል መረጃ ለመሰብሰብ የሚያስችል መሆኑ ከላይ ተገልጿል። በመሆኑም የጽሁፍ መጠይቅ ለጥናቱ በዋናነት የተመረጠ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ በመሆኑ ለተማሪዎች ተዘጋጅቶ ቀርቦላቸዋል::የመጠይቆቹ ይዘትም፡- መምህራን ጽሁፍን የሚያስተምሩበትን

ዘዴ፤ ለመማር ማስተማር ከሚውሉ መሳሪያዎች፤ እንዲሁም ከተማሪዎች ስነ-ልቦናዊ ሁኔታ አንጻር መረጃ እንዲያስገኙ ሆነው የተዘጋጁ ናቸው:: የጽሁፍ መጠይቆቹም ቅርጽ በሶስት ክፍሎች የተከፈለ ነው:: የመጀመሪያው ክፍል የተማሪዎችን ዳራዊ መረጃ የሚጠይቅ መጠይቆችን የያዘ ነው:: ሁለተኛው ክፍል ጽሁፍን በተመለከተ መምህራን የሚያስተምሩበትን ዘዴና ተማሪዎችም መምህራን በሚያስተምሯቸው በጽሁፍ ማስተማር ዘዴ ላይ ያላቸውን ተነሳሽነትና ፍላጎት ምን እንደሚመስል መረጃ ለማግኘት የሚያስችሉ የምርጫ ጥያቄዎች የቀረቡበት ነው:: ሶስተኛውና የመጨረሻው ክፍል ተማሪዎች፤ በተማሪዎች ጽሁፍ ስህተትና በስህተት ምንጮቹ ላይ የራሳቸውን ሀሳብ በጽሁፍ እንዲገልጹ የተደረገበት ክፍት ጥያቄዎችን የያዘ ክፍል ነው:: መጠይቆቹ ለተጠኚ ተማሪዎች ከመቅረባቸው በፊት ስለተገቢነታቸው ሁለተኛ ድግሪ የትምህርት ዝግጅት ባላቸው በሁለት አማርኛ ቋንቋ መምህራን ተፈትሸዋል። በመቀጠልም በአጥኚው አማካሪ ተገምግመዋል:: በግምገማውም ሂደት የተገኙ ድክመቶች እንዲስተካከሉና እንዲሻሻሉ ተደርገዋል:: በዚህ መልኩ የተዘጋጁት የጽሁፍ መጠይቆች በስልጥኛ ቋንቋ አፍ-ፈት መሆናቸው በተጨባጭ ከተለዩት ከ208 ተማሪዎች መካከል በጥናቱ ተተኳሪ ለሆኑት ለ50% ቱ ወይም 104 ተማሪዎች በቀጥታ ከመሰራጨታቸው በፊት የመጠይቆቹን ተገቢነት ለማረጋገጥ ሲባል ከነዚህ ተማሪዎች መካከል አንድ ሶስተኛ (35) በሚሆኑ ተማሪዎች የቅድመ-መጠይቅ ሙከራ ተደርጓል። ቅድመ-መጠይቆቹ ከተሰበሰቡ ቡሁዋላ ባስገኙት ውጤትና ተገቢነት አንጻር ግምገማና ማሻሻያ ከተደረገባቸው ቡኋላ ለጥናቱ ተተኳሪ ለሆኑ ለሁሉም ተማሪዎች እንዲቀርቡ ሆነዋል:: በዚህም ሂደት የተገኙ መረጃዎች በምን ዓይነት መልኩ መተንተን እንዳለባቸው ተገልጸው በመረጃ አተናተን ዘዴ ርዕስ ስር ተተንትነው ቀርበዋል::

#### 3.1.4.1.3. የመምህራን የቃለ-መጠይቅ አዘገጃጀት

ለመምህራን የተዘጋጁት ቃለ-መጠይቆች ለተጠያቂ መምህራን ከመቅረባቸው በፊት ስለተገቢነታቸው በአጥኚው አማካሪ ተገምግመው ለተመረጡና ልምዱ ላላቸው ለአማርኛ ቋንቋ መምህራን ቀርቦላቸዋል። የመጠይቁም አላማ ጽሁፍን በተመለከተ የተማሪዎቹን ዳራ ለማወቅ፤ የመርሀትምህርቱና የመማሪያ መጽሀፍ የጽሁፍ ክሂልን በማዳበር በኩል ያላቸውን አዎንታዊና አሉታዊ ጠቀሜታ፤ የስህተት ዓይነቶችንና የስህተት ምንጮችን እንዲሁም የመማር ማስተማሩን ሂደት በሚመለከት መምህራን ስላላቸው አስተያየት መረጃ ማሰባሰብ ነው: በዚህም ሂደት የተገኙ መረጃዎች በምን ዓይነት መልኩ መተንተን እንዳለባቸው በመረጃ አተናተን ዘዴ ርዕስ ስር ተተንትነው ቀርበዋል:

### 3.1.5 የመረጃ አተናተን ዘዴ

ይህ ክፍል በመረጃ ማግኛ ዘዴዎች የተሰበሰቡትን መረጃዎች የመረጃ ምንጭነታቸውን በመፈተሽና በማረጋገጥ ትንታኔ የሚሰጥበት ነው። በዚህም መሰረት ተተኳሪ ተማሪዎቹ

ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተት ዓይነቶች፤ ለስህተቶቹ ምንጭ የሆኑትን ጉዳዮች፤ በተተኳሪ ተማሪዎች የተፃፉ የድርሰት ፈተናዎች እንዲሁም በተለያዩ መንገዶች የተገኙትን መረጃዎች ዓይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ዘዴ በመጠቀም ገለፃዊ በሆነ መልኩ ትንተናው የተካሄደ ሲሆን የስህተቶቹን መጠንና ድግግሞሽ፤ በጽሁፍ መጠይቅ፣ በቃለ-መጠይቅና በድርሰት ጽህፍ ፈተና የተሰበሰቡትን ውጤቶች አሀዛዊ በሆነ መልኩ ለመተንተን መጠናዊ የምርምር ዘዴ አገልግሎት ላይ ውሏል።ከተለያዩ ምንጮች፤ በድርሰት መልመጃዎች፣ በጽሁፍ መጠይቅና በቃለ-መጠይቅ ዘዴዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች በአጥኚው ምልከታ እየተዳኙ ከጥናቱ ርዕስ ጋር እየተገናዘቡ ተተንትነዋል:: በሂደቱም ለአተገባበር ትክክለኝነት የአቀራረብ ቅደምተከተል በጥንቃቄ ተከናውኗል:: ቅደምተከተሉም መረጃ ሰጪዎችን ማሳወቅ፤ የተሰበሰቡ መረጃዎችን ከትንተናው በፊት ተፈትሸውና ተለይተው በተለያዩ የትንተና ዘርፎች ስር መመደብ፤ ለትንተናው በሚመች መልኩ በሰንጠርዥ ቁጥርና መጠሪያ ተሰጥቶ ቅድመ-ትንተናና ገለጻ ተደርጓል:: በመቀጠልም እንደየትንተናው በህሪይ፤ በመቶኛና በአማካይ ነጥብ እየተገለጸ ከጥናቱ ርዕስ ጋር እየተገናዘበ ቀርቧል::

### 3.1.5.1 የድርሰት መረጃዎች ትንተና

የስህተት ትንተናን ለማከናወን ከምንገለገልባቸው ዘዴዎች መካከል ለዚህ ጥናት በአጥኚው የተመረጠው ቅድመ-ግንዛቤን መሰረት ያደረገ የስህተት ትንተና ዘዴ ነው። ይህም ማለት አስቀድሞ በተለየ ምድብ የተማሪዎችን ስህተቶች መመደብ ነው። እናም በተማሪዎች ድርሰት ውስጥ የታዩት ስህተቶች ቀደም ሲል በተመረጡና በታወቁ የስህተት ዓይነቶች የተከፈለ እና በየምድባቸው የተቀመጡ ናቸው። ለዚህም መነሻ የሆነውን ጉዳይ Dulay and etal (1982)፣ Brown (1994) እንደገለጹት ለዚህ መሰረቱ አጥኚው በማስተማር ሂደት የተመለከታቸው ችግሮች ናቸው። ካሉ በሁዋላ በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የሚፈጠሩ ስህተቶችን በተለያዩ ክፍሎች እንደሚከፈሉ ይገልፃሉ። በተጨማሪም የሀገር ውስጥ አጥኚዎችም (ተገኝ (2000)፣ መሰረት (2003)):- የስህተቶችን ክፍፍሎች፡-

- የቋንቋ አጠቃቀም ግድፈቶች፤
- የቋንቋ አወቃቀር ግድፈቶች፤
- የስርአተ-ነጥብ አጠቃቀም ግድፈቶች፤
- የጽንሰ-ሀሳብ ግንዛቤ ግድፈቶችና
- መለየት ያልተቻሉ ግድፈቶች በሚል መድበውት ጥናታቸውን አካሂደዋል::

አጥኚውም በመማር ማስተማር ልምድ ቆይታው ከተመለከተቻው ስህተቶች አፈጻጸም አንጻር፤ በቋንቋ ትምህርት ልምዱ ካላቸው መምህራን ካገኛው ልምድ በመነሳት የጥናቱን ዓላማ ያሳካሉ ብሎ ያመነባቸውን የሚከተሉትን ቅድመ ግንዛቤን መሰረት ያደረጉ የስህተት አከፋፈል ዘዴን ተጠቅሟል:

- *የቋንቋ አጠቃቀም ስህተቶች፤*
- *የቋንቋ አወቃቀር ስህተቶች፤*
- *የስርዓተ-ነጥቦች አገባብ ስህተቶች፤*
- *ለመለየት ያልተቻሉ ስህተቶች ናቸው:*

በየድርሰቶቹ ውስጥ የተገኙ የቋንቋ አጠቃቀም ስህተቶች፡- (ከሆሂያት ቅርጽ፣ ሳድስና ሳልስ ከመለየት፣ ከሆሂያት ጭመራና ቅነሳ፣ ከሆሂያት ቦታ ቅይይር፣ ከአላስፈላጊ ድግግሞሽ፣ ከቃላት ምርጫ፣ ከአፍ-መፍቻ ቋንቋ ቃላት ጣልቃ ገብነትና ከትርጉም አልባ ቃላት አጠቃቀም)፤ የቋንቋ አወቃቀር ስህተቶች፡- (ከባለቤትና ከግስ መጣጣም፣ ከባለቤትና ከተሳቢ መጣጣም፣ ከጾታ፣ ከመደብና ቁጥር ወዘተ...) አወቃቀር፤ ከስርዓተ-ነጥቦች አገባብ ስህተቶች እና ለመለየት ያልተቻሉ ስህተቶች አንጻር እየለዩ ማውጣትና መመዝገብ እንዲሁም ለስህተቶቻቸው መፈጠር ምክንያት የሆኑ ጉዳዮችን መጠቆም ስራ ተከናውኗል:: በመቀጠልም በተጠቀሱት በያንዳንዱ ቅድመ-ግንዛቤ ስህተት ምድቦች ስር የተገኙ የስህተት ስርጭቶች በየፈርጁ እንዲመዘገቡ ከተደረጉ ቡሁዋላ ስህተቶቹ እንደየስህተት በህሪያቸው ተተንትነዋል።

### 3.1.5.2 የጽሁፍ መጠይቅ መረጃዎች ትንተና

ለጥናቱ ዓላማ ማሳኪያ የሚሆኑ መረጃዎችን ያስገኛሉ ተብለው በመረጃ መሰብሰቢያነት ከተመረጡት ውስጥ አንዱ የጽሁፍ መጠይቅ ነው:: ይህ የጽሁፍ መጠይቅ የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች ከሚጽፏቸው ድርሰቶች በተጨማሪ ለጥናቱ የሚያስፍልገውን መረጃ በጽሁፍ እንዲሰጡ ለማስቻል የቀረበ ነው:: ዋና ዓላማው ከተማሪዎች ድርሰት ጽሁፍ ከተገኙ መረጃዎች ጋር በማስተያየት የመረጃዎችን ትክክለኝነት ለማረጋገጥ እንዲያስችል ነው::በመሆኑም በተለያዩ ምሁራን የስህተት ምንጮች ተብለው የተጠቀሱትን:- የመማር ማስተማር ዘዴና ማስተማሪያ መሳሪያዎች፤ የተማሪዎች ስነ-ልቦና እንዲሁም የውስጥ ቋንቋ በተማሪዎች ጽሁፍ ክሂል ላይ ተጽዕኖ እያሳደሩ እንደሆነ ለመፈተሽ የሚያስችሉ መጠይቆች ለተማሪዎቹ ቀርበዋል:: መጠይቆቹ በሁለት መልክ የቀረቡ ናቸው:: የመጀመሪያው ከጥያቄ ቁጥር አንድ እስከ ጥያቄ ቁጥር ሃያ (1-20) ድረስ ያሉ ዝግ ጥያቄዎችና የተለያየ መጠን ያላቸው አማራጮች ያሉዋቸው ሲሆኑ ሁለተኛው አቀራረብ ክፍት የሆነና ተማሪዎቹ በተማሪዎች ድርሰት ውስጥ ስለሚፈጽሙት ስህተቶችና በስህተቶቹ ምንጮች ላይ የራሳቸውን ሀሳብ እንዲገልጹ የተደረገበት ክፍል ነው:: በዚህም መሰረት በጥናቱ ቀጥተኛ ተተኳሪ ሆነው ለተመረጡ ለመቶ አራት (104) ተማሪዎች መጠይቁ የተዘጋጀ ቢሆንም በአተገባበር እቅድ ዕለት በተለያዩ ምክንያቶች ሰባት (7) ተማሪዎች በጽሁፍ መጠይቁ ተሳታፊዎች ሳይሆኑ ቀርተዋል:: የተቀሩት ዘጠና ሰባት(97) ተማሪዎች በሶስት ምድብ ተከፍለው በአጥኚውና የጽሁፍ መጠይቅ አሞላል መመሪያ ግንዛቤ ከተሰጣቸው ሁለት

መምህራን ጋር በመሆን መጠይቁን እንዲሞሉ ተደርገዋል:: ተማሪዎቹም ለአሞላሉ በተሰጣቸው ሰዐት መሰረት ሞልተው የሰጡት የሶስቱም ምድብ የጽሁፍ መጠይቅ ወረቀቶች ተሰብስበው የጽሁፍ መጠይቁን በማስሞላት ከተባበሩ መምህራን ጋር በመሆን በጥልቀት ተፈትሸዋል:: በሂደቱም አጠቃላይ ዘጠና ሰባት(97) ተማሪዎች ከሞሉት ጽሁፍ መጠይቅ ውስጥ:- ያልተፈለጉ ጽህፎችን የያዙ አራት እንዲሁም ምንም ዓይነት መረጃ ያልሰጡ ሁለት በድምሩ ስድስት (6) የጽሁፍ መጠይቅ ወረቀቶች ተለይተው እንዲወጡ ተደርገዋል:: እንዲለዩ የተደረገበትም ምክንያት ‹የጥናቱን ውጤት በማዛባት ተዓማኒነትን ያሳጣሉ› ተብለው በመታሰባቸው ነው:: በመሆኑም ለጥናቱ ብቁ ሆነው የተገኙት የተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቆች ዘጠና አንድ (91) ናቸው:: በነዚህ በዘጠና አንድ (91) ጽሁፍ መጠይቅ ወረቀቶች የተገኙ መረጃዎች እያንዳንዱን መጠይቅ እንደየአጠያየቅ ዓላማቸውና በተሰጡት ምላሾች መሰረት የተገኙት ውጤቶች በምዕራፍ አራት የውጤት ትንተና ርዕስ ስር በዝርዝር በገለጻ ተተንትነው ቀርበዋል:

### 3.1.5.3 የቃለ-መጠይቅ መረጃዎች ትንተና

በዚህ ጥናት ሶስተኛው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ቃለ-መጠይቅ ነው። ቃለ-መጠይቁ የቀረበው በትምህርት ቤቱ ጥናቱ እየተደረገባቸው ያሉ ተማሪዎችን በማስተማር ላይ ላሉና ያስተምሩ ለነበሩ ሶስት አማርኛ ቋንቋ መምህራን ነው:: ለመምህራን የቀረበው ቃለ-መጠይቅ የተለያዩ ሀሳቦችን የያዘ ሲሆን የቃለ-መጠይቁ ይዘቶች በስልጥኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ በሚፈጽሟቸው ስህተቶች ዙሪያ ትኩረት ያደረገ ነው። ለመምህራኑ የቀረቡት ቃለ-መጠይቆች በተማሪዎች ለሚፈጸሙ ለድርሰት ልምምድ ሂደት ስህተቶች እንደምንጭነት ሊጠቀሱ ይችላሉ ተብለው ለታሰቡት:- ለመማር ማስተማር ዘዴዎች፤ ለማስተማሪያ መሳሪያዎች (የተማሪው መጽሀፍ፣ መርሀ-ትምህርት...አዘገጃጀት) እንዲሁም የተማሪዎች የጽሁፍ ላይ ልምምድ ተነሳሽነት ምን ይመስላል? ለተማሪዎቹስ የድርሰት ልምምድ ሂደት ለሚፈጽሙት ስህተቶች እንደምክንያት ሊጠቀሱ ይችላሉ? ወይስ አይችሉም? የሚለውን ለማረጋገጥ በተለያየ መልኩ የተዘጋጁ ሰባት (7) ቃለ-መጠይቆች ቀርበዋል። ለቀረቡት ቃለ-መጠይቆችም መምህራኑ ካላቸው ከመማር ማስተማር ልምድ በመነሳት ምላሻቸውን ሰጥተዋል:: በቃለ-መጠይቆቹም በተሰበሰቡ መረጃዎች የተገኙት ውጤቶች በውጤት ትንተና ርዕስ ስር ተተንትነው በገለጻ ቀርበዋል:: መጠይቆቹ የተዘጋጁት በተቀራራቢ የጥናት ርዕስ ጥናት ካደረጉት፤ እስጢፋኖስ ተረፈ (2012) ለመምህራን ካዘጋጁት ቃለ-መጠይቅና አዲስዓለም ዘሪሁን (2012) ለመምህራን ካዘጋጁት ከጽሁፍ መጠይቅ ሞዴል በመውሰድና ለዚህ ጥናት በሚያመች መልኩ በማስተካከል ነው።

# ምዕራፍ አራት

## 4.1 የጥናቱ ውጤት ትንተናና ማብራሪያ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በስልጥኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጸሙ ስህተቶች፣ የስህተት ዓይነቶችና የስህተቶቹን ምንጮች መፈተሽ ነው።

ከዚህም በመነሳት በጥናቱ የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ የታቀደ መሆኑ በምዕራፍ አንድ ተገልጿል።

- በስልጥኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች የትኞቹ ናቸው?
- ተማሪዎቹ በድርሰቶቻቸው ውሰጥ ለሚፈፅሙት ስህተቶች ምንጮቻቸው ምን ምን ሊሆኑ ይችላሉ?
- ከተጽዕኖ ምንጮቹ በተማሪዎቹ ድርሰት ውስጥ በንጽጽር ጎልቶ የታየው የትኛው ነው?
- ችግሩን መቀነስ የሚቻለው እንዴት ነው? ለሚሉት የጥናቱ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ለጥናቱ

በተመረጡ ተማሪዎች ከተጻፉ ድርሰቶችና ከቀረቡላቸው ጽሁፍ መጠይቆች እንዲሁም ከመምህራን ቃለ-መጠይቅ ተሰብስበው የተገኙ መረጃዎች በዚህ ምዕራፍ ስር በሚከተለው መልኩ ተተንትነዋል።

### 4.1.1 በተማሪዎች ድርሰት አተገባበር ወቅት የነበረ ሂደት መረጃ ትንተና

በሌራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ በ2015 ዓ.ም በዘጠነኛ ክፍል በመማር ላይ የሚገኙ ሶስት መቶ ሰላሳ (330) ተማሪዎች አሉ። ከነዚህም ተማሪዎች ውስጥ ሁለት መቶ ስምንቱ (208) አፋቸውን በስልጥኛ ቋንቋ የፈቱ በመሆናቸው ለጥናቱ ተለይተዋል። ከተለዩት ተማሪዎች ውስጥ አንድ መቶ አራት (104) ተማሪዎችን በቀላል የእጣ ንሞና ዘዴ በመምረጥ ጥናቱ ተከናውኗል። ተጠኝ ተማሪዎቹ ድርሰቶቹን በሁለት ዙር እንዲጽፉ ሆኗል፡ ፡ ይህም እንዲሆን የተደረገበት ምክንያት በአንድ ጊዜ በተጻፈ ድርሰት ስህተትን እንደስህተት ቆጥሮ መተንተን አሳማኝ ሊሆን ስለማይችል ነው። ተማሪዎች በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ ሆነው ሊጽፉ ስለሚችሉ እንዲሁም በሌሎች ምክንያቶች ጭምር ለድርሰቱ ዓላማ ማሳኪያ ሊሆኑ የሚችሉ መረጃዎች የተዛቡ እንዳይሆኑ ለማስቻል ሲባል ነው።

የድርሰት ፈተናው በሁለት ዙር እንዲከናውን ሲደረግም፤ በድርሰት አንድ ሶስት(3) እና በድርሰት ሁለት አንድ (1) በድምሩ ሶስት (3) ተማሪዎች በተለያዩ ምክንያቶች ሳይሳተፉና ሳይጽፉ ቀርተዋል:: በመሆኑም መርጃ ይሰጣሉ ተብለው ከታቀዱት ከአንድ መቶ አራት

(104) ተማሪዎች ሁለት መቶ ስምንት (208) የድርሰት ፈተናዎች ይሰበሰባሉ ተብሎ ቢታሰብም በመጀመሪያ ዙር አንድ መቶ ሁለት (102)፣ በሁለተኛ ዙር አንድ መቶ ሶስት (103) በአጠቃላይ ሁለት መቶ አምስት (205) የድርሰት ፈተናዎች ተሰብስበዋል።

በተጠኝ ተማሪዎች ከተጻፉት ድርሰቶች ውስጥ በመጀመሪያ ዙር 08፣ በሁለተኛ ዙር 09 በአጠቃላይ 17 ድርሰቶች በእጅ ጽሁፍ ባለመሳካታቸው ምክንያት ከጥናቱ ውጭ ተደርገዋል። እነዚህ ያልተሳኩ የተባሉት ድርሰቶች ምን ሀሳብ እንደያዙ ለመረዳት አዳጋች በመሆናቸው፤ ያሉባቸውን ስህተቶች ለይቶ ለማውጣት አስቸጋሪ በመሆናቸውና በጥናቱ ውስጥ ቢካተቱ መረጃ ያዛባሉ ተብለው በመታሰባቸው ከሌሎቹ የድርሰት ጽህፎች እንዲለዩና በጥናቱ ውስጥ እንዳይካተቱ ተደርገዋል።

በአጠቃላይ በተጠኚ ተማሪዎች የተጻፉትን አንድ መቶ ሰማንያ ስምንት (188) ድርሰቶች ከዚህ በታች ባለው ሰንጠረዥ ውስጥ ጠቅለል ባለ መልኩ ለማስቀመጥ ተሞክሯል።

ሰንጠረዥ አንድ: - በድርሰት መልመጃዎችን አተገባበር ሂደቶች የሚያሳይ ሰንጠረዥ።

| የድርሰት ዓይነት | የትግበራ ጊዜ | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ድርሰት አንድ | 10/4/14/4/15 | 104 | 2 | 102 | 8 | 94 |
| ድርሰትሁለት | 17/4/21/4/15 | 104 | 1 | 103 | 9 | 94 |
| አንድና ሁለት | 10/4/21/4/15 | 208 | 3 | 205 | 17 | 188 |

መግለጫ:- በሰንጠረዡ ውስጥ (1)= የሚገልጸው (የታቀዱ ተማሪዎች ብዛት) (2) የሚገልጸው (ከታቀዱ ተማሪዎች ውስጥ ያልጻፉ ተማሪዎች ብዛት) (3)= የሚገልጸው (ከታቀዱ ተማሪዎች ውስጥ የጻፉ ተማሪዎች ብዛት) (4) የሚገልጸው (ያልተሳኩ ድርሰቶች ብዛት) (5) የሚገልጸው (የተሳኩ ድርሰቶች ብዛት) የሚል ይሆናል። በመቀጠልም በ188 ድርሰቶች ውስጥ የተገኙ የስህተት ስርጭቶች እንደየምድቦቻቸው በሚከተለው መልኩ ተተንትነዋል::

### 4.1.2 በድርሰቶች ውስጥ የተገኙ አጠቃላይ የስህተቶች ብዛት

ከላይ እንደተገለጸው ለተማሪዎች በሁለት ዙር በቀረቡ ድርሰቶች ውስጥ የተገኙ አጠቃላይ ስህተቶች መለየት ተግባር ተከናውኗል:: በመቀጠል የስህተቶቹ ስርጭት እንደየስህተት ምድቦቻቸው ተለይተው አጠቃላይ ትንተና ተሰጥተውባቸዋል:: ለትንተናውም በአንድ ድርሰት ውስጥ በአማካይ ምን ያህል ቃላት እንዳሉት ለማወቅ:- የአንድ ድርሰት አማካይ የቃላት ብዛት= የቃላት ብዛት ሲካፈል ለድርሰት ብዛት፤ የአንድን ድርሰት አማካይ ስህተቶች ለማወቅ:- አማካይ ስህተት= አጠቃላይ የስህተት ብዛት ሲካፈል ለአጠቃላይ የድርሰት ብዛት፤ በመቶ ቃላት አንድ ስህተት የሚፈጸምበትን መጠን ለማወቅ:- የስህተት ድርግግሞሽ= አማካይ ስህተት ሲባዛ በ100 ሲካፈል ለአማካይ ቃላት፤ አንድ ስህተት

የሚገኝበትን የቃላት ብዛት ለማወቅ እንዲሁም የትክክለኝነት ተዛማጅነት= አጠቃላይ የቃላት ብዛት ሲካፈል ለአጠቃላይ የስህተት ብዛት በሚለው ቀመር መሰረት ትንተናው ቅደም-ተከተሉን ጠብቆ ተከናውኗል::

በዚው መሰረት በተጠኚ ተማሪዎች በተጻፉባቸው ድርሰቶች ውስጥ የተጻፉባቸው ቃላት ተቆጥረው ብዛታቸው ታውቋል:: አጠቃላይ ቃላቱ ተማሪዎች ለጻፏቸው ድርሰቶች ቁጥር ተካፍለው እያንዳንዱ ድርሰት አማካይ ቃላት ተለይቷል:: በተጠኚ ተማሪዎች በተጻፉ በሙሉ ድርሰቶች ውስጥ የተፈጸሙ ስህተቶች ተቆጥረው ብዛታቸው ታውቋል:: አጠቃላይ ስህተቶች ለአጠቃላይ ድርሰቶች ተካፍለው አማካይ ስህተት ብዛት ተለይቷል:: አማካይ ስህተቶች በመቶ ተባዝተው ውጤቱ ድርሰቶቹ ለተጻፉባቸው አማካይ ቃላት ተካፍለው በመቶ ቃላት ውስጥ ያለው የስህተት ድግግሞሽ ተለይቷል:: በመጨረሻም አጠቃላይ የቃላት ብዛት ለአጠቃላይ የስህተት ብዛት ተካፍለው አንድ ስህተት በምን ያህል ቃላት ውስጥ እንደሚገኝ በትክክለኛነት ተዛማጅነት ታውቋል::

ከላይ በቀረበው አሰራር መሰረት በጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች በሁለት ዙር የተጻፉት 188 ድርሰቶች በ11253 ቃላት የተጻፉ ናቸው:: ከነዚህም ቃላት ውስጥ ስህተቶቹ ተቆጥረው 4558 መሆናቸው ተረጋግጠዋል:: በተጻፉት ድርሰቶች ውስጥ ያሉት አማካይ ቃላት ብዛትም 59.85 ናቸው:: የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች በሁለት ዙር ከጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የመጀመሪያው ከ5417 ቃላት ውስጥ የስህተት ብዛት 2589 እና በመቶኛ ሲሰላ 48.1 ሲሆን በሁለተኛው ድርሰት ከ5836 ቃላት ውስጥ የስህተት ብዛት 1969 እና በመቶኛ ሲሰላ 51.9 ሲገኝ ባጠቃላይ በሁለቱም ድርሰቶች ውስጥ 4558 ስህተቶች ተገኝተዋል:: በሁለቱም ድርሰቶች ውስጥ 24.24 አማካይ የስህተት መጠን አሳይቷል:: ከመጀመሪያው ድርሰት 57.63 አማካይ ቃላት ውስጥ የተፈጸሙ የድግግሞሽ ብዛት 47.8 እንዲሁም ከሁለተኛው ድርሰት 62.1 ቃላት ውስጥ የተፈጸሙ የድግግሞሽ ብዛት 33.7 መሆኑ ሲታወቅ በአጠቃላይ በሁለቱም ድርሰቶች ውስጥ ባሉ በ59.85 አማካይ ቃላት ውስጥ የተፈጸሙ የስህተት ድግግሞሽ ብዛት 40.5 ነው:: በመጨረሻም የያንዳንዱ ድርሰት የተጻፉባቸው አጠቃላይ ቃላት ለአጠቃላይ ስህተት ቃላት ተካፍለው 2.09 እና 2.96 በመሆን የትክክለኛነት ተዛማጅነት ውጤት ተሰልቶ 2.47 ሆኗል:: ይህ ማለት ደግሞ በየ2.47 ቃላት ውስጥ አንድ ስህተት የሚፈጸም መሆኑን ነው:: ከላይ የተገለጹትን አጠቃላይ መረጃዎች በሚከተለው ሰንጠረዥ ውስጥ ጠቅለል ባለ መልኩ ለማስቀመጥ ጥረት ተደርጓል::

ሰንጠረዥ ሁለት:- የድርሰት አይነቶችንና የስህተት አቀማመሮች አንጻር መረጃ የሚሰጥ ሰንጠረዥ:-

| የድርሰት ዓይነት | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ድርሰት አንድ | 94 | 5417 | 57.63 | 2589 | 48.1 | 27.54 | 47.8 | 2.09 |
| ድርሰት ሁለት | 94 | 5836 | 62.1 | 1969 | 51.9 | 20.95 | 33.7 | 2.96 |
| ድርሰት አንድና ሁለት | 188 | 11253 | 59.85 | 4558 | 100 | 24.24 | 40.5 | 2.47 |

መግለጫ:- በሰንጠረዡ ውስጥ (1) የሚገልጸው (የድርስቶቹን ብዛት) (2) የሚገልጸው (ድርሰቶቹ የተጻፉበትን ቃላት ብዛት) (3) የሚገልጸው (የአማካይ ቃላት ብዛት) (4) የሚገልጸው (በመቶኛ ሲሰሉ) (5) የሚገልጸው (ድርሰቶቹ ውስጥ ስህተት ብዛት) (6) የሚገልጸው (አማካይ ስህተቶች ብዛት) (7) የሚገልጸው (የስህተት ድግግሞሽ) እና (8) የሚገልጸው (ትክክለኛነት ተዛማጅነት) ነው::

### 4.1.3 በድርሰቶች ውስጥ የተገኙ ዋና ዋና የስህተት ዓይነቶች፡-

በምዕራፍ ሶስት የድርሰት አተናተንን በተመለከተ እንደተገለጸው ስህተቶች በዓይነት የተለዩትና የተመደቡት በቅድመ ምድብ የስህተት ዓይነት ምድቦች አማካይነት ነው:: በመሆኑም በዚህ ጥናት ውስጥ የተተኮረባቸው የስህተት ዓይነቶች የቋንቋ አጠቃቀም፣ የቋንቋ አወቃቀር፣ የስረዓተ-ነጥብ አጠቃቀምና መለየት ያልተቻለ ስህተቶች ናቸው::

በአጠቃላይ በሁለቱም ድርሰቶች ውስጥ በሁሉም ስህተት ምድቦች ስር 4558 ስህተቶች ተቆጥረዋል። ከተቆጠሩት ከ4558 ስህተቶች ውስጥ 3660 ያህሎቹ በቋንቋ አጠቃቀም ምድብ የተከሰቱ ናቸው:: ይህም በመቶኛ ሲሰላ 80.3% ሆኗል:: የስህተት አማካይ መጠኑም 19.46 ሲሆን በመቶ ቃላት ውስጥ የተገኘው አማካይ የስህተት ድግግሞሽ 32.51 መሆኑን አሳይቷል:: ከቋንቋ አጠቃቀም ቀጥሎ ከፍተኛ የስህተት ቁጥር የተመዘገበው በቋንቋ አወቃቀር ስህተት ምድብ ውስጥ ነው:: ይህም ከአጠቃላይ 4558 ስህተቶች ውስጥ 662 የሚሆኑት ስህተቶች የተቆጠሩበት ነው:: ይህም በመቶኛ ሲሰላ 14.5%፣ አማካይ የስህተት መጠኑ 3.52 እንዲሁም ድግግሞሹ 5.88 መሆኑን አሳይቷል:: ሶስተኛውን ደረጃ የያዘው የስርዓተ-ነጥቦች አጠቃቀም ነው። ይህም አጠቃላይ ከተቆጠሩት 4558 ስህተቶች ውስጥ 213 ስህተቶች የተመዘገቡበት ነው። የዚህም ስህተት በመቶኛ ሲሰላ 4.7%፣ አማካይ የስህተት መጠኑ 1.13 እንዲሁም አማካይ የህተት ድግግሞሹ 1.89 መሆኑን አሳይቷል። አራተኛውና የመጨረሻው መለየት ያልተቻሉ በሚል ምድብ ውስጥ የተገኙ ስህተቶች ናቸው:: ይህም ከአጠቃላይ 4558 ስህተቶች ውስጥ 23 ያህሉ የተቆጠሩበት ምድብ ነው። ይህም በመቶኛ ሲሰላ 0.5%፣ አማካይ የስህተት መጠኑ 0.12 እንዲሁም አማካይ የህተት ድግግሞሹ 0.20%

መሆኑ የታየበት ምድብ ነው:: በአጠቃላይ ከተገኘው መረጃ መገንዘብ የሚቻለው ከፍተኛ የሆነው የስህተት ምዝግብ የታየው በቋንቋ አጠቃቀም ምድብ ውስጥ ሲሆን ሁለተኛውን፣ ሶስተኛውንና አራተኛውን የስህተት ብዛት ደረጃ የያዙት በቅደም ተከተል የቋንቋ አወቃቀር፣ የስርዓተ-ነጥቦች አጠቃቀምና መለየት ያልተቻሉ በሚሉ ስህተት ምድቦች ስር የታዩ ስህተቶች ናቸው::ከላይ የተገለጹትን የስህተት ዓይነት ምድቦች፤ በያንዳንዱ ድርሰት ውስጥ የተቆጠሩ፡- የስህተት ብዛት፤ በመቶኛ ሲሰላ፤ አማካይ የስህተት ብዛትና የስህተት ድግግሞሽ ጠቅለል ባለ መልኩ በሚከተለው ሰንጠረዥ ውስጥ ለማስቀመጥ ተሞክሯል::

ሰንጠረዥ ሶስት፡- የስህተት ዓይነት ምድቦች፤ በያንዳንዱ ድርሰት ውስጥ የተቆጠሩ፡- የስህተት ብዛት፤ በመቶኛ ሲሰላ፤ አማካይ የስህተት ብዛትና የስህተት ድግግሞሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ፡-

| የስህተት ዓይነት | ድርሰት አንድ | | | | ድርሰት ሁለት | | | | ድርሰት አንድና ሁለት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| የቋንቋ አጠቃቀም | 2150 | 83.04 | 22.87 | 39.68 | 1510 | 76.7 | 16.06 | 25.86 | 3660 | 80.3 | 19.5 | 32.6 |
| የቋንቋ አወቃቀር | 314 | 12.12 | 3.34 | 5.79 | 348 | 17.7 | 3.70 | 5.95 | 662 | 14.5 | 3.52 | 5.88 |
| የስርዓተ-ነጥቦች | 111 | 4.3 | 1.18 | 2.05 | 102 | 5.2 | 1.08 | 1.73 | 213 | 4.7 | 1.13 | 1.89 |
| ያልተለዩ | 14 | 0.54 | 0.15 | 0.26 | 9 | 0.4 | 0.09 | 0.14 | 23 | 0.5 | 0.12 | 0.20 |

መግለጫ:- በሰንጠረዡ ውስጥ (1) የሚገልጸው (የስህተት ብዛት) (2) የሚገልጸው (በመቶኛ ሲሰላ) (3) የሚገልጸው (አማካይ ስህተት) እና (4) የሚገልጸው (የስህተት ድግግሞሽ) ነው:: ከላይ በቋንቋ አጠቃቀም ስህተት ምድብ ስር የተጠቀሱትን ንዑሳን ስህተቶች በየርእሶቻቸው ስር ለአብነት በመጥቀስ እንደሚከተለው ለማቅረብ ጥረት ተደርጓል ::

### 4.1.3.1 የቋንቋ አጠቃቀም ችግር:-

ከመደበኛ አጻጻፍ ስርዓት ውጭ የሆነ የቋንቋ አጠቃቀም ሀሳብን በተፈለገ መልኩ ከማስተላለፍ የሚገታ መሆኑና በዚህም የተነሳ የመግባባትን ሂደት የሚያስተጓጉል መሆኑን በክለሳ ድርሳናት ርእስ ስር ለመዳሰስ ተሞክሯል:: በመሆኑም በጽህፍም ሆነ በንግግር ሀሳብን ለማስተላለፍ ወይም ለመግባባት መሰረታዊ የሆነውን የቋንቋ አጠቃቀምና የተግባቦቱን ሂደት በወጉ ማወቅ ተገቢ ነው::በዚህ አቢይ የስህተት ምድብ ውስጥ የተካተቱት ነዑሳን የስህተት ምድቦች:- የሆሄያት አጻጻፍ ችግሮች፣ የሳልስ ሆሄና የሳድስ ድምጾች ለይቶ ያለመጠቀም ወይም በመተካካት የመጠቀም ችግሮች፣ የተናባቢዎችና አናባቢዎች ጭመራና ግድፈት፣ አላስፈላጊ ድግግሞሽ ችግሮች፣ የቃላት ምርጫና በታላሚው ቋንቋ ውስጥ የስልጥኛ ቃላትን የማጠቀም ችግሮች ናቸው:: በምሆኑም በስልጥኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ በጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ከተቆጠሩት 3660 ከቋንቋ አጠቃቀም ስህተቶች ውስጥ:- የፊደላት ስርዓታዊ አደራደር ጠብቆ ያለማስፈር 2863፣ የሳልስና ሳድስ ፊደላት ለይቶ ያለመጠቀም 381፣ ተናባቢ ፊደላትንና አናባቢ ድምጾችን ቀያይሮና ተካክቶ /ጨምሮ ወይም ቀንሶ/ የመጠቀም ችግሮች 145፣ አላስፈላጊ ድግግሞሽ 126 እንዲሁም የቃላት ምርጫ 111 እና የአፍ-መፍቻ ቋንቋ ቃላት ጣልቃ መግባት ችግሮች 34 የሚሆኑ ስህተቶች የተፈጠሩና በቋንቋ አጠቃቀም ላይ ተጠኚ ተማሪዎች ምን እንደሚመስሉ የሚያሳይ መሆኑን ነው:: ተተኳሪ ተማሪዎች ከጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ከተፈፀመው 3660 ስህተቶች ውስጥ 2863 የሚሆኑት ስህተቶች በሆሄያት አጻጻፍ የተፈጠሩ ናቸው።

የዚህ ስህተት ብዛትም በመቶኛ ሲሰላ 78.2 ሲሆን አማካይ ስህተቱም 15.23 ነው:: የስህተት ድግግሞሹ ደግሞ 25.44 መሆኑን ጥናቱ አሳይቷል። ሁለተኛው ደረጃ የሚይዛው በሳልስና ሳድስ ንዑስ ምድብ ውስጥ የተፈጠሩ 381 ስህተቶች ናቸው:: በመቶኛ ሲሰላ 10.41 ሲሆን አማካይ ስህተቱም 2.03 ነው:: የስህተት ድግግሞሹ ደግሞ 3.4 መሆኑን ጥናቱ አሳይቷል። ሶስተኛውን ደረጃ የያዛው በጭመራና ግድፈት ንዑስ ምድብ ውስጥ የተፈጠሩ 145 ስህተቶች ናቸው:: በመቶኛ ሲሰላ 4.00 ሲሆን አማካይ ስህተቱም 0.8 ነው:: የስህተት ድግግሞሹ ደግሞ 1.33 ሆኗል። ከቃላት እስከ ዓረፍተ-ነገርራት ባሉ መዋቅሮች ውስጥ ተገቢ ያልሆኑ ሀሳቦችን መደጋገም ስህተት ስር የተቆጠሩት 126 ስህተቶች ናቸው:: የነዚህም ስህተት በመቶኛ ሲሰላ 3.44 ሲሆን አማካይ ስህተቱም 0.67ነው:: የስህተት ድግግሞሹ ደግሞ 1.10 ሆኗል። በመቀጠልም አምስተኛና ስድስተኛውን ደረጃ የያዙት የቃላት ምርጫና የአፍ-መፍቻ ቋንቋ ቃላት አጠቃቀም በሚሉ ንዑሳን ስህተት ምድቦች ውስጥ የተከሰቱ ስህተት ብዛት ናቸው:: እንደቅደም ተከተላቸውም:- የስህተት ብዛት111 እና 34 ሲሆን በመቶኛ ሲሰላ 3.03 እና 0.93 ሲሆን አማካይ ስህተቱም 0.6 እና 0.2 መሆናቸው ተደርሷል። የስህተት ድግግሞሻቸውም 1.00 እና 0.33 ሆኗል።

በአጠቃላይ በቋንቋ አጠቃቀም ስር የተቆጠሩ 3660 ስህተቶች ናቸው። የነዚህም ስህተቶች በመቶኛ ሲሰላ 100 ሲሆን አማካይ ስህተቱም 19.5 ነው:: የስህተት ድግግሞሹ ደግሞ 32.6 የሆነ መሆኑን መረዳት ተችሏል። ይህ ቁጥር የሚያሳየው ስህተት ወይም ግድፈት ያለባቸውን የሆሄያት ወይም የድምጾች መጠን ሳይሆን ስህተቱ ወይም ግድፈቱ የተገኙባቸውን ቃላት መጠን ነው። በመሆኑም በአንድ ቃላት ውስጥ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ የሆሄያት ወይም የድምጾች አጻጻፍ ችግሮች ሊገኙ እንደሚችሉ መገንዘብ ያስፈልጋል:: ከላይ በቋንቋ አጠቃቀም ስህተት ምድብ ስር የተጠቀሱትን ንዑሳን ስህተቶች ከጽሁፋዊ ገለጻ በተጨማሪ በሚከተለው መልኩ በሰንጠረዥ አራት ውስጥ ጠቅለል ባለ መልኩ ለማሳየት ተሞክሯል።

## ሰንጠረዥ አራት:- በቋንቋ አጠቃቀም ምድብ የተፈጸሙ ነዑሳን ስህተቶች መመዝገቢያ ቅጽ:-

| የስህተት ዓይነት | ድርሰት አንድ | | | | ድርሰት ሁለት | | | | ድርሰት አንድና ሁለት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የቋንቋ አጠቃቀ | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| የሆሄያት አጻጻ | 1682 | 78.23 | 17.9 | 31.06 | 1181 | 78.20 | 12.56 | 20.22 | 2863 | 78.2 | 15.23 | 25.44 |
| የሳልስና የሳድስ | 224 | 10.42 | 2.38 | 4.13 | 157 | 10.4 | 1.67 | 2.67 | 381 | 10.41 | 2.03 | 3.4 |
| ጭመራና ግድፈት | 145 | 3.95 | 0.9 | 1.56 | 60 | 4.00 | 0.64 | 1.03 | 145 | 4.00 | 0.8 | 1.33 |
| ድግግሞሽ | 74 | 3.44 | 0.79 | 1.37 | 52 | 3.44 | 0.55 | 0.90 | 126 | 3.44 | 0.67 | 1.10 |
| የቃላት ምርጫ | 65 | 3.02 | 0.69 | 1.2 | 46 | 3.05 | 0.49 | 0.79 | 111 | 3.03 | 0.6 | 1.00 |
| የስልጥኛ ቃላት | 20 | 0.93 | 0.21 | 0.36 | 14 | 0.92 | 0.15 | 0.24 | 34 | 0.93 | 0.2 | 0.33 |
| ድምር | 2150 | 100 | 22.87 | 39.68 | 1510 | 100 | 16.06 | 25.86 | 3660 | 100 | 19.5 | 32.6 |

መግለጫ:- በሰንጠረዡ ውስጥ (1) የሚገልጸው (የስህተት ብዛት) (2) የሚገልጸው (በመቶኛ ሲሰላ) (3) የሚገልጸው (አማካይ ስህተት) እና (4) የሚገልጸው (የስህተት ድግግሞሽ) ነው::

ከላይ በቋንቋ አጠቃቀም ስህተት ምድብ ስር የተጠቀሱትን ንዑሳን ስህተቶች በየርእሶቻቸው ስር ለአብነት በመጥቀስ እንደሚከተለው ለማቅረብ ጥረት ተደርጓል::

#### 4.1.3.1.1 በሆሄያት አጻጻፍ ችግር በቃላት ላይ የታዩ ስህተቶች

በሆሄያት አጻጻፍ ችግር ከተከሰቱ ስህተቶች ውስጥ የሚከተሉት ለአብነት ተጠቃሾች ናቸው::

1. በኮድ/A-36 በተጻፉ አረፍተ-ነገሮች ውስጥ በሆሄያት አጻጻፍ ችግር የተፈጠሩ ስህተቶች፣

| <u>ስህተት የሆኑት</u> | <u>ሲስተካከል</u> | <u>የአናባቢ ችግር</u> | <u>ሲስተካከል</u> |
|---|---|---|---|
| "ሰገረ" | => ሲጋራ | => ስኧግኧርኧ | => ስእግኣርኣ |
| "መጩስ" | => ማጨስ | => ምኧጭኤስ | => ምኣጭኧስ |
| "በጠም" | => በጣም | => ብኧጥኧም | => ብኧጥኣም |
| "መጠፎ" | => መጥፎ | => ምኧጥኧፍኦ | => ምኧጥፍኦ |
| "የሰንበ" | => የሳንባ | => ይኧስኧንብኧ | => ይኧስኣንብኣ |
| "በሽተን" | => በሽታን | => ብኧሽትኧን | => ብኧሽትኣን |
| "ያስከትለል" | => ያስከትላል | => ይኣስክኧትልኧል | => ይኣስክኧትልኣል |
| "እንድሁመ" | => እንዲሁም | => እንድእህኡምኧ | => እንድኢህኡም |

(አባሪ አንድ ኮድ/A-36 ይመልከቱ)

2. በኮድ/E-34 በተጻፉ አረፍተ-ነገሮች ውስጥ በሆሄያት አጻጻፍ ችግር የተፈጠሩ ስህተቶች፣

| <u>ስህተት የሆኑት</u> | <u>ሲስተካከል</u> | <u>የአናባቢ ችግር</u> | <u>ሲስተካከል</u> |
|---|---|---|---|
| "ጠቀሜተ" | => ጠቀሜታ | => ጥኧቅኧምኤትኧ | => ጥኧቅኧምኤትኣ |
| "ገሮ" | => ጓሮ | => ግኧርኦ | => ግኡ ወርኦ * |
| "ይጠቅመሉ" | => ይጠቅማሉ | => ይእጥኧቅምኧልኡ | => ይእጥኧቅምኣልኡ |
| "ስረ" | => ስራ | => ስእርኧ | => ስእርኣ |

(አባሪ ሁለት ኮድ/E-34 ይመልከቱ)

3. በኮድ/F-3 በተጻፉ አረፍተ-ነገሮች ውስጥ በሆሄያት አጻጻፍ ችግር የተፈጠሩ ስህተቶች፡-

| <u>ስህተት የሆኑት</u> | <u>ሲስተካከል</u> | <u>የአናባቢ ችግር</u> | <u>ሲስተካከል</u> |
|---|---|---|---|
| "ይለየየል" | => ይለያያል | => "ይእልኧይኧይኧል" | => ይእልኧይኣይኣል |
| "ይተጠበል" | => ይታጠባል | => "ይእትኧጥኧብኧል" | => ይእትኣጥኧብኣል |
| "ይከፈፈለሉ" | => ይከፋፈላሉ | => "ይእክኧፍኧፍኧልኧልኡ" | => ይእክኧፍኣፍኧልኣልኡ |
| "በመዘገጀት" | => በማዘጋጀት | => "ብኧምኧዝኧግኧጅኧት | => ብኧምኣዝኧግኣጅኧት |
| "በመምጣት" | => በማምጣት | => "ብኧምኧምጥኣት | => በኧምኣምጥኣት |

(አባሪ ሶስት ኮድ/F-3 ይመልከቱ)

በስልጥኛ ቋንቋ አፍ-ፈት የሆኑና በዚህ ጥናት የተተኮሩ ተማሪዎች በጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ በርካታ ስህተቶች ተስተውለዋል። እነዚህም ስህተቶች በቅድመ ግንዛቤ ስህተት ምድቦች ስር ተለይተው ተመዝግበዋል። ይህንንም ከላይ ባለው ሰንጠረዥ ውስጥ ለማሳየት ተሞክሯል። በቅድመ ግንዛቤ ስህተት ምድቦች ስር ከተመዘገቡት ስህተቶች ከፍተኛውን የስህተት ብዛት የያዘው ከቅድመ ግንዛቤ ስህተት ምድቦች አንዱ በሆነው የበቋንቋ አጠቃቀም ምድብ ነው።

የዚህን ምድብ ስህተቶች በስድስት ንዑሳን ስህተት ከፋፍሎ ለማሳየት ጥረት ተደርጓል። ከስድስቱም ስዑሳን ስህተት ክፍፍሎች አንዱ የሆሄያት አጻጻፍ /የሆሄያት ስርዓታዊ አደራደር ጠብቆ ባለማስፈር ችግር የተከሰቱ ስህተቶች/ ናቸው። ይህ ንዑስ ክፍል በቋንቋ አጠቃቀም ምድብ ስር ከተቆጠሩ 3660 ስህተቶች ውስጥ 2863 ስህተቶችን በመያዝ የመጀመሪያውን ደረጃ የያዘ ክፍል ነው።

በዚህ ክፍል ከተመደቡ ስህተቶች ውስጥም ከፍ ሲል በፌደል "1"፣ "2" እና "3" ስር የተጠቀሱት በተተኳሪ ተማሪዎች ከተጻፉ ድርሰቶች ለአብነት ያህል በማመሳከሪያነት የቀረቡ ናቸው። ከቀረቡት አስረጂዎች መገንዘብ የሚቻለው በተጠኚ ተማሪዎች በተጻፉ ድርሰቶች ውስጥ የቋንቋው ድምጾች የሚወክሏቸውን ሆሄያት በትክክል ለይቶ ያለመጻፍ ችግሮች በስፋት የተስተዋሉ መሆናቸውን ነው።

ከነዚህም ስህተቶች ውስጥ አብዛኛው ራብዕ ሆሄያትን በግዕዝ ሆሄያት ተክቶ በመጠቀም ችግር የተከሰቱ ስህተቶች ናቸው። ይህም በአፍ ዋሻ ውስጥ ምላስ በምታደርገው የላይ-ታች እና የፊት-ኋላ እንቅስቃሴ እንዲሁም ከከናፍር ክበትና ዝርገት ቅርጽ አንጻር የታች፣ የመካከልና ዝርግ የሆነውን አናባቢ (ኣ) ድምጽ ከላይ በተገለጸው በምላስ እንቅስቃሴና በከናፍር ቅርጽ አንጻር የመካከል፣ የመካከልና ዝርግ በሆነው (ኧ) ድምጽ ተክቶ መጠቀም ከላይ ለተጠቀሱ ለአብዛኞቹ ቃላት ስህተት እንዲሆኑ አስችሏቸዋል።

ለምሳሌ፡-

1. የሳንባ [ይኧስኣንብኣ] በማለት ፈንታ የሰንበ [ይኧስኧንብኧ] ብሎ መጻፍ። (ኮድ/A-36)

2. ይታጠባል [ይእትኣጥኧብኣል] በማለት ፈንታ ይተጠበል [ይእትኧጥኧብኧል] ብሎ መጻፍ። (ኮድ/F-03)

3. ይለያያል [ይእልኧይኣይኣል] በማለት ፈንታ ይለየየል [ይእልኧይኧይኧል] ብሎ መጻፍ። (ኮድ/F03)

እነዚህ ምሳሌዎች ባንድ ቃል ውስጥ ካንድ በላይ ግዕዝ ሆሄያትን በራብዕ ሆሄያት ተተክተው ከተጻፉ ቃላት ውስጥ ለአብነት የቀረቡ ናቸው። ይህ ስህተት ምንም እንኳን በተናባቢዎቹ ላይ የታየ ባይሆንም አንድ ቃል የሚፈለገውን ትርጉም እንዲሰጥ የሚዋቀሩ ሆሄያት

ተናባቢያቸው በተገቢው አናባቢዎች የተዋቀሩና በተገቢው ቦታ የተገኙ መሆን መቻል አለባቸው። ይህ ሳይሆን ቀርቶ አንድ ቃል ትርጉም እንዲሰጠን አድርገው ያዋቀሩትን ሆሄያት ባሉበት ሆነው ተዋቃሪ ድምጾቻቸውን እየቀያየሩ መጠቀም የቃሉን ትርጉም ከማዛባትና ትርጉም አልባ ከማድረግም በተጨማሪ የጽሁፉ መልዕክት የተድበሰበሰ እንዲሆን ያስችላል፡ ፡

ይህም በዚህ ጥናት በተተኮሩ ተማሪዎች በተጻፉ ድርሰቶች ውስጥ በስፋት የታዩ ስህተቶች ናቸው። ለነዚህም ስህተቶች የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ተጽዕኖ ሊሆን እንደሚችል ተገምቷል። ይህን ለማለት የሚያስችሉ ሁለት ተጨባጭ መነሻዎች አሉ። አንደኛውና የመጀመሪያው የስልጥኛ ቋንቋ አናባቢ ድምጾች ከአማርኛ (ከታላሚው) ቋንቋ አናባቢ ድምጾች በቁጥር የሚበልጡና ረጅምና አጭር ተብለው በሁለት የሚከፈሉ መሆን። በአማርኛ ቋንቋ ለራብዕ ፊደል በአናባቢነት የሚያገለግለው አናባቢ (ኣ) በስልጥኛ ቋንቋ አናባቢዎች ውስጥ የሌለ ነገር ግን /አአ/ ወይም /አ/ ቦታውን ተክቶ መግባት እንደሚችል የቋንቋው መዋቅር ይፈቅዳል። በዚው መሰረት በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ በአማርኛ ቃላት ውስጥ አናባቢን (ኣ) ሊወስድ በሚችለው ድምጽ ቦታ በስልጥኛው ቋንቋ ሊተከው የሚችለውን አናባቢ (አ) ወይም (አአ) አድርገው /ተክተው/ ይጠቀማሉ። ይህም እንደስህተት ታይቷል።የስልጥኛ ቋንቋ የሚጠቀማቸው ሁለቱም ዓይነት አናባቢዎች የሚከተሉት ናቸው።

ግዶር /ረጅም/ => "አአ"፣ "ኡኡ"፣ "ኢኢ"፣ "ኤኤ" እና "ኦኦ"

አንጭር /አጭር/ => "አ"፣ "ኡ"፣ "ኢ"፣ "ኤ"፣ "እ" እና "ኦ" በመሆኑም /ግዶር/ ተብለው የሚጠሩት ወይም በአማርኛ ትርጉም ረጅም የተባሉት ብዛታቸው አምስት ሲሆኑ /አንጭ/ ተብለው የሚጠሩት ወይም በአማርኛ ትርጉም አጭር የተባሉት አናባቢዎች ስድስት ብዛት አላቸው። በድምሩ አስራ አንድ አናባቢዎች እንደሆኑ መረዳት ይቻላል። ከነዚህም ውስጥ /አ/ እና /አአ/ የአማርኛውን አናባቢ /ኣ/ ተክተው የሚገቡ ናቸው። በተጨማሪም የሚከተለውን ከስልጥኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መጽሀፍ ከገጽ 25 የተወሰደውን እና ከ11-12ኛ ክፍል ተማሪዎች ለስልጥኛ ቋንቋ አጋዥ ከሆነው መጽሀፍ ገጽ 23 የተወሰዱ መረጃዎችን ይመልከቱ።

## ከስልጥኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መጽሀፍ ከገጽ 25 የተወሰደ



አትቃሬላሎ

የስልጥኛ አትቃሬላሎ ቦሽት ኢሳዶን። ኡሁንም አንፙር ዋ ግዶር አትቃሬላሎ በበሎትን። አንፙር አትቃሬላሎ ኢልነይማነይ ሰርፕ አፕኡፕኢፕኤፕእ ዋ ኦ ኒሙ። ግዶር አትቃሬላሎ ኢልነይማነይንገ

ሰር፦ አአፕኡኡፕኢኢፕኤኤ ዋ አኦ ኒሙ

ግዶር አትቃሬላሎ ኢትባሎነይ ሰር ሀድ ቀውል ቴግዶር ማእነ ያለይኮ ላቴሮት ኢድጋለልነቢያነ፦

ለባይትከ 1. ሙት = ምኡኡት
= ምኡት
2. በር = ብእር
ባር = ብአአር
3. ቦለት= ብኦኦልእት
4. ፌቅ = ፍኤኤቅ
5. ጎሮ = ግኦኦርኦ

ሙት እላነይ ቀውል አንጠረ ቴትቀረ ነብሳ የውጣ/ተቀበጥ በሎት ቴዮን ቴማዷርንገ "ኡኡ" ን በድጋለሎት "የጋር ኢድገለልቡያን" ሀነግነ ማነሚ አድጋለልነቢያን ሙት" እላነይ ማእነ ዪንዘን"

ለዷር ተጨቀመይ አስረድ አትቃሬለሎ ኡስጥ /ኡ/ዋ/ኦ/ ቴትዋለኩ ግርጬ ሊያትኬቦነኮ ኩቡቢ ተቀረላሎ ቴለይሙ ገናይንገ ሰረ ፍቼ በባሎት ኢጠፋይማን። ተኩቡቢዋ ታፍ የግርጬ ቆረ በድባየ አትቃሬላሎ አረመት ብታሺያቴ ጎት በሎት ዋ ሀርክ በሎት የነተ ኢትላሎን። ቴታይ አረመት ትረከብያቴ የጎትት ዋ ዩርክት መቃም መንቴ ባሶት አትቃሬላሎ የዷርፕ የጉት ዋ የታት አትቃሬላሎ በበሎት ኢቾሎን። ቢታይ ሺሽት ጎሊጋነ ኡስጥ ኢትረከቦነይ አትቃሬላሎም ኢትኬተሎነኒ ሰር።

- የዷር ፦ ኢፕኡፕኢኢፕኡኡእ
- የጉት፦ ኤፕአፕአፕኤኤፕኦኦ
- የታት፦ አአ/አ)

25

ስልጢኛ 12ኛ ክፍል    አቀርቡያን

## ለስልጥኛ ቋንቋ አጋዥ ከሆነው መጽሀፍ ገጽ 23 የተወሰደ



በስልጥኘ ያሉይአትረከቦነይ አትቃሪሎ ጠምባቦ፡-

[አ፣ ኡ፣ ኢ፣ ኤ፣ እ፣ ኦ] ዋ

[አአ፣ ኡኡ፣ ኢኢ፣ ኤኤ፣ ኦኦ]

አትቃሪሎ ሁልምኒሙ የአፍዋ ኑጡቂኒሙ፡፡ የአፍኒሙ የባሉይሙይ መሰከ ቲጠሩይሙ ተሳምበ እንቃነይ አየር ባፍ አሽ ሊዮጫነንከ፡፡

"የስልጥኘ አትቃሪላሎ አስረድ ቲዮኑ ኡሁኑም አንጭርዋ ጉደር በበሎት ቦሽት እሳዶን፡፡

1.አንጭርቻይ አትቃሪላሎ፡- [አ]፣[ኡ]፣[ኢ]፣[ኤ]፣ [እ]፣[ኦ]

2.ጉደርቻይ አትቃሪላሎ፡- [ [ አ]፣ [አአ]]፣ [ኡኡ]፣ [ኢኢ]፣[ኤኤ]፣ [ኦኦ]፣

ሂታይ አስረድ የስልጥኘ አትቃሪሎ ጠምባቦ በትቅላቀላት መሰ በሼሽት እሳዶን፡፡ ኡሁኑም፡-

ሀ. የቀደ(ኡፍትሉፍተኘ)፡- [ኢ]፣[ኢኢ]፣[ኤ][ኤኤ]

ለ. ጉተኘ(ልከኘ)፡- [አ]፣ [ [ አ]፣ [አአ]]፣[ እ]

መ. ሬርቾኘ(የሬር)፡- [ኡ]፣ [ኡኡ]፣[ኦ]፣ [ኦኦ]

ቢትቅላቀላነይ ያረመት ቃም እትረከቢያነይ ኤተ መሰ ባሶት አኩም አትቃሪሎ ጠምባቦ **በሼሽት** እሳዶን፡፡

ሀ. ጎትተኘ(ደረኘ)፡- [ ኢ]፣ [ኢኢ]]፣[ አ]፣[ኡ]፣ [ኡኡ]

ለ. ልከኘ ፡- [ኤ]፣ [ኤኤ]፣[አ]፣ [ኦ]፣ [ኦኦ]፣

መ. እርከተኘ(ታተኘ)፡- [ [ አ]፣ [አአ]]

**ለሰቤ** በከዲራ አብዱልፈተ ተሰናደ

23

ተናባቢዎቹም ቢሆኑ ከአማርኛ ቋንቋ ተናባቢዎች አንጻር: - "ኽ"፣ "ጽ"፣ "ዕ"፣ "ህ"፣ "ጎ"፣ እና "ዲቃላ" ወይም ባለ ሁለት ተናባቢ የሆኑ (ኋ፣ቧ፣ሟ...) የተሰኙትን ጨምሮ በስልጥኛ ቋንቋ ውስጥ ግድፍ የሆኑ መሆናቸው ከፍ ሲል ለተጠቀሙ ስህተቶች አቢይ ምክንያቶች

ሊሆኑ የሚችሉ ጉዳዮች ናቸው። ለዚህም ነው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ ሊሆን ይችላል የሚል ግምት የተሰጠው።

በተጨማሪም የሚከተለውን ከስልጥኛ ቋንቋ ማስተማሪያ መጽሀፍ ከገጽ 8 የተወሰደውን የተናባቢ ድምጾች ከመፈጠሪያ ቦታቸውና ከሚፈጠሩበት ባህሪይ አንጻር የሚያሳየውን መረጃ ይመልከቱ።



ማቴክሼ

ተቀረላሉ እትለቅቡያን ኤትዋ ሃለት

| እትራቅቡያን ሃለት | | እትለቅቡያን ኤት | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ግልጨ | እስን ግርጨ | ደንደነ | ደንደነ እንተ | እንተ | እንቅረ | ኑኬ |
| ኡፉር | ንጡቁ | ብ | | ድ | | | ግ | ቋ |
| | አይነጥቆ | ፕ | | ት | | | ክ | ቦ |
| | ጠምቢ | ጵ | | ጥ | | | ቐ | |
| ፉኪት | ንጡቁ | | | ዝ | | | | ኽ |
| | አይነጥቆ | | ፍ | ስ | ሽ | | | ሀ |
| | ጠምቢ | | | ፀ | ዥ | | | |
| ኡፉር ፉኪት | ንጡቁ | | | | ጅ | | | |
| | አይነጥቆ | | | | ች | | | |
| | ጠምቢ | | | | ጭ | | | |
| ከንኑናኚ | | ም | | ን | | ኝ | | |
| ሚጠተኚ | | | | ል ር | | | | |
| ደረት እትቃረሎ | | ው | | | | ይ | | |

ስልጢኛ 12ኛ ጎልጌ 8 አቀርቡያን

በሌላ መልኩ በታችኛው ትምህርት ዕርከን ተገቢውን የደረጃ ብቃት ይዘው ያለመምጣት ችግር የተስተዋለ ሲሆን ለዚህም ምንጩ ብቁ የመማር ማስተማር ሂደት አለመኖር እንደሆነ አመላካች መሆኑን ነው።

በተማሪዎቹ ድርሰትቶች ውስጥ የተፈጠሩት ችግሮች ተማሪዎች ሊያስተላልፉ የፈለጉትን መልዕክት በትክክል ለአንባቢያን ለማድረስ እክል የሚፈጥሩ ከመሆናቸውም ባሻገር የተግባቦት ሂደቱም የተዛባ እንዲሆን ከማድረግ አንጻር ሰፊ ዕድል ያላቸው ናቸው።

#### 4.1.3.1.2 ሳልስና ሳድስ ለይቶ ባለመጠቀም ችግር በቃላት ላይ የታዩ ስህተቶች፡-

1. በኮድ/A-43 የተጻፉ የሳልስና የሳድስ ለይቶ ባለመጠቀም የተፈጠሩ ስህተቶች፡-

| ስህተት የሆኑት | ሲስተካከል | የአናባቢ ችግር | ሲስተካከል |
|---|---|---|---|
| "ሚክናቱ" | => ምክንያቱም | => ምኢክንኣተኡ | => ምእክንእይኣትኡም |
| "አስፋለግ" | => አስፈላጊ | => ኧስፍኣልኧግእ | => ኧስፍኧልኣግኢ |
| "ያሲፋልገናል" | => ያስፈልገናል | => ይኣስኢፍኣልግኧንኣል | => ይኣስእፍኧልግኧንኣል |
| "ስላዝ" | => ስለዚህ | => ስእልኣዝእ | => ስእልኧዝኢህ |
| "የምችለው" | => የሚችለው | => ይኧምእችልኧው | => ይኧምኢችልኧው |
| "ስመር" | => ሲማር | => ሰእምኧር | => ሰኢምኣር |
| "የሚለው" | => የምለሁ | => ይኧምኢልኧውኡ | => ይኧምእልኧህኡ |
| "የምለው" | => የሚለው | => "ይኧምእለኧው" | => ይኧምኢለኧው |

(አባሪ አራት ኮድ/A-43 ይመልከቱ)

2. በኮድ/B-48 የተጻፉ የሳልስና የሳድስ ለይቶ ባለመጠቀም የተፈጠሩ ስህተቶች፡-

| ስህተት የሆኑት | ሲስተካከል | የአናባቢ ችግር | ሲስተካከል |
|---|---|---|---|
| "ኢና" | => እና | => ኢንኣ | => እንኣ |
| "ሚክኒየቱ" | => ምክንያቱ | => ምኢክንኢይኧትኡ | => ምእክንእይኣትኡ |
| "ሲለዝ" | => ስለዚህ | => ስኢልኧዝእ | => ስእልኧዝኢህ |
| "ኢኛም" | => እኛም | => ኢኝኣም | => እኝኣም |
| "ቢሆን" | => ብንሆን | => ብኢህኦን | => ብእንህኦን |
| "ቢኒመር" | => ብንማር | => ብኢንኢምኧር | => ብእንእምኣር |
| "ትሚርት" | => ትምህርት | => ትእምኢሀርት | => ትእምእህእርት |

(አባሪ አምስት ኮድ/B-48 ይመልከቱ)

3. በኮድ/F-45 የተጻፉ የሳልስና የሳድስ ለይቶ ባለመጠቀም የተፈጠሩ ስህተቶች፡-

| ስህተት የሆኑት | ሲስተካከል | የአናባቢ ችግር | ሲስተካከል |
|---|---|---|---|
| "ቢዙ" | => ብዙ | => ብኢዝኡ | => ብእዝኡ |
| "ኢነሱም" | => እነሱም | => ኢንኧስኡም | => እንኧስኡም |
| "በሺተ" | => በሽታ | => ብኧሽኢትኧ | => ብኧሽእትኣ |
| "ሲለዝ" | => ስለዚህ | => ስኢልኧዝእ | => ስእልኧዝኢህ |

"የምየስቸግር" => የሚያስቸግር => የኧምእይኧስችኧግር => የኧምኢ.ይኣስችኧግር

"ሲለሆና" => ስለሆነ => ስኢ.ልኧህኦንኣ => ስእልኧህኦንኧ

(አባሪ ስድስት ኮድ/F-45 ይመልከቱ)

በስልጥኛ ቋንቋ አፍ-ፈት የሆኑና በዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሳልስና የሳድስ ሆሄያት አጠቃቀም ችግር በስፋት እንዳለባቸው ተመልክቷል።

ከላይ ከተራ ቁጥር "1" እስከ "3" ድረስ ባሉ ኮዶች ተዘርዝረው የተቀመጡት ቃላት በተጠኚ ተማሪዎች ከተጻፉ ድርሰቶች መካከል ለአብነት በተወሰዱ ድርሰቶች ውስጥ የተገኙ የሳልስና የሳድስ ሆሄያት ችግር ያለባቸው ቃላት ናቸው:: በቀረቡት ቃላት ውስጥ እንደተስተዋለው ተጠኚ ተማሪዎቹ በጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ በሳድሱ ቦታ ሳልሱን፤ አልፎ አልፎም በሳልሱ ቦታ ሳድሱን እያፈራረቁ የሚጠቀሙ ስለመሆናቸው ነው።

ከላይ በተጠቀሱት ቃላት ከተገነቡ አረፍተ-ነገሮች ውስጥ ለአብነት የሚሆኑትን ከዚህ በታች በማቅረብ ስህተታቸው ተስተካክሎ ሲጻፍ ምን መሆን እንዳለበት ለማሳየት ተሞክሯል። በዚህም መሰረት በተማሪ ኮድ/A-43፣ B-48 እና F-45 ከተጻፉ ድርሰቶች ውስጥ የሚከተሉት አረፍተ-ነገሮች ተመርጠዋል።

1. በኮድ/A-43 የተጻፉ የሳልስና የሳድስ ለይቶ ባለመጠቀም የተፈጠሩ ስህተቶች፡-

1. "... **ሚክናቱ** የሀገረ ሰው ከልተመረ ሀገር መሰደግ አይችልም..." ይህ አረፍተ-ነገር ተስተካክሎ ሲጻፍ "... **ምክንያቱም** ሰው ካልተማረ ሀገሩን ሊያሳድግ አይችልም። ..."

2. "... አንድ ሰው የሆነ ነገር ለማፍጠር ትምርት ያስፈልገናል **ስለዝ** ሀገር ለድግ **የምችለው** ስመር ነው..." ይህ አረፍተ-ነገር ሲቃና፡- "... አንድ ሰው አንድን ነገር ለመፍጠር ትምህርት ያስፈልገዋል። **ስለዚህ** አንድ ሀገር ሊያድግ **የሚችለው** ትምህርት ሲኖር ነው።..."

3. "... አሁን እኔ **የሚለው** ሰዎች የተመረ ዬት ደረሰ **የምለው** አበበል ህቅር ኢ.ለላው። ..." የተስተካከለ ሲሆን፡- "... አሁን እኔ **የምለሁ** አንዳንድ ሰዎች 'የተማረ ሰው የት ደረሰ **የሚለው**' የሚሉት አባባል ይቅር ባይ ነኝ። " በሚል ቢስተካከል የተሻለ ሀሳብ ይገልጻል።

2. በኮድ/B-48 የተጻፉ የሳልስና የሳድስ ለይቶ ባለመጠቀም የተፈጠሩ ስህተቶች፡-

1. "... የተማረና ያልተማረ ሰው እኩል አደለም **ሚክኒየቱ** የተመረ ሰው የልተማረ ሰው የዘል፡ ፡ **ሲለዝ** መመር ይሸለል።... "

ሲስተካከል፡- "... የተማረና ያልተማረ ሰው ዕኩል አይደለም። **ምክንያቱም** የተማረ ሰው ያልተማረን ሰው ያዛል። **ስለዚህ** መማር ለሁሉም ነገር የተሻለ ነው።..."

2. "... **ኢኛም ቢሆን ትሚርት** ጥቅም አሁቀን **ቢኒመር** ጡሩ ነው። ..." ይህን ሀሳብ "... **እኛም ብንሆን** የትምህርትን ጥቅም አውቀን **ብንማር ጥሩ** ነው። ..."

3. በኮድ/F-45 የተጻፉ የሳልስና የሳድስ ለይቶ ባለመጠቀም የተፈጠሩ ስህተቶች፡-

1. "... **ኢነሱም** የሰባ **በሺተ**፣ የጉባት **በሺተ**፣ ..." "**እነሱም** የሳንባ **በሽታ**፣ የጉበት **በሽታ**፣ ..." በሚል

ሀሳብ አገላለጽ ቢሻሻል ይመረጣል።

ከላይ በተማሪ ኮድ/A-43፣ በተማሪ ኮድ/B-48 እና በተማሪ ኮድ/F-45 ከተጻፉ ድርሰቶች ውስጥ ለአብነት ከቀረቡ አረፍተ-ነገሮች ውስጥ የተፈጠሩትን ስህተቶች ለማየት ብንሞክር፡- በኮድ/A-43 በመጀመሪያ አረፍተ_ነገር ውስጥ "**ሚክናቱ**"፣ በሁለተኛው "**ስለዝ**" እና "**የምችለው**"

እንዲሁም በሶስተኛው አረፍተ-ነገር ውስጥ "**የሚለው**" እና "**የምለው**" የሚሉት ቃላት እንደ ቅደም ተከተላቸው "**ምክንያቱም**፣ **ስልዚህ**፣ **የሚችለው**፣ **የምለሁ** እና **የሚለው**" ለማለት የተፈለጉ ቃላት ናቸው።

በኮድ/B-48 በመጀመሪያ አረፍተ_ነገር ውስጥ "**ሚክኒየቱ** እና **ሲለዝ**" በቅደም ተከተላቸው "**ምክንያቱም**" እና "**ስለዚህ**" በሁለተኛው አረፍተ-ነገር ውስጥ ደግሞ "**ኢኛም**፣ **ቢሆን**፣ **ትሚርት** እና **ቢኒመር**" የተሰኙ ቃላት እንደቅደም ተከተላቸው "**እኛም**፣ **ብንሆን**፣ **ትምህርት** እና **ብንማር**" ለማለት የተፈለጉ ቃላት ናቸው። እንዲሁም በኮድ/F-45 "**ኢነሱም**" እና "**በሺተ**" የተሰኙ ቃላት እንደቅደም ተከተላቸው "**እነሱም**" እና "**በሽታ**" የተሰኙ ቃላትን ለመጻፍ ተፈልጎ ሳይሳኩ የቀሩ ናቸው።

በአጠቃላይ ቃላቱ ለማለት የፈለጉትን ሳይሉ መቅረታቸው ብቻ ሳይሆን የመደብ፣ የቁጥር፣ የባለቤትና የተሳቢ አልመጣጣም ችግሮች እንዲፈጠሩ ምክንያት ሊሆኑ የቻሉ ቃላት ስለመሆናቸው ለማወቅ ተችሏል። በመሆኑም በነዚህና በመሳሰሉት ስህተቶች የተነሳ በስልጥኛ ቋንቋ አፍ-ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ በጻፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ስህተቶች ተፈጥረዋል። የስህተቶቻቸው መንሴዔያቸው በአብዛኛው በሳድስ ቦታ ሳልስ በመጠቀም እንዲሁም አልፎ አልፎ በሳልስ ቦታ ሳድስን እያፈራረቁ በመጠቀማቸው የተነሳ የተፈጠሩ ስህተቶች ናቸው።

ለነዚህ ስህተቶች ምንጮቻቸው በአመዛኙ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ቢሆንም የመምህራን አስተምሮት ድክመትም የታከለበት እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል።

4.1.3.1.3 **በጭመራ፣ በግድፈትና በቅየራ ችግር በቃላት ላይ የታዩ ስህተቶች፡-**

በጭመራ፣ በግድፈትና በቅየራ ችግር የተፈጠሩ ስህተቶች ሲባል ፊደላትን ወይም ድምጾችን በአንድ ቃል ውስጥ ሳያስፈልግ መጨመር፣ አስፈላጊውን መግደፍና አንዱን በአንዱ ቀያይሮና ተካክቶ በመጠቀም ችግሮች የሚፈጠሩ ስህተቶች እንደሆኑ መገንዘብ ያስፈልጋል፡

፡

ለዚህም በተለያዩ ተጠኚ ተማሪዎች ከተጻፉ ድርሰቶች ውስጥ ከተገኙ የጭመራ፣ የግድፈትና የቅየራ ስህተቶች መካከል ለአብነት የሚሆኑትን እንደሚከተለው ለማሳየት ጥረት ተደርጓል፡ ፡

<u>ስህተት የሆኑት</u>  <u>ሲስተካከል</u>  <u>ጭመራ</u>  <u>ግድፈት</u>  <u>ምንጭ</u>

ገሮ "ግኧርኦ" => ግኡውኣርኦ => => ውኣ* አባሪ-2/ኮድ/E-34

ሂየዘል "ህኢይኧዝኧል" => ይእይኣዝኣል => "ህ" => ይ አባሪ-6/ኮድ/F-45

ሲለዝ "ስኢልኧዝ" => ስእልኧዝኢህ => "ኢ" => ህ አባሪ-5/ኮድ/B-48

የሚለው "ይኧምኢልኧው" => ይኧምምእለኧህኡ => "ው" => ህ አባሪ-4/ኮድ/A-43

የለበትም "ይኧልኧብኧትም" => ይኧልኧብንእም => "አ፣ት" =>ን አባሪ-6/ኮድ/F-45

ቢሆን "ቢኢህኦን" => ብእንሆኦን => "ኢ" => ን አባሪ-5/ኮድ/B-48

ትሚርት "ትእምኢርት" => ትእምህርት => "ኢ" => ህ አባሪ-5/ኮድ/B-48

ሚክኒየቱ "ምኢክንኢይኧትኡ" => ምእክንእይኣትኡም => "ኢ፣ኧ" => ም አባሪ-5/ኮድ/B-48

ከዘ "ክኧዝኧ" => ክኧዝኢይኣ => __ => ይ አባሪ-7/ኮድ/C-03

ተቆይቶ "ትኧቅኦይትኦ" => ቅኦይትኦ => "ት፣ኧ" => ---- አባሪ-7/ኮድ/C-03

ያረግሃል "ይኣርኧግህኧል" => ይኣድኧርግኧህኧል => "ኧ" => ድ አባሪ-8/ኮድ/D-52

ያነሰውት "ይኣንኧስኧውኡት" => ይኣንኧስኧህኡት => "ው" => ህ አባሪ-8/ኮድ/D-52

ከላይ በቀረቡት ቃላት ውስጥ የታዩት ስህተቶች በሶስት መልኩ የሚታዩ ናቸው። አንደኛው የሆሂያት ጭመራ ሁለተኛው የሆሂያት ቅነሳ /ግድፈት/ እና ሶስተኛው ቅየራ/መተካት/ ናቸው። የመጀመሪያው በቃሉ ውስጥ ሊካተት የማይገባውን ሆሄ የቃሉ ተዋቃሪ ማድረግ ወይም ጭመራ ነው። ለምሳሌ፡- በአባሪ 6 እና 7 "የለበትም" እና "ተቆይቶ" በተሰኙ ቃላት ውስጥ የሚገኙ ሆሂያት ሲሆኑ "የለበ**ት**ም" በሚለው ቃል ውስጥ "ት" ጭመራ "ን" ቅነሳ ተደርጎበታል። ቃሉ መሆን የነበረበት "የለብ**ን**ም" ነበር። ይህ ባለመሆኑም ቃሉ እንደገባበት ቦታ የመደብ አለመስማማትን ችግር ፈጥሯል። ሌላው "**ተቆይቶ**" በሚለው ቃል ውስጥ ቅድመ-ቅጥያ ሆና የገባችዋ "**ተ**" ለቃሉ አላስፈላጊ ሆሄ ሆኖ ታይቷል። ለዚህ ቃል ስህተት መነሻ የሆነው የአማርኛ ቋንቋ ከተደራጊ ግሶች ህግ የመጣ ጠቅላይ ፍረጃ ስህተት ነው።

ሁለተኛው በቃላት ውስጥ የሆሄያት ቅነሳ /ግድፈት/ ነው። ይህ ስህተት የተፈጠርባቸው ቃላት በአባሪ 5 "**ትሚርት**" እና "**ቢሆን**"፣ በአባሪ-4 "**ሚክኒየቱ**" እና በአባሪ-8 "**ያረግሃል**" ሲሆኑ በቃላቱ ውስጥ የተጎረዱት ፡- "ህ"፣ "ን"፣ "ም" እና "ድ" ሲሆኑ የ"ህ" መጎረድ "ትምህርት" የሚል የነበረውን "**ትምርት**"፣ የ"ን" መጎረድ "ብንሆን" ይል የነበረውን "**ቢሆን**"፣ የ"ም" መጎረድ "ምክንያቱም" መሆን የነበረበትን "**ምክንያቱ**" እና የ"ድ" መጎረድ "ያደርገሃል" መባል የነበረበትን "**ያረግሃል**" ወደሚሉት ትርጉም አልባና በአረፍተ-ነገሮቹ ውስጥም የባለቤትና የመደብ መዋቅራዊ ችግሮች እንዲፈጠሩ ምክንያት ሆነዋል። ሌላኛው ከቅየራ አንጻር ሲሆን አንድን ሆሄ በሌላ ሆሄ በመተካት የተፈጠሩ ስህተቶች ናቸው። በዚህ መልኩ ለተፈጠሩ ስህተቶች ምክንያት ከሆኑት ውስጥ የሚከተሉት ለአብነት ተጠቃሾች ናቸው።

በአባሪ 6 እና 8 ድርሰት ውስጥ በተጠቀሱ "**ሂየዘል**" እና "**ያነሰውት**" በሚሉት ቃላት ውስጥ የሚገኙት ሆሄያት ሲሆኑ በ"ሂየዘል" በቃሉ ውስጥ ያለው መነሻ ሆሄ "**ሂ**"ተገቢ ባልሆነ መልኩ "**ይ**"ን ተክቶ የገባ ነው። ሌላው ተኪ ሆኖ የገባው ሆሄ በ"**ያነሰውት**" በሚለው ቃል ውስጥ ያለው "ው" ሲሆን ይህ ሆሄም "ህ"ን ተክቶ የገባ ነው። የነዚህ ሆሄያት ሌሎችን ተክተው የገቡበት መንገድ ተገቢ አለመሆን ብቻ ሳይሆን በተተኳሪ ቋንቋ ውስጥ ትርጉም የነበራቸውን ቃላት ወደ ትርጉም አልባነት የወሰደ ስህተት የፈጠሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ ተችሏል።

በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱት የሆሄያት /የድምጻች/ ጭመራ፣ ግድፈትና ቅየራ ችግሮች በተተኳሪ ተማሪዎች በተጻፉት ድርሰቶች ውስጥ እንደአንዱ ስህተት ዓይነት ሆነው ተቆጥረዋል። ይህም ተተኳሪ ተማሪዎቹ የተተኳሪውን ቋንቋ ሆሄያትን ድምጽ ወኪል ለይተው ባለምወቃቸው ምክንያት በቦታው ሌሎች ሆሄያትን ትክተው የመጻፍ ሁኔታ በሰፊው ታይቷል። ይህ የሚያሳየው ተማሪዎቹ በታችኛው ትምህርት ደረጃ ላይ መለየት የነበረባቸውን የሆሄያት ቅርጽ አጣጣል ለይተው አለመምጣታቸውን ነው። ለዚህም ምንጩ በመማር ማስተማር ሂደት ላይ የሚኖሩ የአተገባበር ድክመቶች እንደሆኑ ለመገመት ተቸሏል።

### 4.1.3.1.4 በድግግሞሽ ችግር የተነሳ የታዩ ስህተቶች

የድግግሞሽን ትርጉም ከድርሰት ውስጥ ስህተት አንጻር እንጂ ከአስፈላጊነቱ መደጋገም አንጻር አልተቃኘም:: በዚህም መሰረት በድርሰት ውስጥ አንድ ዓይነት ቃላት፣ ሀረጋትና ዓረፍተ-ነገራት ለአንድ ዓይነት ትርጉም ከሁለትና ከዚያ በላይ መጠቀም ከድርሰት አጻጻፍ ስህተቶች ውስጥ አላስፈላጊ ድግግሞሽ በሚል ተይዟል:: በሌላ መልኩ በንግግር አሊያም በጽሁፍ ሂደት ስለምንገልጸው ጉዳይ አጽንዖት ለመስጠት ስንል ተገቢ የሆነ ድግግሞሽ ልንጠቀም እንችላለን::

በዚህ ጥናታዊ ጽሁፍ ውስጥ ግን አላስፈላጊ ድግግሞሽ የአንድን ጽሁፍ ተገቢነት ከመቀነስና

ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት ከማደብዘዝ አንጻር በስህተትነት ተቃኝቷል:: በዚህም መሰረት በተጠኚ ተማሪዎች በተጻፉ ድርሰቶች ውስጥ የታዩ አላስፈላጊ ድግግሞሾች ሊሆኑ ከቻሉት ውስጥ የሚከተሉትን ለአብነት ለመጥቀስ ተሞክሯል::

1. "... ስገረ የሰንበ በሽተን **ያስከትለል** እንዲሁመ የእከኖሚ ጉዳትን **ያስከትለል**::" (አባሪ አንድ ኮድ/A-

36) ይመልከቱ።

2. "... እንሰት **ጠቀሜታው** የጎላ ነው ...እንሰት **ጥቅሙ** ለእንስሳትም እንድምግብነት **የሚጠቅም**

ነው እንድሁም ለሰው ልጅ **የሚጠቅሙ** ናቸው የእንሰት **ጥቅሞች** አንዱ ፍነንቾ እና አተካና፣ ሀሙቾ፣ ... ለገመድ እና ልጅቢሳም ስረ **ይጠቅመሉ**::" (አባሪ ሁለት ኮድ/E-34) ይመልከቱ።
።

3. " ... መልከምነቱ **እጅጉን** ዘርፍ ብዙ ጥቅሞችና ፀገዎች አሉት ... **እጅጉን** ጥሩ መልከምነድ'ነዬ...

**እሱዋ** መልከምናት አውርቹም ባልጨርሰውም ... **እሰዋ ማልከምናት አውርቹም በልጨርሰው** ለምሰሌው ያክል ነው" (አባሪ ስምንት ኮድ/D-52) ይመልከቱ።

4. "...ከዘ ቡሀላ ይፈተፈተል ከዘ ቡሀላ በትልቅ ሲሀን ይገበል እሰት ይቀጠጠላል ከዘ ቡሀላ መድጀ...

ከዘ ቡሀላ ቡለው በምጠድ ለይ **ይገበል** ከዘ ቡሀላ ይቆለል... በትልቅ ሰሀን **ይገበል** ትንሽ ቆይቶ ውሀ **ይገበል** ... አይቤ **ይገበል**... ቅቤ **ይገበል** ከዘ ቡሀለ ምጥምጠ **ይገበል**..." (አባሪ ሰባት ኮድ/C-3) ይመልከቱ።

በነዚህ በአራት ነጥብ ባልተቋጨ አረፍተ-ነገሮች ውስጥ ባንድ ቅርጽ ያለው አንድ ቃል ባላስፈላጊ ሁኔታ የተደጋገመውን ስህተት ማረም ቢያስፈልግ የተጠቀሱትን ሀሳቦች በቅደም ተከተል በማስቀመጥ በመጨረሻኛው "ይገባል" በሚል ግስ /ማሰሪያ አንቀጽ/ ብቻ በመጠቀም መቋጨት ይቻላል። "... **ከዝየም** ሰው መጥቶ አወጠኝ'ኝ። ... **ከዝየም** እነቴ እያለቀሰች መጠችነ አቅፈ'ኝ ወስድችኝ...**ከዝየ** አበቴመ መጥቶ ወደ ቤት...ትምህርት ቤቱ በጣም ይርቅ **ነበር**... መንገድ ለይ እየተቀመጥኩ'ኝ እሄድ **ነበር** ... ልጆች ትተውኝ ስሄዱ አለቅስ ነበር... አብዘኘው ትልቅ ሆኖ ስለምገበ **አብዘኘው** ትልልቅ ነበር" (አባሪ ዘጠኝ/ኮድ C-47) ይመልከቱ።

ከላይ ከቀረቡት ምሳሌዎች እንደምንረዳው በተጠኚ ተማሪዎች በተጻፉ ድርሰቶች ውስጥ በተለያየ መልኩ የቋንቋ አጠቃቀም ችግሮች ተከስተዋል። በዚህ በቋንቋ አጠቃቀም ሂደት ከተከሰቱ ስህተቶች አንዱ በአላስፈላጊ ድግግሞሽ የተከሰቱ ናቸው። እነዚህም ስህተቶች ከቃላት እስከ ዓረፍተ-ነገር ድረስ ባሉ መዋቅሮች ደረጃ የተከሰቱ ስለመሆናቸው ከላይ

በተጠኚ ተማሪዎች ከተጻፉ ድርሰቶች ውስጥ ለአብነት ከቀረቡ ድግግሞሾች መገንዘብ ይቻላል።

ከነዚህም ውስጥ የተወሰኑትን በመውሰድ እንደሚከተለው ማብራሪያ ለመስጠት ተሞክሯል። በቁጥር "1" የተጠቀሰው "...ስገረ የሰንበ በሽተን **ያስከትለል** እንዲሁመ የእከኖሚ ጉዳትን **ያስከትለል**:: " የሚል ሀሳብ ተገልጾበታል። በዚህ ሀሳብ አገላለጽ ውስጥ በሽታን ከሚለው ቃል ቀጥሎ ያልው "ያስከትላል" የሚለው ቃል ተገቢ ባልሆነ መንገድ የተደገመና ያለ ቦታው የገባ ቃል ነው። የጽሁፉን ተገቢነትንና የሀሳብ መድበስበስን ያስከተለው የቃሉ አላስፈላጊ ድግግሞሽ ብቻ ሳይሆን የሌሎች ተዋቃሪዎች ሰዋሰዋዊ ህተቶችም ጭምር ነው።

ተስተካክሎ ይጻፍ ቢባል "...ሲጋራ ማጨስ የሳንባ በሽተን እንዲሁም የኢኮኖሚ ጉዳት ያስከትላል::" በሚል ቢስተካከል የጽሁፍ ተገቢነት ይኖረዋል። የመልዕክት ፍሰቱም ጤናማ ይሆናል።በቁጥር "2" በተጠቀሰው በተገቢው ስርዓት-ነጥቦች ባልተቋጩ አራት ዓረፍተ-ነገሮች ውስጥ ከአንድ የቃል ክፍል የወጡ ስድስት ቃላት ያለ አራት ነጥብ መቋጫ ተደጋግመው ግብተዋል። እነሱም:- **ጠቀሜታው፣ ጥቅሙ ፣ የሚጠቅም፣ የሚጠቅሙ፣ ጥቅሞች እና ይጠቅመሉ**:: የተሰኙ ናቸው። ከነዚህ ውስጥ ከመጨረሻው "ይጠቅመሉ" ከሚለው ቃል በስተቀር አምስቱ ቃላት አላስፈላጊ ድግግሞሽ ናቸው። በአራት ዓረፍተ-ነገር ውስጥ ተዝረክርከው ያሉትን ሀሳቦችንና ድግግሞሾችን አስተካክሎ መጻፍ ቢያስፈልግ፡- "... እንሰት ዘርፈ-ብዙ ጠቀሜታዎች አሉት።

ከነዚህም ጠቀሜታዎች ውስጥ፡- ለሰው ልጅ ምግብነት፣ ለእንስሳት መኖነት መዋሉ እንዲሁም ለገመድ እና ለጂብሳም ስራ አገልግሎት መስጠቱ ተጠቃሾች ናቸው።" በሚል ቢስተካከል የጽሁፉን ተገቢነትንና የሀሳብ ፍሰትን ያቃና ይሆናል። በቁጥር "4" የተጠቀሰው ሀሳብ፡- "...**ከዘ ቡሀላ** ይፈተፈተል **ከዘ ቡሀላ** በትልቅ ሲሀን **ይገበል** እሰት ይቀጠጠላል **ከዘ ቡሀላ** መድጀ... **ከዘ ቡሀላ** ቡለው በምጠድ ለይ **ይገበል ከዘ ቡሀላ** ይቆለል... በትልቅ ሰሀን **ይገበል** ትንሽ ቆይቶ ውሀ **ይገበል** ... አይቤ **ይገበል**... ቅቤ **ይገበል ከዘ ቡሀለ** ምጥምጠ **ይገበል**..." የሚል ነው። በዚህ ሀሳብ አገላለጽ ውስጥ ያሉት የሰዋሰውና የመዋቅር ችግሮች እንዳሉ ሆነው ተገቢ ያልሆኑ የቃላትና ሀረጋት ድግግሞሽ በሰፊው ታይቷል። ከነዚህም ውስጥ "**ከዘ ቡሀላ**" እና "**ይገበል**" የተሰኙ ናቸው። በተጠቀሱ ሀሳቦች ውስጥ መነሻ ሀሳብ የሆኑት የተጠኚ ተማሪዎች የድግግሞሽ ስህተት ብቻ ሳይሆኑ የሰዋሰው ስህተቶች ጭምር ቃል በቃል የተቀመጡ ናቸው።

በአጠቃላይ ከላይ በተጠኚ ተማሪዎች በተጻፉ ድርሰቶች ውስጥ የተቆጠሩት የድግግሞሾች ችግር በቀጥታ ከመማር ማስተማር ድክመቶች የመነጩ እንደሆኑ ታምኗል።

### 4.1.3.1.5 በቃላት ምርጫ ችግር የተፈጠሩ ስህተቶች፡-

እንደ Raimes (1991) አገላለጸ አንድ ጸሀፊ የቋንቋውን ቃላት በተገቢ ቦታ ካልተጠቀመ ሊያስተላልፍ የፈለገው ሀሳብ ተድበስብሶ ሊቀር ይችላል። ከምሁሩ መረዳት የሚቻለው በጽሁፍም ሆነ በንግግር የአንድን ቋንቋ የቋንቋውን ቃላት መርጠን በተገቢው መንገድና በተገቢው ቦታ መጠቀም ካልቻልን ለማስተላለፍ የፈለግነውን ሀሳብ ለአድማጭም ሆነ ለአንባቢ በትክክል ልናደርስ እንደማንችልና ተድበስብሶ ሊቀር እንደሚችል እንገነዘባለን። በዚህ ጥናትም በተተኳሪ ተማሪዎች በተጻፉ ድርሰቶች ውስጥ ተማሪዎቹ ለማስተላለፍ የፈለጉትን ሀሳብ ለማስተላለፍ ያላስቻላቸውን በርካታ ስህተቶችን የፈጠሩ ስላመሆናቸው ለማረጋገጥ ተችሏል። ከነዚህም ስህተቶች ውስጥ የቃላት አመራረጥ ስህተት ተጠቃሽ ነው። ከላይ በሰንጠረዥ አራት በተጠቀሰው በቋንቋ አጠቃቀም ምድብ ስር ከተመድቡት ንዑሳን ስህተቶች ውስጥ የቃላት ምርጫ አንዱ ሲሆን ከአጠቃላይ 3660 ስህተቶች ውስጥ 111 የቃላት ምርጫ ስህተቶች ናቸው። ስህተቶቹ በመቶኛ ሲሰሉ 3.03 ሲሆኑ አማካይ ስህተታቸው 0.6 እንዲሁም የስህተት ድግግሞሻቸው 1.00 መሆኑን በተሰራበት ቀመር ለማረጋገጥ ተችሏል። ከነዚህም ስህተቶች ለአብነት ከተመርጡ ከተማሪዎች ድርሰቶች ውስጥ ከተለዩ ከቃላት ምርጫ ስህተቶች የተወሰኑትን በማቅረብ እንደሚከተለው ለመተንተን ጥረት ተደርጓል።

1. በኮድ/C-47 "የልጅነት ጊዜዬ" በሚል ርዕስ ከተጻፈ ጽሁፍ የተወሰደ፡-

በኮድ/C-47 "የልጅነት ጊዜዬ" በሚል ርዕስ በተዓፈው ጽሁፍ ውስጥ በሶስተኛው መስመር መጀመሪያ ላይ ያለው "ውሀ..." የሚለው ቃል "... **ውሀ** ላይ ገብቼ መውጣት አቅቶኝ ውሀው እየወሰደኝ..." በሚል ሀሳብ ውስጥ ያለ ቦታው የገባ በመሆኑ በተነሳው ሀሳብ ላይ አንባቢዎች ብዙ ጥያቄዎችን እንዲያነሱ ያደርጋቸዋል። ምክንያቱም "ውሀ ላይ ገብቼ" ሲል በምን ዓይነት ውሃ? በጋንዳ ውሃ? በጉድጓድ ውሃ? በወንዝ ውሃ? እነዚህን ጥያቄዎች ሊያስነሳ የቻለው ቃሉ ለቦታው ተመርጦ የገባ ያለመሆኑን ያሳያል። በመሆኑም በተጠቃሹ ቃል ቦታ "ወንዝ ውስጥ..." በሚል የተተካ ቢሆን በተሻለ መልኩ ሀሳቡን ያስተላልፍ ነበር። በዚው ጽሁፍ ውስጥ በአምስተኛው መስመር መጀመሪያ ላይ ያለው "የኔ..." የሚለው ቃል "... **የኔ** አምስት አመቴ ነበር። ... " በሚል መዋቅር ውስጥ ያለ ቦታው ገብቶ የባለታሪኳን የዛሬ አምስት ዓመት ስለነበራት ዕድሜ ለመግለጽ የተፈለገ ቢሆንም ቃሉ እንደገባበት ቦታ ያገለገለው እንደአንደኛ መደብ ነጠላ ቁጥር የዓረፍተ-ነገሩ ባለቤት በመሆን እንጂ የጻሀፊዋን ሀሳብ ለመግለጽ አልቻለም። ጸሀፊዋ ለማስተላለፍ የፈልገችውን ሀሳብ ሊያስተላልፍላት ይችል የነበረው "ያኔ..." የሚል ያለፈ ጊዜን/ዘመን/ አስተዋሽ ቃል መርጣ የተጠቀመች ቢሆን ነበር። ሌላው በስምንተኛው መስመር መጀመሪያ ላይ "ከዚያም" ለማለት ተፈልጎ "**ከዝም**" ተብሎ የተቀመጠው ቃል ለቦተው ተገቢ ሆኖ የተመረጠ ቃል ባለመሆኑ ባለታሪኳ ወንዝ ውስጥ ገብታ

የተሰቃየችበት ዘመን አምስት ዓመቷ የነበራት መሆኑን ይዘን እያለ ከወንዝ ውስጥ ስትወጣ ውሃው ያበሰበሰውን ልብሷን ወላጆቿ እንዳወለቁላት ሰባት ዓመቷ እንደሞላት አድርገን እንድንረዳ አስችሏል። ይህ ቃል የገባበት ቦታ ሌላም ቃል የሚያስፈልገው ቦታ አይደለም። በተመሳሳይ መልኩ በመስመር ዘጠኝ መግቢያ ላይ ያለው "**ከዚያም**..." የሚለው ቃል ተገቢ ያልሆነና መግባትም ያልነበረበት ነው። (አባሪ ዘጠኝ/ኮድ C-47) ይመልከቱ።

2. በኮድ/F-03 "የለቅሶ ስርዓት በስልጤ ብሄረሰብ" በሚል ርዕስ ከተጻፈ የተወሰደ፡-

በዚህ ጽሁፍ ውስጥ  የቃላት ምርጫ ችግሮች ተከስተዋል። ከነዚህም ውስጥ በአምስተኛው መስመር "**ሬሳ**"፣ በሰባተኛው መስመር "**ዓይነት**"፣ በአስረኛው መስመር "**በመወጠር**" እና ከመጨረሻው ሁለተኛው መስመር ላይ የተጠቀሰው "**ሬሳውን**" የተሰኙ ቃላት የምርጫ ችግር ያለባቸው ሆነው ተገኝተዋሉ። ቃላቱ ምንም እንኳን የምርጫ ጉድለት ይኑርባቸው እንጂ የጸሀፊውን ሀሳብ ከማስተላለፍ አላስተጓጎሉም። ነገር ግን ከቋንቋ ማህበራዊነትና ባህላዊነት አጠቃቀም አንጻር ያፈነገጡ ናቸው። መስተካከል ካለባቸው እንደቅደም ተከተላቸው፡- "... እንደሞተ ሬሳ ይታጠባል።..." የሚለው " ... እንደሞተ አስክሬኑ ይታጠባል።..." በሚል፣ "... የስራ ዓይነት ይከፋፈላሉ..." የሚለው "... የስራ ድርሻ ይከፋፈላሉ..." በሚል፣ " ... ድንኳን በመወጠርና ..." የሚለው " ... ድንኳን በመጣልና ..." እንዲሁም "... ወደ ቀብሩ ይዘው ሬሳውን ይወስዳሉ..." የሚለው "... ወደ ቀብሩ አስክሬኑን ይወስዳሉ..." በሚል ቢስተካከሉ ጠንከር ያለ ሀሳብ ከማስተላለፉም ባሻገር የቋንቋውን ባህላዊና ማህበራዊ አገልግሎት የጠበቀ አጠቃቀም እንዲኖረው ያስችላል። (አባሪ ሶስት ኮድ/F-03 ይመልከቱ)

3. በኮድ/E-2 "የጓደኛዬ ታሪክ" በሚል ርዕስ ከተጻፈው ጽሁፍ ውስጥ የተወሰደ፡-

በተጠቀሰው ርዕስ በተጻፈው ጽሁፍ ውስጥ በርካታ የአማርኛ ቋንቋ ያልሆኑ ቃላት አገልግሎት ላይ ውለዋል። ይህም ጸሀፊው በጻፈው ጽሁፍ የቃላት ምርጫ ያላደረገ መሆኑን የሚያሳይ ነው። ለተጨባጭነት ያህል ከተጻፈው ጽሁፍ ውስጥ ባሉት ዓረፍተ-ነገሮች ውስጥ፡- በሁለተኛው መስመር መጨረሻ ላይ "... **ችክ** ..."፣ በአራተኛው መስመር መሃል ላይ "... **ፈሬንዴ** ..."፣ በስድስተኛው መስመር "... **ሙቲስ**፣ Biology ..."፣ ስምንተኛ መስመር መሃል ላይ "**...ወደ ብራዘሩ**..." እና ከመጨረሻው ሁለተኛ መስመር ላይ "... **ጄኒቲሊ** ..." የተሰኙ ቃላት ተመዝግበው የምርጫ ችግር ያለባቸው መሆኑ ተረጋግጠዋል። ቃላቱ ያለምርጫ በመግባት የጽሁፉን ሀሳብ ውስን አንባቢዎች ብቻ እንዲረዱት የሚያስችሉ ከመሆናቸውም በላይ የጽሁፉን ተገቢነት የጣሱ ሆነው ተገኝተዋል። እነዚህ ቃላት በተመረጡ ቃላት ይተኩና ዓረፍተ-ነገሮቹ ተስተካክለው ይጻፉ ቢባል እንደቃላቱ ቅደምተከተል፡- "... ችክ ..." የሚለው "ከሴት ጓደኛ"፣ "...ፍሬንዴ..." የሚለው "ጓደኛዬ"፣ "... ሙቲስ፣ Biology ..." የሚለው "... ሂሳብ፣ ባዮሎጂ ..."፣ "... ወደ ብራዘሩ ..." የሚለው "ወደ ወንድሙ" እና "... ጄኒቲሊ ..." የሚለው "ጎበዝ" በሚሉ ቃላት ቢተኩ የተሻለ የሀሳብ ሽግግሮሽ እንዲኖርና ከውስን

አንባቢዎች ሀሳብ መረዳት አላቆ ወደ ሰፊው አንባቢዎች የሚያሸጋግር ይሆናል። (አባሪ አስር ኮድ/E-2) ይመልከቱ።

በአጠቃላይ ከላይ ያየናቸውና በተተኳሪ ተማሪዎች ድርሰት ውስጥ ተጽፈው የተገኙት ቃላት የቃላት ምርጫ ችግሮች ያሉባቸው ናቸው። ለችግሮቻቸው መፈጠር ምንጮቻቸው፡- ከመማር ማስተማርና ከማስተማር ዘዴዎች፤ ከተማሪዎቹ ቸልተኝነትና ለተተኳሪ ቋንቋ ቃላት ትውስታ ትዕግስት ማጣት፤ ከተተኳሪና ከአፍመፍቻ ቋንቋዎች በተጨማሪ የሌላ ቋንቋ ቃላት ጣልቃ ገብነት እንዲሁም ተቀራራቢ ፍች ያላቸውን ቃላት ለመጠቀም መጣር የስህተት ምንጮቻቸው ሊሆኑ እንደቻሉ ታምኗል።

#### 4.1.3.1.6 የስልጥኛ ቋንቋ ቃላት የመጠቀም ችግር፡-

በቋንቋ አጠቃቀም ምድብ ስር ከተቆጠሩት አጠቃላይ 3660 ስህተቶች ውስጥ 34ቱ የአፍ-መፍቻ ቋንቋ ቃላት አጠቃቀም ስህተቶች ናቸው። ስህተቶቹ በመቶኛ ሲሰሉ 0.93 ሲሆኑ አማካይ ስህተታቸው 0.2 እንዲሁም የስህተት ድግግሞሻቸው 0.33 መሆኑን በተሰራበት ቀመር ለማረጋገጥ ተችሏል።

በአጠቃላይ በቋንቋ አጠቃቀም ስህተት ስር ከተመደቡት ንዑሳን ስህተቶች መካከል በጣም ዝቅተኛው ቁጥር የተቆጠረበት ንዑስ ክፍል ነው።

በዚህም ክፍል በተጠኚ ተማሪዎች በተጻፉ ድርሰቶች ውስጥ የስልጥኛ ቋንቋ ቃላት ጣልቃ ገብነት ችግሮች ተስተውለዋል። በዚህም ምክንያት በድርሰቶቹ ውስጥ ከንዑሳን ስህተት ክፍሎች እንደአንዱ በመሆን ተለይቷል። በመሆኑም እንደስህተት ከተለዩት ከስልጥኛ ቋንቋ ቃላት መካከል ለአብነት የሚሆኑትን ቃላት ከዚህ በታች በማቅረብ ለመተንተን ተሞክሯል።

ምሳሌዎች፡-

1. "...ቆሎ ይጨመቃል '**አፍርንጄ**' ይወቀጣል..."(አባሪ አስራ አንድ ኮድ/F-21) ይመልከቱ።
2. "...ከአንሰት ጥቅሞች አንዱ '**ፍነንቾ**' እና አተካና ... ናቸው..." (አባሪ ሁለት ኮድ/E-34) ተመልከቱ።
3. "...መታዘዝ '**ሀጅር**' ያስገኛል። ... አንድ ልጅ ለእናቱና አባቱ የምታዘዝ ከሆነ ሂመርቂታል '**ጋረ**'

ሰርተው ሰጥተው 'ሂዘውጁታል' ካገባት.... (አባሪ አስራ ሁለት ኮድ/E-42) ይመልከቱ።

ከላይ የቀረቡት ምሳሌዎች ተጠኚዎቹ ተማሪዎች በድርሰታቸው ውስጥ የስልጥኛ ቋንቋ ቃላትን በተተኳሪው (በአማርኛው) ቋንቋ ቃላት መተካት አሊያም በተተኳሪ ቋንቋ ትርጉማቸውን በቅንፍ ውስጥ ማስቀመጥ ሲገባቸው ቀጥታ በመጠቀማቸው ምክንያት በጽሁፋቸው ለማስተላለፍ የፈለጉትን ሀሳብ በፈለጉት ልክ እንዳያስተላልፉ እንቅፋት ሊሆኑ እንደቻሉ ታምኗል። በመጀመሪያው ምሳሌ '**አፍርንጄ**' የሚለው ምጥምጣ መባል ሲገባው

በሁለተኛውም ምሳሌ '**ፍነንቾ**' የሚለው ቆሮጭ ማባል ሲገባው እንዲሁም በምሳሌ ሶስት " '**ሀጅር**'፣ '**ጋረ**'፣ እና '**ሂዘውጁታል**'" የተሰኙት ቃላት እንደቅደም ተከተላቸው፡- ጽድቅ፣ ቤትና ትዳር ያስዙታል በሚሉት በተተኳሪው ቋንቋ ቃላት ቢተኩ አሊያም ፍችዎቻቸው ቢቀመጡ ሀሳብ የማስተላለፍ አቅማቸው በጨመረ ነበር። በምሳሌዎቹ ለማሳየት የተፈለገው የተማሪዎቹ አፍ-መፍቻቸው ቋንቋ ጣልቃ ስለመግባቱና ችግር መፈጠሩን በማሳየት ላይ የተተኮረ በመሆኑ ከድርሰቶቹ ለወጡ አረፍተ-ነገሮች መጠነኛ ማሻሻያ እየተደረገባቸው እርምት የተሰጠባቸው ናቸው። ቃላቱ ከላይ በተገለጸው መንገድ ባለመግባታቸው ከሀሳብ አድበስባሽ ስህተቶች ውስጥ ተመድበዋል። በአጠቃላይ ተጠኚ ተማሪዎች ከላይ የተተነተኑትን የስልጥኛ ቋንቋ ቃላት ጣልቃ መጠቀም እንደችግር ታይቷል። ይህም በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ ምክንያት የተከሰቱ ስህተቶች እንደሆኑ ለመገመት ተችሏል።

### 4.1.3.2 የቋንቋ አወቃቀር ችግር፡-

በስንጠርዥ ስሶስት በቀረበው መረጃ መሰረት በሁለቱም ድርሰቶች ከተመደቡት የስህተት ዓይነቶች በሁለተኛ ደረጃ ቁጥር የተመዘገባው በቋንቋ አወቃቀር ስህተት ምድብ ውስጥ ነው:: በአጠቃላይ ከተገኙት 4558 ስህተቶች ውስጥ በቋንቋ አወቃቀር ችግር ምድብ ውስጥ 662 የሚሆኑት ስህተተች ተቆጥረዋል። ይህም በመቶኛ ሲሰላ 14.5% ሆኗል:: አማካይ የስህተት መጠኑም 3.52 ሲሆን ድግግሞሹ ደግሞ 5.88 ነው::

የዚህ ምድብ ስህተቶችም በሶስት ንዑሳን ስህተት ምድቦች ተሸንሽነው ተፈትሸዋል። የተሸነሸኑት ንዑሳን የስህተት ምድቦች:- የአረፍተ-ነገር ስኬት ችግሮች፣ መዋቅራዊ አገባብ ችግሮችና የአያያዥ ቃላት ችግሮች ናቸው:: ንዑሳን ስህተት ምድቦቹ ከቋንቋ አወቃቀር ስህተት ውስጥ እንደመውጣታቸው የአማርኛን ቋንቋ አወቃቀር መሰረት አድርገው እንደየመዋቅራዊ በህሪያቸው የተለዩ ስህተቶች የተመደቡባቸው ናቸው።

በዚህ በቋንቋ አወቃቀር ምድብ ስር የተቆጠሩትን 662 ስህተቶች እንደየ ድርሻቸው የወሰዱትን ንዑሳን ምድቦች እንዳስቆጠሩት ስህተት ብዛት እንደሚከተለው በዝርዝር ለማቅረብ ተሞክሯል። በዚህም መሰረት በምድቡ የመጀመሪያውን የስህተት ደረጃ የያዘው ንዑስ ምድብ የአረፍተ-ነገር ስኬት ችግር ነው። ብዛቱም 315 ነው። ይህ ስተት በመቶኛ ሲሰላ 47.58%፤ አማካይ ስህተት 1.68 እንዲሁም የስህተት ድግግሞሹ 2.80 ሆኗል። ሁለተኛውን የስህተት ደረጃ የያዘው ደግሞ መዋቅራዊ አገባብ ችግር ነው። ብዛቱም 209 ነው። ይህ በመቶኛ ሲሰላ 31.58%፤ አማካይ ስህተቱ 1.11 እንዲሁም የስህተት ድግግሞሹ 1.85 መሆኑ ተረጋግጧል። ቀሪውና በሶስተኛ ደረጃ ላይ ያለው ንዑስ ስህተት ምድብ የአያያዥ ቃላት ችግር ነው። በዚህ ንዑስ ስህተት ምድብ ስር የተመዘገቡት የስህተት ብዛት 138 ናቸው፡ ፡ የነዚህ ስህተት መቶኛ ስሌት 20.84%፤ አማካይ ስህተቱ 0.73 እንዲሁም የስህተት ድግግሞሹ 1.23 መሆኑ ተረጋግጧል።

በአጠቃላይ የአቢይ የምድቡ 662 ስህተቶች ብዛት መቶኛቸው (100%)፤ አማካይ ስህተታቸው 3.52 እንዲሁም የስህተት ድግግሞሻቸው 5.88 መሆኑን መረዳት ተችሏል።
ከላይ በቋንቋ አወቃቀር ምድብ ስር የተሸነሸኑትን ንዑሳን ስህተት ምድቦች እንደቅደም ተከተላቸው በተጠኚ ተማሪዎች ከተጻፉ ድርሰቶች ውስጥ ለአብነት የሚሆኑትን ድርሰቶች በማቅረብና በማጣቀስ እንደሚከተለው በየምድቦቻቸው ትንታኔ ለመስጠት ጥረት ተደርጓል፡፡ በየምድቦቹም ተለይተው የወጡትን ስህተቶች በሚከተለው በሰንጠረዥ ውስጥ ጠቅለል መልኩ ለማሳየት ተሞክሯል።

## ሰንጠረዥ አምስት:- በቋንቋ አወቃቀር ምድብ የተፈጸሙ ነውሳን ስህተቶች መመዝገቢያ ቅጽ:-

| የስህተት ዓይነት | ድርሰት አንድ | | | | ድርሰት ሁለት | | | | ድርሰት አንድና ሁለት | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| በቋንቋ አወቃቀር | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| የዓረፍተ ነገር ስኬት ችግር | 142 | 21.45 | 1.51 | 2.62 | 173 | 26.13 | 1.84 | 2.96 | 315 | 47.58 | 1.68 | 2.80 |
| መዋቅራዊ አገባብ ችግር | 103 | 15.15 | 1.09 | 1.9 | 106 | 16.01 | 1.13 | 1.81 | 209 | 31.58 | 1.11 | 1.85 |
| አያያዥ ቃላት ችግር | 69 | 10.42 | 0.73 | 1.27 | 69 | 10.42 | 0.73 | 1.18 | 138 | 20.84 | 0.73 | 1.23 |
| ድምር | 314 | 47.43 | 3.34 | 5.79 | 348 | 52.56 | 3.7 | 5.95 | 662 | 100 | 3.52 | 5.88 |

መግለጫ: - በሰንጠረዡ ውስጥ (1) የሚገልጸው (የስህተት ብዛት) ፤ (2) የሚገልጸው (በመቶኛ ሲሰላ) ፤ (3) የሚገልጸው (አማካይ ስህተት) እና (4) የሚገልጸው (የስህተት ድግግሞሽ) ነው:

### 4.1.3.2.1 በአረፍተ-ነገር ስኬት ችግር የተፈጠሩ ስህተቶች፡-

አንድ ዓረፍተ-ነገር ሙሉ መልዕክት ሊያስተላልፍ የሚችለው የየቋንቋዎቹን ህግጋትና ስርዓታዊ መዋቀር የጠበቀ እንደሆነ ብቻ ነው። በመሆኑም ከድምጾች እስከ ሀረጎች ድረስ ያሉት መዋቅሮች ስርዓታዊ መዋቅራቸውን ጠብቀው ከተዋቀሩ የተፈለገውን ሀሳብ ሊያስተላልፍ የሚችለውን ዓረፍተ-ነገር ሊያዋቅሩ ይችላሉ። ይህ ሲሆን ብቻ የተሟላ ትርጉምና የተስተካከለ ቅርጽ ይኖረዋል። ይህንን ሀሳብ ባየ (2010) ሲገልጹት "አንድ መዋቅር የአንድ መሪ ቃልና የተዋቃሪዎች ቅንጅት ነው። ...አንድ ሀረግ በትርጉሙ የተሟላና በቅርጹ የተስተካከለ መሆን አለበት። ... የተስተካከለ የሚሆነውም መሪውና አጃቢዎቹ በሙሉ በቦታቸው ሲገኙና አጃቢዎቹ ከቃቱጋር ስምሙ ሲሆኑ ነው።..." በማለት ይገልጻሉ።

በአጠቃላይ አንድ ዓረፍተ-ነገር የተስተካከለ ወይም የተሳካ ሊሆን የሚችለው ተዋቃሪዎቹ (በጊዜ፣ በጸታ፣ በመደብና በቁጥር...) ቅደምተከተላዊ መዋቅራቸውን ጠብቀው የተሰደሩ እንደሆነ ብቻ ነው። በዚህ ጥናታዊ ስራም በስልጥኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተጠኚ ተማሪዎች በጻፉዋቸው በተለያዩ ድርሰቶች ውስጥ የአረፍተ-ነገሮች አወቃቀር ሰኬት በማጉደላቸው ምክንያት በርካታ ስህተቶች እንደተፈጸሙ ለማረጋገጥ ተችሏል።

ከላይ በሰንጠረዥ አምስት እንደተመለከተው በቋንቋ አወቃቀር አቢይ ስህተት ምድብ ውስጥ ከተፈጸሙት ንዑሳን ስህተት ዓይነቶች መካከል ከፍተኛውን ቁጥር ያላቸው ስህተቶች የተመዘገቡት የተሳኩ ዓረፍተ-ነገሮችን አዋቅሮ ባለመጠቀም ምክንያት የተፈጠሩ ናቸው። በዓረፍተ-ነገሮች ስኬት ችግር ምድብ ውስጥ ትኩረት የተደረገባቸው ነጥቦች፡- የአረፍተ-ነገሮቹን ዋናና ንዑሳን ተዋቃሪ የሆኑትን ሀረጎች መሰረት በማድረግ በጊዜ፣ በፆታ፣ በመደብ፣ በቁጥር፣ በተሳቢ አመልካች ቅጥያዎችና በአጸፋዎች አወቃቀር ስኬት ላይ በማተኮር ነው። እነዚህንም በተጠኚ ተማሪዎች ከተጻፉት ድርሰቶች መካከል ለአብነት ከተወሰዱ ድርሰቶች ውስጥ በቀረቡ ዓረፍተ-ነገሮች እንደሚከተለው ማረጋገጫ ለመስጠት ጥረት ተደርጓል።

**ሀ) በዓረፍተ-ነገር ባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽ አለመሳካት የተፈጠሩ ችግሮች፡-**

በኮድ E-34 በተጻፈው ድርሰት ጽሁፍ ውስጥ የተገኙ ስህተቶች

**ምሳሌ**

1. "... እንሰት ጥቅሙ ለእንስሳትም እንደምግብነት የሚጠቅም ነው( ) እንድሁም ለሰው ልጅ የሚጠቅሙ ናቸው( )..."
2. "...ቃንጨ" ለገመድ እና ለጂቢሳምስራ ይጠቅመሉ።..." (አባሪ ሁለት/ኮድ E-34) ይመልከቱ።

በምሳሌ አንድ በተጠቀሱት ዓረፍተ-ነገሮች ውስጥ የተፈጠረው ችግር "እንሰት" የሚለው ቃል ነጠላ ቁጥር የሆነና የዓረፍተ-ነገሩ ባለቤት በመሆን የገባ የተለያዩ ያላሰሩና ያሰሩ ግሶች ያሉት ነው። ነገር ግን ያሰሩ ግሶቹን ስንመለከት አንደኛው በነጠላ ሌላው በብዙ ቁጥር ያሰሩ ናቸው፡ ፡ በመጀመሪያ ዓረፍተ-ነገር ውስጥ "...የሚጠቅም ነው( )..." ብሎ ሲያበቃ "...እንድሁም ለሰው ልጅ የሚጠቅሙ ናቸው( )..." ይላል።

ይህን ዓረፍተ-ነገር የባለቤትና የማሰሪያ አንቀጽ ተጣጥሞሽ እንዲንኖረው ከተፈለገ የዓረፍተ-ነገሩን ባለቤት የሆነውን ቃል "እንሰቶች" በማለት የመጀመሪያውን ማሰሪያ አንቀጽ "የሚጠቅሙ ናቸው።" በማለት አሊያም የዓረፍተ-ነገሩ ባለቤትና የመጀምሪያው ማሰሪያ አንቀጽ ሳይነካ ሁለተኛውን ማሰሪያ አንቀጽ "የሚጠቅም ነው።" በማለት እንዲጣጣም፤ በሁለተኛው ምሳሌ የተጠቀሰው ዓረፍተ-ነገር ደግሞ የዓረፍተ-ነገሩ ባለቤት "ቃንጨ" የሚልና በነጠላ ቁጥር የተቀመጠ ሆኖ ሳለ ማሰሪያ አንቀጹን "...ይጠቅመሉ።... " በማለት የተቀመጠበት ሁኔታ አግባብነት የሌለውና የቋንቋውን ስርዓታዊ መዋቅሩን ያፋለሰ በመሆኑ "ቃጫ ለገመድና ለጂብሰም ስራ ይጠቅማል።" በሚል ማሰሪያ አንቀጹን ወደ ነጠላ ቁጥር በመቀየር ከዓረፍተ-ነገሩ ባለቤት ጋር እንዲስማማ በማድረግ የአረፍተ-ነገሩ መዋቅር እንዲቃና ማድረግ ይቻላል።

በኮድ C-47 በተጻፈው ድርሰት ጽሁፍ ውስጥ የተገኙ ስህተቶች

ምሳሌ፡-

1. "... አባቴ መጥቶ ወደ ቤት ወሰደኘነ ልብሴን ቀየሩልኘ።..." (አባሪ ዘጠኝ/ኮድ C-47) ይመልከቱ።
2. "... የገጠር ተመርዎች አብዘኘው ትልቅ ሆኖ ስለምገባ..." (አባሪ ዘጠኝ/ኮድ C-47) ይመልከቱ።

በምሳሌ አንድ በተጠቀሰው ዓረፍተ-ነገር የዓረፍተ-ነገሩ ባለቤት "አባቴ" የሚል ስም መሆኑ ግልጽ ነው። ይህ የዓረፍተ-ነገሩ ባለቤት በአንቱታም በአንተታም ሊጠራ የሚችል ነው። ነገር ግን በዓረፍተ-ነገሩ መዋቅር ውስጥ ባሉት ሶስት ተዋቃሪ ግሶች ውስጥ ያሉት አጸፋዎች የዓረፍተ-ነገሩን ባለቤት በትክክል ከማመላከት አንጻር ጉድለት የታየባቸው ሆነዋል። ይህ ውስብስብ ዓረፍተ-ነገር መስተካከል ካለበት "... አባቴ መጥቶ ወሰደኝና ልብሴን ቀየረልኝ። ..." በማለት ወይም "... አባቴ መጥተው ወሰዱኝና ልብሴን ቀየሩልኝ።..." በማለት በሁለት መልኩ ማስተካከል ይቻላል።በሁለተኛው ምሳሌ ላይ በተጠቀሰው ዓረፍተ-ነገር የዓረፍተ-ነገሩ ባለቤት "የገጠር ተማሪዎች" የሚለው ነው። ነገር ግን ከዚህ ባለቤት ጋር ተጣጣሚ የሚሆን ማሰሪያ አንቀጽ አልተበጀለትም። ምክንያቱም በብዙ ቁጥር የተነገረው የዓረፍተ-ነገሩ ባለቤት ማሰሪያ አንቀጹም ብዙ ቁጥር አማለካች በሆነ መነገር ሲገባው ነጠላ ቁጥር አመልካች ቅጥያ ባለውና ባላሰረ አንቀጽ ስለሚገባ በማለት ፈንታ"... ስለምገባ ..." በማለት

ተገልጿል። ይህም ለአረፍት-ነገሩ ስህተት መነሻ ሆኗል። ዓረፍተ-ነገሩ ተስተካክሎ መጻፍ ካለበት "... የገጠር ተማሪዎች አብዛኞቹ ትልልቅ ሆነው ስለሚገቡ..." ወይም "... የገጠር ተማሪ አብዛኛው ትልቅ ሆኖ ስለሚገባ..." በማለት ማቃናት ይቻላል።

በኮድ F-21 በተጻፈው ድርሰት ጽሁፍ ውስጥ የተገኙ ስህተቶች

ምሳሌ፡-

1. "... አንድ ሰምንት ይቆዩነ ከዲሰበ የመጡት እንግደ ይሄዳሉ።..." (አባሪ አስራ አንድ/ኮድ F-21)

ይመልከቱ።

ይህ በተጠቃሹ ኮድ በተጻፈው ድርሰት ጽሁፍ ውስጥ የተገኘው ዓረፍተ-ነገር የባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽ አለመጣጣም ችግር ያለበት ነው። ከዓረፍተ-ነገሩ እንደምንረዳው "ከአዲስ አበባ የመጡ እንግዶች" የዓረፍተ-ነገሩ አብይ ስማዊ ሀረግ መሆኑን የሀረጉም መሪ "እንግዶች" የሚለው የብዙ ቁጥር አመልካች (-ኦች) ያለበት ስም እንዲሁም "አንድ ሰምንት ቆይተው ይሄዳሉ።" የሚለው አብይ ግሳዊ ሀረግ መሆኑን ነው። ለዚህ ለስማዊ ሀረጉ መሪ የቁጥር አቻነት ያለው ግሳዊ ሀረግ መሪ ግስ ያስፈልጋል። አሊያም የአብይ ስማዊ ሀረጉ መሪ ስም ለአብይ ግሳዊ ሀረግ መሪው አቻ የሚሆን መሆን አለበት። ነገር ግን ይህ ሳይሆን ቀርቶ የዓረፍተ-ነገሩ አብይ ስማዊ ሀረጉ መሪ ስም በነጠላ ቁጥር "እንግዳ" በሚል መቀመጡ የዓረፍተ-ነገሩን ስኬት አስተጓጉለዋል። ዓረፍተ-ነገሩ የተስተካከለበት መንገድ ብቸኛ አማራጭ አይደለም። በሌላ መንገድም ሊስተካከል ይቻላል።

## ለ) በባለቤት፣ በተሳቢና በማሰሪያ አንቀጽ ውስጥ የአጸፋዎች አለመስማማት ችግር፡-

በዚህ ክፍል ውስጥ የተፈጸሙት ችግሮች በባለቤት፣ በተሳቢ፣ በማሰሪያ አንቀጽና በሌሎችም ሙያ ዘርፍ በገቡ ቃላት ላይ ተገቢ ያልሆኑ አጸፋዎች በመግባታቸው ምክንያት የተፈጠሩ ችግሮች ናቸው። ተዋቃሪዎቹ ከተተኳሪ ቋንቋ ስርዓታዊ አወቃቀር ያፈነገጡ በመሆናቸው ከተፈጠሩ ስህተቶች ለአብነት ያህል ከተመረጡ ድርሰቶች ውስጥ በወጡ አረፍተ-ነገሮች ውስጥ ባሉ ቃላት እንደሚከተለው ለማሳየት ተሞክሯል። ለአገላለጽ እንዲመች በቅንፍ ውስጥ የተመለከቱት አጸፋዎችና አጸፋዎችን የያዙት ቃላት ለአረፍተ-ነገሮቹ መሳካት የሚሆኑ እንዲሁም በቀይ የተመለከቱት ሊወገዱ/ሊገደፉ/ የሚገባቸው ናቸው።

በኮድ C-47 በተጻፈው ድርሰት ጽሁፍ ውስጥ የተገኙ ስህተቶች

ምሳሌ፡-

1. "... ትምህርት ቤቱ(ም) በጣም ይርቅ (ስለ)ነበር ስደክመች(ኝ) መንገድ ላይ እየተቀመጥኩኝ

(እያረፍኩኝ) እሄድ ነበር(።)

2. "... ከዚያም ሰባት አመቴ ስሆን (ሲሆነኝ) በደ (ወደ) አንደኛ ክፍል ገበሁ'ና(ኝ) (።)
3. "... ከዝየ (ቡ-ኳላ) ድስ እየለች(አለኝ) ..."
4. "... የገጠር ተመርዎች አብዘኘው ትልቅ (ትልልቅ) ሆኖ (ሆነው) ስለምገበ(ቡ)..."(አባሪ ዘጠኝ

ኮድ/C-47) ይመልከቱ።

በኮድ F-21 በተጻፈው ድርሰት ጽሁፍ ውስጥ የተገኙ ስህተቶች

ምሳሌ፡-

1. "... አንድ ቀን ለቀረው ከዲሰበ የሉት ሰዎች ይመጠሉ(።)
2. "... ዳቦ(፣) ሲከር(፣) ዘይት(፣) ... እዘ (ይዘው) ይማጠሉ(።) (አባሪ አስራ አንድ ኮድ/F-21)

ይመልከቱ።

በኮድ B-48 በተጻፈው ድርሰት ጽሁፍ ውስጥ የተገኙ ስህተቶች

1. "... ኢኛም ቢ(ን)ሆን (የ)ትሚርት..." (አባሪ አምስት/በኮድ B-48) ይመልከቱ።

በኮድ E-42 በተጻፈው ድርሰት ጽሁፍ ውስጥ የተገኙ ስህተቶች

ምሳሌ፡-

1. "... መታዘዝ(ን) አላህ የሚወድ(ው) ነገር ነው። ..." (አባሪ አስራ ሁለት/ኮድ E-42) ይመልከቱ።
2. "...መታዘዝ ከ(በ)አለህም በሰዎችሚ ተቀበህነት አለው..."(አባሪ አስራ ሁለት ኮድ/E-42) ይመልከቱ።

በኮድ D-52 በተጻፈው ድርሰት ጽሁፍ ውስጥ የተገኙ ስህተቶች

ምሳሌ፡-

1. "... ስለ እሱዋ ማልከምነት አውርቼም በልጨርሰው(ም)..."አባሪ ስምንት/ኮድ D-52) ይመልከቱ።

ከላይ በቀረቡ ዓረፍተ-ነገሮች ውስጥ ባሉ ቃላት ላይ የተቀነሱና የተቀለሙ አጸፋዎች ለዓረፍተ-ነገሮቹ መቃናት አስተዋጽዖ ያላቸው መሆኑ ከላይ ተገልጿል። በዚው መሰረት በተለያዩ ሙያ ዘርፍ በገቡ ቃላት ላይ ተገቢ ያልሆኑ አጸፋዎች በመግባታቸው፣ በመገደፋቸውና በመተካታቸው ምክንያት የየዓረፍተ-ነገሮቹን መዋቅራዊ መልዕክታቸውን ለማደብዘዝ ችለዋል። በመሆኑም ከኮድ C-47 እስከ ኮድ D-52 ድረስ ባሉት ውስጥ የተጠቀሱትን ዓረፍተ-ነገሮች በሚከተለው መልኩ ማቃናት ከተቻለ የጽሁፎቹ ሀሳብ ሳይስተጓጎል ለአንባቢያን ሊደርስ ይችላል።

በኮድ C-47 ውስጥ የተጠቀሱት መስተካከል ካለባቸው፡-

1. "... ትምህርት ቤቱም በጣም ይርቅ ስለነበር መንገድ ላይ እያረፍኩኝ እሄድ ነበር።

2. "... ከዚያም አስር አመቴ ሲሆነኝ አንደኛ ክፍል ገበሁኝ።

3. "... ከዚያ ቡኋላ ደስ አለኝ ..."

4. "... የገጠር ተማሪዎች አብዘኛው ትልልቅ ሆነው ስለምገቡ..."

በኮድ F-21 ውስጥ የተጠቀሱት መስተካከል ካለባቸው፡-

1. "... አንድ ቀን ስቀረው አዲስ አበባ ያሉት ሰዎች ይመጣሉ።

2. "... ዳቦ፣ ክኳር፣ ዘይት፣ ... ይዘው ይማጠሉ።

በኮድ B-48 ውስጥ የተጠቀሰው መስተካከል ካለበት፡-

1. "... እኛም ብንሆን የትምህርት..."

በኮድ E-42 ውስጥ የተጠቀሱት መስተካከል ካለባቸው፡-

1. "መታዘዝን አላህ የሚወደው ነገር ነው። ..."

2. "... መታዘዝ በአላህም በሰዎችም ተቀበህነት አለው..."

በኮድ D-52 ውስጥ የተጠቀሰው መስተካከል ካለበት፡-

1. "... ስለሷዋ መልካምነት አውርቼ በልጨርሰውም..."

በአጠቃላይ ከቀረቡት ምሳሌዎች መገንዘብ የሚቻለው ተጠኚ ተማሪዎቹ በጻፉዋቸው ድርሰቶች ውስጥ፡- በባለቤት፣ በተሳቢና በማሰሪያ አንቀጽ ተዋቃሪ ቃላት ውስጥ የቁጥር፣ የመደብ፣ የፆታ፣የአመስተዋድድና የመሳሰሉትን አጸፋዎች ተገቢ ባልሆነ መልኩ በመጠቃማቸው ምክንያት ስህተቶችን ፈጽመዋል።

### 4.1.3.2.2 በመዋቅራዊ አገባብ ችግር የተፈጠሩ ስህተቶች፡-

ድርሰት ከዓረፍተ-ነገሮች የሚዋቀር በመሆኑ እያንዳንዱ ዓረፍተ-ነገር የቋንቋውን ትክክለኛ ሰዋሰዋዊ ስርዓት ጠብቆ መዋቀር አለበት። በተለይ በጽሁፍ ለሚተላለፍ መልዕክት የቋንቋውን ስዋሰዋዊ ስርዓት መጠበቅ ትኩረት የሚሸው ጉዳይ ነው።በየደረጃቸው ያሉት የአንድ ቋንቋ መዋቅሮች የቋንቋውን ሰዋሰዋዊ ስርዓት ጠብቀው ካልሆነ በስተቀር ሊተላለፉ የተፈለጉትን መልዕክቶች በስርዓቱ ሊያስተላልፉ አይችሉም።

በዚህ ርዕስ ስርም የአማርኛ ቋንቋ ሰዋሰዋዊ መዋቅርን መሰረት በማድረግ በቃላት በሀረጋትና በዓረፍተ-ነገሮች ላይ ትኩረት ተደርጓል። በመሆኑም በተጠኚ ተማሪዎች ከተጻፉት ድርሰቶች መካከል ከተወሰዱ መዋቅሮች ለአብነት ያክል የሚከተሉትን በማቅረብ ትንታኔ ለመስጠት ተሞክሯል።

በኮድ F-3 በተጻፈው ድርሰት ጽሁፍ ውስጥ የተገኙ ስህተቶች

ምሳሌ፡-

1. "... ወንዶች... ወደ ቀብሩ ይዘው እሬሳውን ..."

2. ጸሀፊው "... ለቅሶ ማለት..." ብሎ ጀምሮ ስለለቅሶ ምንነት ሳይጨርስ "... የለቅሶ ባህላዊ

አከባበር..." (አባሪ ሶስት ኮድ/F-3) ይመልከቱ።

መስተካከል ካለባቸው፡- በምሳሌ አንድ የተጠቀሰውን ሀሳብ በያዙት ዓረፍተ-ነገሮች ውስጥ የተፈጠረው ችግር የተሳቢ (እሬሳውን)ና ያላሰረ አንቀጽ (ይዘው) የተሰኙ ቃላት ያለቦታቸው በመግባታቸው ነው። ቃላቱ ወደየመዋቅራዊ ስፍራቸው እንዲገቡ ተደርገው ቢዋቀሩ እንደሚከተለው የተስተካከለ ይሆናል።"

...ወንዶች...አስክሬኑን ይዘው ወደ ቀብሩ ይሄዳሉ።..." የሁለተኛውም ምሳሌ ያልተቋጨና ቅደም ተከተላቸውን ያልጠበቁ ሀሳቦች ታጭቀዋል። ሀሳቦቹ መስተካከል ካለባቸው፡- "... ለቅሶ ማለት አንድ ሰው ሲሞት የሚደረግ የሀዘን መግለጫ ሂደት ነው። ... ይህ የለቅሶ ሀዘን መግለጫ ባህላዊ ስነ-ስርዓት እንደሀገራችን ብሄረሰቦች ባህል ይለያያል። እንደስልጤ ብሄረሰብም ከማህበረሰቡ አባል የሆነ ሰው ሲሞት በሀዘነ መግለጫ ሂደት ውስጥ የራሱ የሆነ ቅደምተከተሉን ጠብቆ የሚሄድ ባህላዊ ስነ-ስርዓት አለው። ከነዚህም ውስጥ..." በማለት የሀሳብ ፍሰቱ እንዲስተካከል ማድረግ ይቻላል።

በኮድ D-52 በተጻፈው ድርሰት ጽሁፍ ውስጥ የተገኙ ስህተቶች፡-

ምሳሌ፡-

1. "... ጓደኛዬ ህያት ትባላለ...ያማለቀወን ነገር የምተሰወቃኝ፣ ያምትመክርኝ፣... ልክ እንደ እህቴ

ናት..." የተሰኙ ናቸው። (አባሪ ስምንት ኮድ/D-52) ይመልከቱ።

እነዚህ ዓረፍተ-ነገሮች የተሳካ አገባብ እንዲኖራቸው ከተፈለገ "... ጓደኛዬ ህያት የማላውቀውን ነገር የምታሳውቀኝ፣ የምትመክረኝ፣ ... በመሆኗ ልክ እንደ እህቴ ነው የማያት፡ ፡ ... " በሚል የአገባብ ስርዓትቱን ጠብቆ ከተዋቀረ በሀሳብ ፍሰት ላይ መሰናከሎች አይገጥሙም።

በኮድ A-43 በተጻፈው ድርሰት ጽሁፍ ውስጥ የተገኙ ስህተቶች፡-

ምሳሌ፡-

1. " ...በአንድ ሀገር ትምርት አስፋለግ ነው () ሚክናቱ የሀገር ሰው ካልተማረ ሀገረ መሰደግ አይችልም

() ..." (አባሪ አራት ኮድ/A-43) ይመልከቱ።

ከላይ በሁለት ዓረፍተ-ነገሮች ለመግለጽ የተሞከረው ሀሳብ በቃላትና ሀረጋት ያለ ቦታቸው በመግባታችው ምክንያት የሀሳብ መድበስበስ ታይቶበታል። ይህንን ችግር መቅረፍ ቢያስፈልግ "... ትምህርት ላንድ ሀገር ዕድገት አስፈላጊ ነው። አንድ ሀገር የተማረ የሰው

ሀይል ካለው የማደግ ዕድሉ የሰፋ ነው። ምክንያቱም የተማረ ሰው በዕውቀት ስለሚመራ ካልተማረ ሰው በተሻለ ሁኔታ ሀገሩን ሊያሳድግ ይችላል። ..." በሚል መስተካከል አለበት።

#### 4.1.3.2.3 በአያያዥ ቃላት አገባብ ችግር የተፈጠሩ ስህተቶች፡-

ከቋንቋ አወቃቀር ስህተት ምድብ ስር በተጠኚ ተማሪዎች ከተጻፉ ድርሰቶች ውስጥ ከተቆጠሩ 662 ስህተቶች ውስጥ 138ቱ በአያያዥ ቃላት አገባብ ንዑስ ስህተት ምድብ ውስጥ የተቆጠሩ ናቸው። የስህተቶቹ አተፈጻሙበት ሁኔታ አያያዥ ቃላቱን በመዋቅሩ ውስጥ በቦታቸው ባለመጠቀም፣ ያለቦታቸው በማስገባትና የአያያዥ ቃላትን ቦታ በስርዓተ-ነጥቦች ተክቶ በመጠቀም ምክንያት የተፈጠሩ ናቸው። ይህ ንዑስ ስህተት ምድብ ከአብይ ከቋንቋ አወቃቀር ምድብ ስር ከተሸነሸኑት ንዑሳን ክፍሎች የመጨረሻውን የስህተት መጠን ያስቆጠረ ነው። በዚህ ንዑስ ስህተት ክፍል የተቆጠሩ ስህተቶች በመቶኛ ሲሰሉ 20.84%፣ አማካይ ስህተት 0.73 እንዲሁም የስህተት ድግግሞሻቸው 1.23 መሆናቸው ተረጋግጧል። ይህም ከላይ በሰንጠረዥ አምስት ተመልክቷል።

ከዚህ በታችም በተጠኚ ተማሪዎች ከተጻፉ ድርሰቶች መካከል ከተወሰዱ ድርሰቶች ውስጥ ለአብነት በቀረቡ ዓረፍተ-ነገሮች ውስጥ የታዩትን የአያያዥ ቃላት አገባብ ስህተቶችን እንደሚከተለው ለማሳየት ተሞክሯል።

በኮድ A-43 በተጻፈው ድርሰት ውስጥ በአያያዥ ችግር የተፈጠረ ስህተት

ምሳሌ፡-

1. "... ስለዚህ ሀገር ለድግ የሚችለው ስመር ነው። አሁን ኢኔ የሚለው ሰዎች የተመረ ዬት ደረሰ

የምለው አበበል ህቅር ኢለለው። ..." (አባሪ አራት ኮድ/A-43) ይመልከቱ።

በዚህ ምሳሌ የተጠቀሰው ሀሳብ የአያያዥ ችግር ያለበት መዋቅር ነው። ይህም በሁለተኛው ዓረፍተ-ነገር መነሻ ላይ "አሁን" ብሎ የጀመረው ቃል ተነስቶ "በመጨረሻም" በሚል የሚተካ ቢሆን ከመጀመሪያው ሀሳብ አገላለጽ የተሻለ ይሆናል። ይህ አያያዥ ቃል በተጠቀመው ቦታ መግባት የሚያስፈልግበት ሌላው ምክንያት ዓረፍተ-ነገሩ ማጠቃለያ ሀሳብ የያዘ በመሆኑም ጭምር ነው።

በኮድ D-52 በተጻፈው ድርሰት ውስጥ በአያያዥ ችግር የተፈጠረ ስህተት

ምሳሌ፡-

1. "... ስለእሱዋ ማልከምነት አውርጩም አልጨርሰው። ..."
2. "... ለሁላችንንም ፈጠሬ አምለክ እንደሱዋ ያለ መልከም ጎደኘን ይሰጠን እላለው። ..." (አባሪ

ስምንት ኮድ/D-52) ይመልከቱ።

ከላይ በተጠቀሱት ሁለት ዓረፍተ-ነገሮች ውስጥ የአያያዥ ቃላት አጠቃቀም ችግሮች የታዩባቸው ናቸው። መስተካከል ካለባቸው በሚከተለው መልኩ መስተካከል አለባቸው። በምሳሌ አንድ የተጠቀሰው ዓረፍተ-ነገር "... ስለእሱዋ" ብሎ ከመጀመሩ በፊት "በአጠቃላይ" በሚል ማጠቃለያ ለመስጠት በሚያስችል አያያዥ ቃል በመጀመር ሀሳቡን መቋጨት ይቻላል። በሁለተኛውም ምሳሌ የተጠቀሰው ዓረፍተ-ነገር "... ለሁላችንንም... " ብሎ ከመጀመሩ አስቀድሞ "በመጨረሻም" በሚል አያያዥ ቃል የጀመረ ቢሆን የሀሳብ ፍሰቱ የበለጠ የተስተካከለ ሊሆን ይችላል። በዚህም መሰረት፡- የምሳሌ አንድ "... በአጠቃላይ ስለሷዋ መልካምነት አውርቼም አልጨርሰሁም።... " ምሳሌ ሁለት ላይም ያለው ሀሳብ "... በመጨረሻም ለሁላችንም ፈጣሪ አምላክ እንደሷዋ ያለ መልካም ጓደኛ ይሳጠን እላለሁ..." በማለት ማስተካከያ ከተሰጠው ከመጀመሪያው በተሻለ መልኩ የሀሳብ ማስተላለፍ ሁኔታ ይኖራል።

በኮድ E-42 በተጻፈው ድርሰት ውስጥ በአያያዥ ችግር የተፈጠረ ስህተት

ምሳሌ፡-

1. "... መተዘዘ ከኣላህም በሰዎችም ተቀበህነት አለው።..."(አባሪ አስራ ሁለት/ኮድ E 42)

   ይመልከቱ፡:

ይህ ዓረፍተ-ነገር የያዘውን ሀሳብ በተሻለ መልኩ ለመግለጽ የሚያስችል አያያዥ ቃል መጠቀም የነበረበትን መጠቀም ባለመቻሉ የተፈጠረ ስህተት ታይቷል። ይህም "... መተዘዘ ... " ብሎ ከመጀመሩ አስቀድሞ "በአጠቃላይ" የሚል አያያዥ ቃል መጠቀም ቢችል የሀሳብ ፍሰቱ ይበልጥ የተስተካከለ ይሆን ነበር። በዚህም መሰረት "... በአጠቃላይ መታዘዝ በአላህም በሰዎችም ተቀባይነት አለው። ..." በሚል ማስተካከል ይቻላል።

### 4.1.3.3 በስርዓተ-ነጥቦች አጠቃቀም ችግር የተፈጠሩ ስህተቶች፡-

ከላይ በሰንጠርዥ ስሶስት እንደተመለከተው ተጠኚ ተማሪዎቹ በሁለት ዙር በጻፉዋቸው ድርሰቶች ውስጥ አጠቃላይ ከተመዘገቡት 4558 ስህተትቶች ውስጥ 213 ስህተቶች የተመዘገቡበትና ከተጠቀሱት ስህተት ምድቦች ሶስተኛውን ደረጃ የያዘው የስርዓተ-ነጥቦች አጠቃቀም ምድብ ነው። የዚህ ምድብ ስህተቶች በመቶኛ ሲሰሉ 4.7% ሲሆኑ 1.13 አማካይ የስህተት መጠናቸው ነው። አማካይ የህተት ድግግሞሻቸው ደግሞ 1.89 መሆኑን አሳይቷል፡ ፡ የነዚህንም ስህተቶች ሁኔታ በተጠኚ ተማሪዎች ከተጻፉ ድርሰቶች መካከል ለአብነት የሚሆኑትን በመውሰድ በውስጣቸው የተፈጠሩትን የስርዓተ-ነጥቦችን አጠቃቀም፣ አገባብ እንዲሁም ተገቢነት በሚከተለው መልኩ ለምዳሰስ ተሞክሯል።

በኮድ F-21 በተጻፈው ድርሰት ጽሁፍ ውስጥ በስርዓተ-ነጥቦች አጠቃቀም ችግር የተፈጠሩ ስህተቶች፡-

**ምሳሌ፡-**

1. "... ዳቦ () ሲከር () ዘይት () ... እዘ ይማጠሉ () (አባሪ አስራ አንድ ኮድ/F-21) ይመልከቱ።

በተጠቀሰው ምሳሌ ውስጥ የተፈጠሩት ችግሮች የነጠላ ሰርዝ እና የአራት ነጥብ አጠቃቀም ችግሮች ናቸው። እነዚህም ስህተቶች ከመጀመሪያው "ዳቦ" ከሚለው ቃል እስከ ዘይት እስከሚለው እና በቀጣዮቹም ቃላት መካከል ነጠላ ሰረዝ በመጠቀም መዘርዘር ሲቻል ያለ ምንም ስርዓተ-ነጥቦች ቃላቱን ብቻ በመዘርዘር እንዲሁም በስተመጨረሻ የሀሳብ መቋጫ የሆነውን አራት ነጥብ ባለመጠቀም ምክንያት የሀሳብ ፍሰት መስተጓጎል ሁኔታ ታይቷል።

በኮድ B-35 በተጻፈው ድርሰት ጽሁፍ ውስጥ በስርዓተ-ነጥቦች አጠቃቀም ችግር የተፈጠሩ ስህተቶች፡-

ምሳሌ፡-

1. "... አንድ ወጣት እድሜው ለትዳር ሲደርስ ቤተሰቦቹ (ለሱ ትመጥናለች) ብለው ያሰቡዋትን..."
2. "... ሽማግሌ በመላክ (ልጃቹን ለልጃችን) በማለት ይጠይቃሉ( ) ..."
3. "... የወንዱ ቤተሰብ ሰርጉን በደማቅ ሁኔታ ደግሰው( ) ዘመድ አዝማድ ጎረቤት ተጠርቶ ሰርጉ ..."

(አባሪ አስራ ሶስት ኮድ/B-35) ይመልከቱ።

በተጠቀሱት ኮዶች በተጻፉ ድርሰት ጽሁፎች ውስጥ የአገባብ ችግር የታየባቸው የስርዓተ-ነጥብ ዓይነቶች፡- የነጠላ ሰረዝ፣ የነጠላ ትምህርተ-ጥቅስ፣ ድርብ ትምህርተ-ጥቅስ እና አራት ነጥብ ተጠቃሾች ናቸው። እነዚህ ስህተቶች መስተካከያ ተደርጎባቸው የተቃና ሀሳብ ያስተላልፉ ቢባል እንደሚከተለው መስተካከል አለባቸው።

የኮድ F-21 ምሳሌ፡-

1 "...ዳቦ፣ ሲከር፣ ዘይት፣... ወዘተ ይዘው ይማጠሉ። ..." በሚል መስተካከል ይገባል።

የኮድ B-35

ምሳሌዎች፡-

1. "... አንድ ወጣት ዕድሜው ልትዳር ሲደርስ ቤተሰቦቹ 'ለሱ ትመጥናለች' ብለው ያሰቡዋትን... "
2. "... ሽማግሌ በመላክ 'ልጃቹን ለልጃችን' በማለት ይጠይቃሉ። ..." እና
3. "... የወንዱ ቤተሰብ ሰርጉን በደማቅ ሁኔታ ደግሰው፤ ዘመድ አዝማድ እና ጎረቤት ተጠርቶ ሰርጉ

በደማቅ ሁኔታ ይከበራል።..." በሚል መስተካከል አለበት።

በኮድ A-014 በተጻፈው ድርሰት ጽሁፍ ውስጥ በስርዓተ-ነጥቦች አጠቃቀም ችግር የተፈጠሩ ስህተቶች፡-

ምሳሌ፡-

1. "... ቤተሰቦቻችንም ለበዓሉ ቅድመ ዝግጅት ይደራገሉ( ) ከዝግጅቱ ነሙነ የተወሳነውን

ልጥቀሳችሁ(፡-) በመጀመሪያ አበት በሬውን ይገዘል(፡) ወጣትም እንጫት ይፈልጣሉ(፡) ልጃገረዱም ቤት ኖራ ትቀባለች( ) (አባሪ አስራ አራት ኮድ/A-14) ይመልከቱ።

በኮድ A-14 የተጠቀሰው የስርዓተ-ነጥቦች የአገባብና የለይቶ መጠቀም ችግሮች ተቀርፈው የጽሁፉ ሁሳብ ያለምንም መጎርበጥ ለሚፈለገው አካል እንዲደርስ ከተፈለገ በሚከተለው መልኩ ተቃንቶ መቅረብ አለበት።

"... ቤተሰቦቻችንም ለበዓሉ ቅድመ ዝግጅት ያደራጋሉ። ከዝግጅቶቹም መካከል የተውሰኑትን ልጥቀስላችሁ፡- በመጀመሪያ አባት በሬውን ይገዘል፤ ወጣቶቹ እንጨት ይፈልጣሉ፤ ልጃገረዶቹም ቤት ኖራ ይቀባሉ፤ ... " በማለት ማቃናት ይቻላል።

ከላይ እንደተመለከተው በተጠኚ ተማሪዎች በተጻፉ ድርሰቶች ውስጥ በርካታ የስርዓተ-ነጥቦች የአገባብና የለይቶ አለመጠቀም ችግሮች ተስተውለዋል። ጥናቱ ትኩረት ያደረገባቸው በስልጥኛ ቋንቋ አፍ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የስርዓተ-ነጥቦችን አገባብና ስርዓተ-ነጥቦቹን ለይተው ከመጠቀም አንጻር ችግሮች ያሉባቸውና በድርሰቶቻቸውም ውስጥ ስህተቶችን የሚፈጥሩ ስለመሆናቸው ለማረጋገጥ ተችሏል።

በአጠቃላይ ተጠኚ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የአማርኛን ቋንቋ ስርዓታዊ መዋቅር የጠበቁ ስርዓተ-ነጥቦች አጠቃቀም ሂደት ላይ ስህተት ፈጽመዋል። የስህተታቸውም ምንጭ የመማር ማስተማር ጉድለት ሊሆን እንደሚችል ተገምቷል።

### 4.1.3.4 ልለዩ ባልተቻሉ ችግሮች ምክንያት የተፈጠሩ ስህተቶች፡-

በተጠኚ ተማሪዎች በሁለት ዙር በተጻፉ ድርሰቶች ውስጥ ከተገኙት አጠቃላይ ስህተቶች ውስጥም 23 ያህሉ ልለዩ ባልተቻሉ ችግሮች ምክንያት የተፈጠሩ ስህተቶች ምድብ ውስጥ የተቆጠሩ ስህተቶች ናቸው:: ይህም በመቶኛ ሲሰላ 0.5% ሆኗል:: አማካይ የስህተት መጠኑም 0.12 ሲሆን የስህተት ድግግሞሹም 0.20% መሆኑን ያሳየ ነው::

ይህ ከአብይ ግድፈት ዓይነቶች መካከል በቁጥር የመጨረሻውን ደረጃ ይዞ የሚገኝ ምድብ ነው። በዚህ ምድብ ስር የሚቃኙት በድርሰት ጽሁፎቹ ውስጥ ምንም ዓይነት ትርጉምና ፈይዳ የሌላቸው፤ የስህተት ዓይነቶቹን በቀላሉ ላይቶ ለማመልከት አስቸጋሪና ውስብስብ የሆኑ ቃላትና መሰል ምልክቶች ናቸው።

በዚህ ምድብ ውስጥ ከተቃኙ ስህተቶች የድርሻቸውን ከወሰዱ ድርሰቶች መካከል በተወሰዱ ድርሰቶች ውስጥ ለመለየት ያልተቻሉ ሆነው ከተለዩት ውስጥ ለአብነት ያክል እንደሚከተለው ለማሳየት ጥረት ተደርጓል።

በኮድ F-21 በተጻፈው ድርሰት ጽሁፍ ውስጥ መለየት ባልተቻሉ ችግሮች ምክንያት የተፈጠሩ ስህተቶች፡-

ምሳሌ፡-

1. "... ቤትን እና ግቤ እንጸደለን አንድ ሰምንት ስቀረው '**ሽንሽን**' '**እንስቀለገን**' ። ..."
2. "... አንድ ሰምንት ስቀረው ጤፉ እነበከለን '**ገዜይ**' ..." (አባሪ አስራ አንድ ኮድ/F-21) ይመልከቱ።

በኮድ C-3 በተጻፈው ድርሰት ጽሁፍ ውስጥ ለመለየት ባልተቻሉ ችግሮች ምክንያት የተፈጠሩ ስህተቶች፡-

ምሳሌ፡-

1. "... አተካነ ተሰረ **መስት** ነው። ..." (አባሪ ሰባት ኮድ/C-3) ይመልከቱ።

ከላይ በተጠቀሱት ኮዶች በተጻፉ ድርሰት ጽሁፎች ውስጥ በረካታ የስህተት ዓይነቶች ተከስተዋል። ይሁን እንጂ በዚህ ስህተት ምድብ ውስጥ ለማሳየት የተፈለገው ለመለየት ያልተቻሉ ስህተቶች እንደመሆኑ መጠን በጽሁፎቹ ውስጥ ጎልተው/Boled/ ሆነው የሚታዩት በዚው ምድብ ስህተት ዓይነቶች ውስጥ ተጠቃሾች ናቸው።

እነዚህ የተጠቀሱት ቃላት የሰዋሰው መቃናትም ሆነ መዋቅራዊ አገባብ ይስተካከል ቢባል እንኳን ፍንጭ ለመስጣት ያልበቁ፤ በምንባቡ ውስጥም ለመነሳት ለተሞከረው ሀሳብ ምንም ዓይነት ፍንጭ ሊሰጡ ያልቻሉና ትርጉም የሌላቸው በመሆናቸው ምክንያት በዚህ ምድብ ስር ተመዝጋቢ ስህተቶች ሆነው ተገኝተዋል።

በአጠቃላይ በስልጥኛ ቋንቋ አፍ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ በጽሁፋቸው ውስጥ ምንም ትርጉምና ፈይዳ የሌላቸውን ቃላት የሚጠቀሙ በመሆናቸው በድርሰት ጽሁፋቸው ውስጥ ለመለየት ያልተቻሉ ስህተቶችን ፈጥረዋል።

### 4.1.4 ከተማሪዎች ጽሁፍ መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ማብራሪያና ውጤት ትንተና፡-

ለጥናቱ ዓላማ ማሳኪያ የሚሆኑ መረጃዎችን ለማሰባሰብ አገልግሎት ላይ ከዋሉት መረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴዎች አንዱ የሆነው የጽሁፍ መጠይቅ ለተማሪዎች የቀረበ መሆኑ በምዕራፍ ሶስት ተገልጿል:: በዚህም መረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ በተማሪዎች ድርሰት ውስጥ ለሚፈጸሙ ስህተቶች ምንጮቻቸው ምን ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ ለማጣራት በቀረበው በድርሰት ጽሁፍ መልመጃ የተገኘውን ውጤት ለማረጋገጥ እንዲያስችል አገልግሎት ላይ የዋለ ነው::

በተማሪዎች ድርሰት ጽሁፍ ልምምድ ጊዜ ለሚፈጸሙ ለተለያዩ ስህተቶች ተጽዕኖዎች ሊሆኑ ይችላሉ ተብለው ከታለሙ መላምቶች መካከል ከሆኑት ውስጥ፡- የመማር ማስተማር

ዘዴዎችና ማስተማሪያ መሳሪያዎችን፤ የውስጠ-ቋንቋን እንዲሁም የተማሪዎች ስነ-ልቦናዊ ሁኔታዎችን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ መረጃዎችን ከተማሪዎች ለማግኘት ሲባል የቀረቡ መጠይቆች ናቸው። የጽሁፍ መጠይቆቹም የቀረቡት ለጥናቱ ብቁ ሆነው ለተገኙ ለዘጠና አንድ(91) ተማሪዎች ነው። የቀረቡት መጠይቆች የተጠቀሱትን መላምቶች ለማረጋገጥ በሚያስችል መልኩ በተለያዩ አጠያየቅ ዘዴዎች የቀረቡ ናቸው::

በአጠቃላይ ከላይ በተማሪዎች በጽሁፍ ልምምድ ጊዜ ለሚፈጸሙ ስህተቶች ተጽዕኖ ሊፈጥሩ ይችላሉ ተብለው ግምት የተሰጣቸውን ነጥቦች ዒላማ ያደረጉ ስብጥር የጽሁፍ መጠይቆች ቀርበዋል። ተማሪዎቹም ለመጠይቆቹ በሰጡት ምላሽ መሰረት በያንዳንዱ በተጽዕኖነት በታለሙ ነጥቦች ስር የተገኙ ውጤቶችን እንደሚከተለው ተተንትነው እንዲቀመጡ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል:: አተናተኑም መላሾቹ የሰጡትን አማራጮች ብዛት መሰረት በማድረግና ወደ መቶኛ በመለወጥ ለያንዳንዱ ጥያቄ የተሰጡትን አማራጮች ቃላዊ ትንታኔ በመስጠትና በሰንጠረዥ አሀዛዊ በሆነ መልኩ በማስቀመጥ ነው።

### 4.1.4.1 የመማር ማስተማር ዘዴዎችና የማስተማሪያ መሳሪያዎች፡-

በተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝት ርዕስ ስር እንደተዳሰሰው አንድን ቋንቋ በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎችን ለስህተት ከሚያጋልጡዋቸው ምክንያቶች መካከል ታላሚውን ቋንቋ ለማስተማር የተዘጋጁት የማስተማሪያ መሳሪያዎችና የመማር ማስተማር ዘዴ ድክመቶች ናቸው። Nation (2001) "በተማሪዎች ውጤት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ከሚያሳድሩ ተላውጦዎች አንዱ የማስተማሪያ መሳሪያው ተገቢነት፣ ክብደትና ቅለት ነው፤... "በማለት ያስረዳሉ።

ስለሆነም የመምህሩ የትምህርት አቀራረብ ዘዴ ድክመትና የማስተማሪያ መሳሪያዎች በተገቢው ሁኔታ አለመቀረጽ ለተማሪዎች ስህተት መፈጸም በምክንያትነት ልጠቀሱ ይችላሉ:: በመሆኑም በተማሪዎቹ በድርሰት ጽሁፍ ልምምድ ሂደት ውስጥ ለሚፈጸሙት ስህተቶች እንደምንጭነት ሊጠቀሱ ይችላሉ? ወይስ ሊጠቀሱ አይችሉም? የሚለውን ለመፈተሽ የሚያስችሉ መጠይቆች በተለያዩ አቀራረቦች ቀርበዋል:: ከነዚህም ውስጥ በተራ ቁጥር 9፣ 12፣ 18 እና 19 የተጠቀሱት ለአብነት ተጠቃሾች ናቸው:: (አባሪ አስራ ስድስት ይመልከቱ)

ከነዚህም መጠይቆች ለአብነት የሚሆኑትን በመውሰድ ከቆሙለት ዓላማ አንጻር የተማሪዎቹ ምላሽ ምን እንደሚመስል በዝርዝር በገለጻ እንደሚከተለው ለማሳየት ተሞክሯል።

በተጠቆመው መሰረት በስልጥኛ ቋንቋ አፍ-ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ ለሚፈጽሙት ስህተቶች የመምህራን ማስተማር ዘዴና ማስተማሪያ መሳሪያዎች ተጽዕኖዎች

ሊሆኑ እንደሚችሉ በአጥኚው ታልመዋል። ይህንኑ ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የጽሁፍ መጠይቆች ለተማሪዎች ቀርበዋል።

ለነዚህም ጥያቄዎች ተጠኚ ተማሪዎች ለያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ ለያንዳንዱ አማራጭ ምላሽ የሰጡ ተማሪዎች ብዛት ወደ አማካይ (%) በመቀየር ከታች ገለጻ ተሰጥቷል።

በጥያቄ ቁጥር (9) "የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የጽህፍ ክሂልን ለማስተማር ከተማሪው መጽህፍ በተጨማሪ አጋዥ መጽህፍት ከመጠቀም አንጻር" ለተጠየቁት ጥያቄ ከስጡት ምላሽ ከፍተኛ አንጻር የመጀመሪያውን ደረጃ የያዘው አማራጭ (ለ) ነው። በዚህ አማራጭ ስር የቀረበውም "ከመማሪያ መጽህፍ ላይ ብቻ" የሚል አማራጭ ሀሳብ ነው። ይህን አማራጭ ምላሻቸው ያደረጉ ተማሪዎችም ብዛት (37) ሲሆኑ ይህም ከአጠቃላይ ዘጠና አንድ(91) ተማሪዎች ውስጥ በመቶኛ ሲሰላ 40.7% የሆነ ምላሽ ነው። ሁለተኛውን ደረጃ የያዘው አማራጭ (ሀ) ነው። በዚህ አማራጭ ስር የቀረበውም "ከመማሪያ መጽህፍ በተጨማሪ ከጋዜጦች፣ ከመጽሄቶች፣...ወዘተ በመጠቀም" የሚል አማራጭ ሀሳብ ነው። ይህን አማራጭ ምላሻቸው ያደረጉ ተማሪዎችም ብዛት (21) ሲሆኑ ይህም ከአጠቃላይ ተማሪዎች ውስጥ በመቶኛ ሲሰላ 23.1% የሆነ ምላሽ ይየያዛ ነው። ሶስተኛውን ደረጃ የያዘው አማራጭ (መ) ነው። በዚህ አማራጭ ስር የቀረበውም "ያለምንም መጽህፍት" የሚል አማራጭ ሀሳብ ነው። ይህን አማራጭ ምላሻቸው ያደረጉ ተማሪዎችም ብዛት (17) ሲሆኑ ይህም ከአጠቃላይ ተማሪዎች ውስጥ በመቶኛ ሲሰላ 18.7% የሆነ ምላሽ ነው። የመጨረሻውና አራተኛውን ደረጃ የያዘው አማራጭ (ሰ) ነው። በዚህ አማራጭ ስር የቀረበውም "አላስታውስም" የሚል አማራጭ ሀሳብ ነው። ይህን አማራጭ ምላሻቸው ያደረጉ ተማሪዎችም ብዛት (16) ሲሆኑ ይህም ከአጠቃላይ ተማሪዎች ውስጥ በመቶኛ ሲሰላ 17.5% የሆነ ምላሽ ነው።

ከተማሪዎቹ ምላሽ መረዳት የተቻለው መምህራን ለመማር ማስተማሩ ሌሎች ቁርጭኝና አጋዥ መጽህፍትን የማይጠቀሙና በተማሪው መጽህፍ ላይ ብቻ የሚንጠለጠሉ መሆንቸውን የሚጠቁሙ ምላሾች ሚዛን የደፉ መሆናቸውን ነው።

በጥያቄ ቁጥር (12) "አማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽህፍ ውስጥ ከሚገኙ ምንባቦች ውስጥ ምን ይህሉ ሳቢና አናቃቂ ናቸው?" ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ ከስጡት ምላሽ አንጻር ከአጠቃላይ ዘጠና አንድ(91) ተማሪዎች ውስጥ የመጀመሪያውን ከፍተኛ ደረጃ የያዘው አማራጭ (ሰ) ነው። በዚህ አማራጭ ስር የቀረበውም "ጥቂቱ" የሚል አማራጭ ሀሳብ ነው። ይህን አማራጭ ምላሻቸው ያደረጉ ተማሪዎችም ብዛት (35) ሲሆኑ ይህም ከአጠቃላይ ተማሪዎች ውስጥ በመቶኛ ሲሰላ 38.5% የሆነ ምላሽ ይየያዛ ነው። ሁለተኛውን ደረጃ የያዘው አማራጭ (መ) ነው። በዚህ አማራጭ ስር የቀረበውም "ውስኑ" የሚል አማራጭ ሀሳብ ነው። ይህን አማራጭ ምላሻቸው ያደረጉ ተማሪዎችም ብዛት (26) ሲሆኑ ይህም ከአጠቃላይ ተማሪዎች ውስጥ

በመቶኛ ሲሰላ 28.5% የሆነ ምላሽ ይየያዛ ነው። ሶስተኛውን ደረጃ የያዘው አማራጭ (ለ) ነው። በዚህ አማራጭ ስር የቀረበውም "ከፍሉ" የሚል አማራጭ ሀሳብ ነው። ይህን አማራጭ ምላሻቸው ያደረጉ ተማሪዎችም ብዛት (21) ሲሆኑ ይህም ከአጠቃላይ ተማሪዎች ውስጥ በመቶኛ ሲሰላ 23.1% የሆነ ምላሽ ነው። የመጨረሻውና አራተኛውን ደረጃ የያዘው አማራጭ (ሀ) ነው። በዚህ አማራጭ ስር የቀረበውም "ሙሉ በሙሉ" የሚል አማራጭ ሀሳብ ነው። ይህን አማራጭ ምላሻቸው ያደረጉ ተማሪዎችም ብዛት (9) ሲሆኑ ይህም ከአጠቃላይ ተማሪዎች ውስጥ በመቶኛ ሲሰላ 9.9% የሆነ ምላሽ ነው።

ከዚህም ጥያቄ ከተማሪዎቹ ምላሽ በመነሳት በመማሪያ መጽሀፋቸው ውስጥ የሚገኙት ምንባቦች አብዛኞቹ ሳቢነት የሌላቸውና የማያነቃቁ መሆናቸውን የሚጠቁሙ ምላሾች አብላጫውን የያዙ መሆናቸውን ነው።

በጥያቄ ቁጥር (18) "የአማርኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ/ የተለያዩ ርዕሶችን በመስጠት ወይም በምትፈልገው /ጊው/ ርዕስ ላይ የድርሰት ጽህፍ ልምምድ እንድታደርግ/ጊ/ ምን ያህል ይጥራሉ?" ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ ከስጡት ምላሽ አንጻር ከአጠቃላይ ዘጠና አንድ(91) ተማሪዎች ውስጥ የመጀመሪያውን ከፍተኛ ደረጃ የያዘው አማራጭ (መ) ነው። በዚህ አማራጭ ስር የቀረበውም "አንዳንዴ" የሚል አማራጭ ሀሳብ ነው። ይህን አማራጭ ምላሻቸው ያደረጉ ተማሪዎችም ብዛት (31) ሲሆኑ ይህም ከአጠቃላይ ተማሪዎች ውስጥ በመቶኛ ሲሰላ 34.1% የሆነ ምላሽ ይየያዛ ነው። ሁለተኛውን ደረጃ የያዘው አማራጭ (ሰ) ነው። በዚህ አማራጭ ስር የቀረበውም "አይሰጡም" የሚል አማራጭ ሀሳብ ነው። ይህን አማራጭ ምላሻቸው ያደረጉ ተማሪዎችም ብዛት (28) ሲሆኑ ይህም ከአጠቃላይ ተማሪዎች ውስጥ በመቶኛ ሲሰላ 30.7% የሆነ ምላሽ ይየያዛ ነው። ሶስተኛውን ደረጃ የያዘው አማራጭ (ለ) ነው። በዚህ አማራጭ ስር የቀረበውም "አልፎ አልፎ" የሚል አማራጭ ሀሳብ ነው። ይህን አማራጭ ምላሻቸው ያደረጉ ተማሪዎችም ብዛት (19) ሲሆኑ ይህም ከአጠቃላይ ተማሪዎች ውስጥ በመቶኛ ሲሰላ20.9% የሆነ ምላሽ ነው።

የመጨረሻውና አራተኛውን ደረጃ የያዘው አማራጭ (ሀ) ነው። በዚህ አማራጭ ስር የቀረበውም "ሁል ጊዜ" የሚል አማራጭ ሀሳብ ነው። ይህን አማራጭ ምላሻቸው ያደረጉ ተማሪዎችም ብዛት (13) ሲሆኑ ይህም ከአጠቃላይ ተማሪዎች ውስጥ በመቶኛ ሲሰላ 14.3 የሆነ ምላሽ ነው። የትምህርት ዕውቀት የተደጋጋሚ ክትትልና ድርጊቶች ውጤት እንደመሆኑ መጠን መምህራን ለሚያስተምሯቸው ተማሪዎች የሚሰጧቸውን ትምህርት ምንያህል እንደተረዱና እንደያዙ ለማረጋገጥ የሚያስችል ክትትልና ግብረ መልስ የመስጠት ጥረት የዘውትር ስራ መሆን ይገባል። ከጥያቄው ምላሾች የተገኘው ግብረ መልስ መምህራኑ ይህንን ተግባር የሚፈጽሙት እየረሱ እያስታወሱ፤ ለዚህ ተግባር አንዳንድ ጊዜ የሚጥሩ መሆናቸውን የአብዛኞቹ ተጠኚ ተማሪዎች ምላሾች ይጠቁማሉ።

በመጨረሻም በጥያቄ ቁጥር (19) "የቋንቋ መምህርህ/ሽ/ በስነ-ጽሁፍና ድራማ ክበብ በማሳተፍ የተለያዩ ስነ-ጽሁፎችን እንታቀርብ/ቢ/ ከማበረታታት አንጻር?" ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ ከስጡት ምላሽ አንጻር ከአጠቃላይ ዘጠና አንድ(91) ተማሪዎች ውስጥ የመጀመሪያውን ከፍተኛ ደረጃ የያዘው አማራጭ (ሰ) ነው። በዚህ አማራጭ ስር የቀረበውም "አያበረታቱኝም" የሚል አማራጭ ሀሳብ ነው። ይህን አማራጭ ምላሻቸው ያደረጉ ተማሪዎችም ብዛት (41) ሲሆኑ ይህም ከአጠቃላይ ተማሪዎች ውስጥ በመቶኛ ሲሰላ 45.1% የሆነ ምላሽ ይየያዛ ነው። ሁለተኛውን ደረጃ የያዘው አማራጭ (መ) ነው። በዚህ አማራጭ ስር የቀረበውም "አልፎ አልፎ ያበረታቱኛል" የሚል አማራጭ ሀሳብ ነው። ይህን አማራጭ ምላሻቸው ያደረጉ ተማሪዎችም ብዛት (23) ሲሆኑ ይህም ከአጠቃላይ ተማሪዎች ውስጥ በመቶኛ ሲሰላ 25.2% የሆነ ምላሽ ይየያዛ ነው። ሶስተኛውን ደረጃ የያዘው አማራጭ (ለ) ነው። በዚህ አማራጭ ስር የቀረበውም "ብዙ ጊዜ ያበረታቱኛል" የሚል አማራጭ ሀሳብ ነው፡ ፡ ይህን አማራጭ ምላሻቸው ያደረጉ ተማሪዎችም ብዛት (17) ሲሆኑ ይህም ከአጠቃላይ ተማሪዎች ውስጥ በመቶኛ ሲሰላ 18.7% የሆነ ምላሽ ነው። የመጨረሻውና አራተኛውን ደረጃ የያዘው አማራጭ (ሀ) ነው። በዚህ አማራጭ ስር የቀረበውም "ዘወትር ያበረታቱኛል" የሚል አማራጭ ሀሳብ ነው። ይህን አማራጭ ምላሻቸው ያደረጉ ተማሪዎችም ብዛት (10) ሲሆኑ ይህም ከአጠቃላይ ተማሪዎች ውስጥ በመቶኛ ሲሰላ11% የሆነ ምላሽ ነው።

ተጠኚ ተማሪዎቹ ድርሰት ሲጽፉ ለሚፈጥሯቸው ስህተቶች በምክንያትነት ለተጠቆሙ ለመምህራን ማስተማር ዘዴና ለማስተማሪያ መሳሪያዎች ማረጋገጫነት ከቀሩቡት ጽሁፋዊ መጠይቆች ውስጥ ለአብነት ለቀረቡት ጥያቄዎች ተማሪዎቹ የሰጡትን ምላሾች ከላይ ለማሳየት ተሞክሯል። በዚህም መሰረት መማር ማስተማርን በተመለከተ መምህራን ለተማሪዎቻቸው ከመማሪያ መጽሀፍት በተጨማሪ ሌሎች አጋዥ መጽሀፍትን ከመጠቀም ይልቅ በተማሪው መጽሀፍ ላይ ብቻ መንጠልጠል፤ የተለያዩ ርዕሶችን ለተማሪዎቻቸው በመስጠት የድርሰት ጽሁፍ እንድለማመዱ ከማድረግ አንጻርና በሰጡትም ስራ ላይ ግብረ-መልስ መስጠቱ ስራ እጅግ ዝቅተኛ አሊያም የሌለ መሆኑን፤ ከክፍል ውስጥ መማር ማስተማር በተጨማሪ ተማሪዎቻቸውን በስነ-ጽሁፍና ድራማ ክበብ እንዲሳተፉ በማድረግ የተለያዩ መጣጥፎችን እየጻፉ እንዲያቀርቡና የጽህፍ ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ለማድረግ ከመጣርና ከማበረታታት አንጻር ሲታይ እጅግ ደካማ የመማር ማስተማር ተግባር ስለመሆኑ የሚጠቁሙ ምላሾች ከፍተኛውን ቁጥር ይዘዋል። እንዲሁም በማስተማሪያ መሳሪያዎች ዙሪያ ለቀረቡ መጠይቆች የአብዛኞቹ ተማሪዎች ምላሾች የሚያመለክቱት በመማሪያ መጽሀፍት ውስጥ የሚገኙት ምንባቦች ለድርሰት ጽሁፍ የማያነቃቁና ሳብነት የጎደላቸው ወይም የሌላቸው መሆኑን የሚጠቁሙ ናቸው።

በአጠቃላይ አማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩና በስልጥኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በተተኳሪው ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ ለሚፈጽሙት ስህተቶች መምህራን ከመማሪያ መጽሀፍት በተጨማሪ ሌሎች አጋዥ መጽሀፍት ባለመጠቀማቸው፤ የተለያዩ ርዕሶችን በመስጠት ድርሰት የመጻፍ ልምምድ እንዲያደርጉ የማያደርጉና ለሚፈጽሙትም ስህተቶች እርምት የማይሰጡ፤ የክሂል ብቃታቸውን ሊያሳድጉ አስተዋጽዖ ወዳለው ወደ ድራማና ስነ-ጽሁፍ ክበብ ውስጥ ተሳታፊዎች እንዲሆኑ አለማበረታታት ለተማሪዎቹ የድርሰት ውስጥ ስህተቶች መፈጸም አስተዋጽዖ ያደረገ መሆኑን የተደረሰበት ውጤት ያሳያል። ይህንን በተመለከተ Ferris (1995) እና Lee (1997) "ለተማሪዎች በተናጠልም ሆነ በቡድን ሰዋስዋዊና የይዘት ምጋቤ ምላሽ መስጠት የስህተት ምንጮችን ልቀንሱ ይችላሉ::" በማለት ይገልጻሉ።

ከምሁራኑ ሀሳብ በመነሳትም ጭምር የመምህራን ክትትልና ምጋቤ ምላሽ ማድረግ የተማሪዎችን የጽሁፍ ውስጥ ስህተትን እንደሚቀንስ ሁሉ ምጋቤ ምላሽ ያለማድረግ ደግሞ ለስህተት መጋለጥ ምክንያት የሚሆን መሆኑን መረዳት ይቻላል። ትምህርትን ለመማርም ሆነ ለማስተማር ፍላጎት የግድ አስፈላጊ ነው። ለዚህ ደግሞ ለትምህርት አቀራረብ የሚያገለግሉ መሳሪያዎች ሳቢና አናቃቂ መሆን መቻል አለባቸው። ይህ ደግሞ በዚህ ጥናት ላይ እንደተደረሰበት ከሆነ ማስተማሪያ መጽሀፍት ውስጥ የሚገኙ ምንባቦች ሳቢና ማራኪ ሆነው ያለመቅረብ እንዲሁም አጋዥ መጽሀፍት በትምህርት ቤቱ ቤተ-መጽሀፍት ውስጥ በሚፈለገው መልኩ አለመገኘት ለመማር ማስተማሩ ሂደት ተጽዕኖ የሚፈጥሩ ስለመሆናቸው ተጠቁሟል።

ከላይ በጽሁፍ ገለጻ የተደረገባቸውን ለመማር ማስተማር ዘዴዎችና ለማስተማሪያ መሳሪያዎች ሁኔታዎች የቀረቡትን የጽሁፍ-መጠይቅ ምላሾች በሚከተለው መልኩ በሰንጠረዥ ጠቅለል ተደርገው እንዲቀርቡ ለማድረግ ጥረት ተደርጓል።

በአጠቃላይ በስልጥኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎችም በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ ለሚፈጽሙት ስህተቶች የመማር ማስተማር ዘዴዎችና ማስተማሪያ መሳሪያዎች በተጽዕኖነት ሊጠቀሱ እንደሚችሉ ጥናቱ ይጠቁማል።

ሰንጠረዥ ስድስት፡- የመማር ማስተማር ዘዴዎችና የማስተማሪያ መሳሪያዎች ሁኔታዎች በተመለከተ ለቀረቡ ጥያቄዎች፤ የተሰጡ ምላሾችና የምላሾቹን ብዛት የሚያሳይ ሰንጠረዥ፡ -

| የመጠ-ይቁ ቁጥር | መጠይቅ | በአማራጮቹ መሰረት የመላሾች ብዛት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | ለ | መ | ሰ |
| 9 | የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የጽህፍ ክሂልን ለማስተማር ከተማሪው መጽሀፍ በተጨማሪ አጋዥ መጽህፍት ከመጠቀም አንጻር፡- | 21 | 37 | 17 | 16 |
| 12 | በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ከሚገኙ ምንባቦች ውስጥ ምን ያህሉ ሳቢና አናቃቂ ናቸው? | 9 | 21 | 26 | 35 |
| 18 | የአማርኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ/ የተለያዩ ርዕሶችን በመስጠት የድርሰት ጽህፍ ልምምድ እንድታደርግ/ጊ/ ምን ያህል ይጥራሉ? | 13 | 19 | 31 | 28 |
| 19 | የአማርኛ ቋንቋ መምህር በስነ-ጽሁፍና ድራማ ክበብ በማሳተፍ የተለያዩ ስነ-ጽሁፎችን እንድታቀርብ/ቢ/ ከማበረታታት አንጻር? | 10 | 1 7 | 23 | 42 |

**መግለጫ፡-** በሰንጠርገዙ ውስጥ ከ(ሀ-ሰ) የተጠቀሱት የያንዳንዱ ጥያቄዎች አማራጮች ናቸው። በአማራጮቹም ስር የተጠቀሱት ቁጥሮች ለጥያቄው አማራጩን የመረጡ ተማሪዎች ብዛት የሚያመለክቱ ናቸው።

### 4.1.4.2 የተማሪዎች ስነ-ልቦናዊ ሁኔታዎች፡-

አንድ ቋንቋ በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች ለቋንቋው አዎንታዊ አመለካከት የሚኖራቸው ከሆነ ቋንቋውን የመልመድ ፍላጎታቸው ስለምጨሚር በቋንቋው አጠቃቀም ላይ ስህተት የመፈጸም ዕድላቸው ጠባብ ሊሆን ይችላል። በአንጻሩ ለቋንቋው አሉታዊ አመለካከት የሚኖራቸው ከሆነ ቋንቋውን የመልመድ ፍላጎታቸው ስለሚቀንስ በቋንቋው አጠቃቀም ላይ ስህተት የመፈጸም ዕድላቸው ሰፊ ሊሆን ይችላል (Norish 1992፣18)። ከዚህ መረዳት የሚቻለው ተማሪዎች ለአንድ ታላሚ ቋንቋ ከሚኖራቸው ስነ-ልቦናዊ አመለካከት አንጻር በቋንቋው አጠቃቀም ሂደት ላይ አዎንታዊ አሊያም አሉታዊ የሆነ ተጽዕኖ ሊፈጥር የሚችል መሆኑን ነው።

ከላይ በቀረቡት ሀሳቦች መሰረት በስልጥኛ ቋንቋ አፍ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ ለሚፈጽሙት ስህተት በቋንቋው ላይ የሚኖራቸው አመለካከት አንዱ ተጽዕኖ ሊሆን እንደሚችል ተገምቷል። ይህንንም ግምት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ መጠይቆች ለተተኳሪ ተማሪዎች ቀርቦላቸዋል። እነዚህ መጠይቆች በተለያየ መልኩ ቀርበው ያስገኙት ውጤትም በሚከተለው መልኩ ለመተንተን ተሞክሯል። ይህንኑ ለመፈተሽ ከሚያስችሉ መጠይቆች ውስጥ በተራ ቁጥር 1፣ 2፣ 7፣ 8፣ 13፣ እና 14 የተጠቀሱት ለአብነት ተጠቃሾች ናቸው:: ለነዚህም መጠይቆች ተጠኚ ተማሪዎቹ በሰጡት ምላሽ መሰረት ለያንዳንዱ ጥያቄ ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ ለያንዳንዱ አማራጭ ምላሽ የሰጡ ተማሪዎች ብዛት ወደ አማካይ(%) በመቀየር በሚከተለው መልኩ በጽሁፋዊ ገለጻ ትንታኔ ተሰጥቶባቸዋል።

በጥያቄ ቁጥር (1) "የአማርኛ ቋንቋ መማር ያስደስትሃል/ሻል/?" ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ ከአጠቃላይ 91 ተጠያቅዎች መካከል 39ኙ ወይም በመቶኛ ሲሰላ 43% የሚሆኑ ተማሪዎች እንደሚያስደስታቸው ሲገልጹ ቀሪዎቹ 52ቱ ወይም በመቶኛ ሲሰሉ 57% የሚሆኑት እንደማያስደስታቸው የገለጹ ናቸው።

የአማርኛ ቁንቋ በሁለተኛ ቋንቋነት መማር የማያስደስታቸው ተማሪዎች መጠይቁ ከደረሳቸው ከአጠቃላዩ 91 ተማሪዎች ውስጥ ከግማሽ በላይ ውይም 57% የሚሆኑ ናቸው። እነዚህን ተማሪዎች ቋንቋውን መማር ለምን እንደማያስደስታቸው ለማጠራት የሚያስችል ጥያቄ በጥያቄ (2) ቀርቧል።

በጥያቄ ቁጥር (2) "ለጥያቄ ቁጥር (1) መልስህ/ሽ/ በአማርኛ ቋንቋ መማር አያስደስተኝም ከሆነ ለምን?" ተብለው ለጥያቄ ቁጥር (1) "አያስደስተኝም" ላሉት ጥያቄው ቀርቦላቸዋል። እንደማያስደስታቸው የገለጹት ከአጠቃላይ 91 ተማሪዎች ውስጥ 52 ሲሆኑ ለምን እንደማያስደስታቸው ከተጠየቁት ከ52ቱ ተማሪዎች ውስጥ፤ 15ቱ "ከብዙ ሰዎች ጋር ስለማልግባባበት" የሚል ምላሽ የሰጡ ሲሆኑ ይህ ቁጥር ከአጠቃላይ 52 ተማሪዎች ውስጥ በመቶኛ ሲሰላ 28.9% የሚሆኑ ናቸው። "በቋንቋው መግባባት ስለሚከብደኝ" ያሉት ደግሞ 7 ተማሪዎች ሲሆኑ ከአጠቃላይ 52 ተማሪዎች ውስጥ በመቶኛ ሲሰላ 13.4% የሚሆኑ ናቸው፡ ፡ ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ "በትምህርት ላይ ስለሚከብደኝ" የሚለውን ሀሳብ የያዘውን የመረጡት ተማሪዎች ብዛት 13 ሲሆኑ ይህም ቁጥር በመቶኛ ሲሰላ 25.3% የሆነ ነው።

በመጨረሻም ከቀረቡት አማራጮች ውሳጥ "ቋንቋውን የመማር ጥቅሙ ስለማይገባኝ" የሚለውን ሀሳብ የያዘውን የመረጡት ተማሪዎች ብዛት 17 ሲሆኑ ከአጠቃላይ 52ቱ ተማሪዎች ውሳጥ በመቶኛ ሲሰላ 32.7% የሆነ መጠን ያላቸው ናቸው።ለዚህ መጠይቅ ተጠኚዎቹ ከሰጡት ምላሽ ከፍተኛውን ቁጥር ማለትም 32.7% የሚሆነውን የያዘው አማራጭ "ሰ" የመረጡ ናቸው። እነዚህ ተማሪዎች ቋንቋውን መማራቸው ምን ጥቅም ሊያስገኝ እንደሚችል ያለመረዳታቸውን የሚያሳይ ነው። በመቀጠልም ሁለተኛውን ደረጃ

ብዛት ቁጥር የያዘው አማራጭ "ሀ" ነው። በዚህ አማራጭ የተቀመጠውም በቋንቋው ከብዙ ሰዎች ጋር ስለማይግባቡበት እንደሆነ የሚያሳይ ነው። ለዚህ ምላሻቸው መሰረታዊ እውነታው 'የሚኖሩበት ማህበራዊ ቀጠና ውስጥ ተማሪዎቹ አፍ ከፈቱበት ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብ ውጭ ሌላ ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብ የለም' ለማለት በሚያስችል ማህበራዊ ቀጠና ውስጥ የሚኖሩ መሆናቸውና የቋንቋውን መማር ጥቅም የሚሰጥ መሆኑን ያልተረዱ መሆናቸውን መረጃ ያስገኛ የጥያቄው አማራጮች ናቸው።

በጥያቄ ቁጥር (7) "ከሰዎች ጋር በአማርኛ ቋንቋ በመግባባት ሂደት ችግር ያጋጥመሃል /ምሻል? /" ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ ከአጠቃላይ 91 ተጠያቂዎች መካከል 36ቱ ወይም በመቶኛ ሲሰላ 39.6% የሚሆኑ ተማሪዎች "አዎ! ያጋጥመኛል" ሲሉ የመለሱ ሲሆን ቀሪዎቹ 55ቱ ወይም በመቶኛ ሲሰሉ 60.4% የሚሆኑት "አይ! አያጋጥመንም" ሲሉ እንደማያጋጥማቸው የገለጹ ናቸው። በመቀጠልም ለጥያቄ ቁጥር (7) ምላሻቸው "አዎ! ያጋጥመኛል" ሲሉ ለመለሱት የሚያጋጥማቸውን የችግር ምድብ የትኛው ሊሆን እንደሚችል ከጥናቱ ትኩረት ነጥብ አንጻር በጥያቄ ቁጥር (8) ለጥያቄ ቁጥር (7) መልስህ/ሽ/ "አዎ! ያጋጥመኛል" ከሆነ አብዛኛውን ጊዜ የሚያጋጥምህ/ሽ/ ችግር የትኛው ነው? በሚል ተጠይቀዋል። ይህ ጥያቄ የሚመለከታቸው ከአጠቃላይ 91 ተማሪዎች ውስጥ 36ቱን ብቻ በመሆኑ እነዚህም የሚያጋጥማቸውን ችግር ከቀረበላቸው አማራጮች ውስጥ ምላሻቸውን ሰጥተዋሉ። ከነዚህም ውስጥ አማራጭ (ሀ) ላይ የተጠቀሰውን "ቋንቋውን ባለመቻሌ ሀሳቤን በትክክል ያለመግለጽ" ሲሉ የመለሱት 10 ተማሪዎች ሲሆኑ ይህ ብዛትም በመቶኛ ሲሰላ 27.8% የሆነ ነው። አማራጭ (ለ) ላይ የተጠቀሰውን "አፍ የፈታሁበት ቋንቋ ቃላት ጣልቃ የመግባት" ሲሉ የመለሱት 15 ተማሪዎች ሲሆኑ ይህ ብዛትም በመቶኛ ሲሰላ 41.7% የሆነ ነው። አማራጭ (መ) ላይ የተጠቀሰውን "የአማርኛን ሆሄያት በተገቢ ሁኔታ መጥራት ያለመቻል" ሲሉ የመለሱት 7 ተማሪዎች ሲሆኑ ይህ ብዛትም በመቶኛ ሲሰላ 19.4% እና አማራጭ (ሰ) ላይ የተጠቀሰውን "በአማርኛ ስናገር ጓደኞቼ ስለሚያሾፉብኝ ዝምታን የመምረጥ" ሲሉ የመለሱት 4 ተማሪዎች ሲሆኑ ይህ ብዛትም በመቶኛ ሲሰላ 11.1% የሆነ ነው።

ከጥያቄው ምላሾች መረዳት የሚቻለው ከሌሎች ሰዎች ጋር በአማርኛ ቋንቋ ንግግር መግባባት ላይ ብዙም ችግር እንደማያጋጥማቸው መጠይቁ የደረሳቸው ከአጠቃላዩ ተማሪዎች ውስጥ 60.4% የሚሆኑት ያረጋገጡ መሆናቸውን ነው። ይህ ደግሞ ተማሪዎቹ በአማርኛ ቋንቋ ንግግር ከሌሎች ጋር የመግባባት ችግር የሌለባቸው መሆኑን ያሳያል።

በጥያቄ ቁጥር (13) "ከወዳጅ ዘመድ ጋር ደብዳቤ ተለዋውጣህ/ሽ/ ታውቃለህ/ቂያለሽ/?" ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ ከአጠቃላይ 91 ተጠያቂዎች መካከል 53ቱ ወይም በመቶኛ ሲሰላ 58.2% የሚሆኑት ተማሪዎች አማራጭ (ሀ) መርጠው "አዎ! ተለዋውጬ አውቃለሁ" የሚል

ሚላሽ ሲሰጡ ቀሪዎቹ 38ቱ ወይም በመቶኛ ሲሰሉ 41.8% የሆኑት ደግሞ አማራጭ (ለ) መርጠው "አይ! ተለዋውጬ አላውቅም" የሚል ሚላሽ የሰጡ ናቸው። ለዚህ ጥያቄ አማራጭ (ሀ) መርጠው "አዎ! ተለዋውጬ አውቃለሁ" የሚል ምላሽ ለሰጡት ለ53ቱ ተማሪዎች ብቻ በጥያቄ ቁጥር (14) ላይ "ለጥያቄ ቁጥር (13) መልስህ/ሽ/ "ሀ" ከሆነ አብዛኛውን ጊዜ በየትኛው ቋንቋ ትጠቀማለህ /ሚያለሽ/?" የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸዋል። ይህ ጥያቄ የሚመለከታቸው ከአጠቃላይ 91 ተማሪዎች ውስጥ 53ቱ ብቻ ለጥያቄው ከቀረቡ አማራጮች ውስጥ የየራሳቸውን ምላሽ በማክበብ ሰጥተዋል። ከነዚህም ውስጥ አማራጭ (ሀ) ላይ የተጠቀሰውን "ስልጥኛ" ሲሉ የመለሱት 33 ተማሪዎች ሲሆኑ ይህ ብዛትም ከአጠቃላይ 53 ተማሪዎች ውስጥ በመቶኛ ሲሰላ 62.2% የሆነ ነው። አማራጭ (ለ) ላይ የተጠቀሰውን "አማርኛ" ሲሉ የመለሱት 18 ተማሪዎች ሲሆኑ ይህም ከ53 ተማሪዎች ውስጥ በመቶኛ ሲሰላ 34% የሆነ ነው። አማራጭ (መ) ላይ የተጠቀሰውን "ጉራጊኛ" ሲል የመለሰው 1 ተማሪ ሲሆን ይህ ብዛትም በመቶኛ ሲሰላ 1.9% እና አማራጭ (ሰ) ላይ የተጠቀሰውን "ሀዲይኛ" ሲል የመለሰው 1 ተማሪ ሲሆን ይህ ብዛትም በመቶኛ ሲሰላ 1.9% የሆነ ነው። ከዚህ ጥያቄ ምላሾች መረዳት የሚቻለው ከወዳጅ ዘመድ ጋር ለሚያደርጉት ለደብዳቤ ልውውጥ የሚጠቀሙት ቋንቋ እንደአብዛኞቹ ምላሽ አፍ በፈቱበት ቋንቋ /በስልጥኛ/ እንደሆነ መረዳት ይቻላል። ይህም የሚያሳየው የቁንቁ ማህበራዊ ውስንነት ያለባቸው መሆኑን ነው። ይህ ደግሞ ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ በሚማረው በታላሚው ቋንቋ ደፍሮ እንዳይለማመድ "ስህተት ቢፈጠር" ብሎ ከመስጋት የመነጨ በመሆኑ

በሚያውቀውና አፍ በፈታበት ለመጻፍ ቅድሚያ ከመስጠት የመጣ እንደሆነ የሚያሳይ ነው፡ ፡ (አባሪ አስራ ስድስት ይመልከቱ)

ከላይ በተማሪዎች ስነ-ልቦናዊ ሁኔታዎች ላይ የተነሱትን መጠይቆችና ምላሾችን ጠቅለል ባለ መልኩ በሚከተለው ሰንጠረዥ ለማስቀመጥ ጥረት ተደርጓል።

ሰንጠረዥ ሰባት፡- የተማሪዎችን ስነ-ልቦናዊ ሁኔታዎች በተመለከተ የቀረቡ ጥያቄዎች፡-

| የመጠ ይቁ ቁጥር | መጠይቅ | በአማራጮቹ መሰረት የመላሾች ብዛት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | ለ | መ | ሰ |
| 1 | የአማርኛ ቋንቋ መማር ያስደስትሃል/ሻል/?<br>ሀ) አዎ! ያስደስተኛል ለ) አይ! አያስደስተኝም | 39 | 52 * | -- | -- |
| 2 | ለጥያቄ ቁጥር (1) መልስህ/ሽ/ "ለ"ከሆነ ለምን? | 15 | 7 | 13 | 17 |
| 7 | ከሰዎች ጋር በአማርኛ ቋንቋ በመግባባት ሂደት ችግር ያጋጥመሃል /ምሻል?/ ሀ) አዎ! ያጋጥመኛል ለ) አይ! አያጋጥመኝም | 36 * | 55 | -- | -- |
| 8 | ለጥያቄ ቁጥር (7) መልስህ/ሽ/ "አዎ! ያጋጥመኛል" ከሆነ አብዛኛውን ጊዜ የሚያጋጥምህ/ሽ/ ችግር የትኛው ነው? | 10 | 15 | 7 | 4 |
| 13 | ከወዳጅ ዘመድ ጋር ደብዳቤ ተለዋውጣህ/ሽ/ ታውቃለህ/ቂያለሽ/?<br>ሀ) አዎ ለ) አላውቅም | 53 * | 38 | -- | -- |
| 14 | ለጥያቄ ቁጥር (13) መልስህ/ሽ/ "ሀ" ከሆነ አብዛኛውን ጊዜ በየትኛው ቋንቋ ትጠቀማለህ/ሚያለሽ/? | 33 | 18 | 1 | 1 |

***መግለጫ፡-*** በሰንጠርገዡ ውስጥ ከ(ሀ-ሰ) የተጠቀሱት የጥያቄዎች አማራጮች ናቸው። በአማራጮቹም ስር የተጠቀሱት ቁጥሮች ለጥያቄው አማራጩን የመረጡ ተማሪዎች ብዛት የሚያመለክቱ ናቸው።

### 4.1.4.3 የውስጠ-ቋንቋ ተጽዕኖዎች፡-

ተጠኚ ተማሪዎቹ በጻፉዋቸው ድርሰቶች ውስጥ ለተፈጸሙት ስህተቶች ምንጭ ይሆናሉ ተብለው ከሚገመቱት መላምቶች መካከል የውስጠ ቋንቋ ተጽእኖ አንዱ ተጠቃሽ ነው። ከተለያዩ ተዛማጅ ጽሁፎች ለመገንዘብ እንደተቻለው ውስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ከታላሚው ቋንቋ ውስብስብነት የተነሳ ተማሪዎቹ የቋንቋውን አወቃቀር ስርዓትና አጠቃቀም በሚገባ ካለመገንዘባቸው፤ የቋንቋውን ስርዓት ከለመዱ በሁዋላ የታላሚውን ቋንቋ አጠቃላይ ህግ ጠቅላይ አድርገው ለመጠቀም ሲፈልጉ፤ ወይም የቋንቋውን ህግ አጥርቶ ሳይዙ ህጉን ተግባራዊ ለማድረግ ሲሞክሩ የሚከሰት ሰህተት ዓይነት ነው (Brown፣ 1994)::

ስለሆነም በስልጥኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የአማርኛውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ስርዓት (ህግ) በተገቢው ሁኔታ ባለመረዳት እንዲሁም ከአሁን

ቀደም ከሚያውቁት ሰዋስዋዊ ስርዓት በመነሳት በዚያው መንገድ ለመጠቀም በመሞከራቸው የሚፈጽሙት ስህተቶች በውስጠ ቋንቋ ተጽዕኖ ስር የሚመደቡ ይሆናሉ። ለዚው ዓላማ ታስበው ለተዘጋጁት መጠይቆች ተጠኚዎቹ የተለያዩ ምላሾቻቸውን ሰጥተዋል። ከነዚህም መጠይቆች ውስጥ በጥያቄ ቁጥር 10፣ 11፣ 16 እና 17 የቀረቡት ለአብነት ተጠቃሾች ናቸው። እነዚህን መጠይቆችና ተጥኚዎቹ የሰጡትን አማራጮች ብዛት በተመለከተ ከዚህ በታች ተተንንትነው ቀርበዋል። በዚህም መሰረት፡- በጥያቄ ቁጥር (10) "የአማርኛ ቋንቋን ሰዋስዋዊ ስርዓት ለይቶ ከመጠቀም አንጻር ያልህ/ያለሽ/ ብቃት ምን ይመስላል?" ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ ከአጠቃላይ 91 ተጠያቂዎች መካከል አማራጭ (ሀ) ላይ የተጠቀሰውን "እጅግ በጣም ጥሩ" ሲሉ የመለሱት 9 ተማሪዎች ሲሆኑ ይህ ብዛትም በመቶኛ ሲሰላ 9.9% የሆነ ነው። አማራጭ (ለ) ላይ የተጠቀሰውን "በጣም ጥሩ" ሲሉ የመለሱት 19 ተማሪዎች ሲሆኑ ይህ ብዛትም በመቶኛ ሲሰላ 20.9% የሆነ ነው። አማራጭ (መ) ላይ የተጠቀሰውን "ጥሩ" ሲሉ የመለሱት 28 ተማሪዎች ሲሆኑ ይህ ብዛትም በመቶኛ ሲሰላ 30.8% እና አማራጭ (ሰ) ላይ የተጠቀሰውን "ዝቅተኛ" ሲሉ የመለሱት 35 ተማሪዎች ሲሆኑ ይህ ብዛትም በመቶኛ ሲሰላ 38.4% የሆነ ነው።

በአጠቃላይ ከላይ በጥያቄ ቁጥር "10" የአማርኛ ቋንቋን ሰዋሰዋዊ ስርዓት አውቀውና ለይተው ከመጠቀም አንጻር ስላላቸው ብቃት ለቀረበው ሀሳብ ተጠኚ ተማሪዎቹ ከሰጡት ምላሽ አንጻር ዝቅተኛ ብቃት ያላቸው ስለመሆናቸው የሚያሳይ ምላሽ ከሌሎቹ ስነጻጸር ከፍተኛ ቁጥር የያዘ ነው። በዚህም መሰረት በስልጥኛ ቋንቋ አፍ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ በመጻፍ ሂደት ላይ የቋንቋው ስዋሰዋዊ ስርዓት አስቸጋሪ የሚሆንባቸው መሆኑን መረዳት ይቻላል።

በጥያቄ ቁጥር (11) "በአማርኛ ቋንቋ ጽሁፍ በምትጽፍበት/ፊበት/ ወቅት ለተለያዩ ስህተቶች እንዲትጻረግ /ጊ/ ከሚያደርጉት ምክንያቶች በአመዛኙ የሚጠቀሰው የትኛው ሊሆን ይችላል?" ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ ከአጠቃላይ 91 ተጠያቂዎች መካከል አማራጭ (ሀ) ላይ "የአማርኛ ሰዋሰው ስርዓት ውስብስብነት" ሲሉ የመለሱት 34 ተማሪዎች ሲሆኑ ይህ ብዛትም በመቶኛ ሲሰላ 37.3% የሆነ ነው። አማራጭ (ለ) ላይ የተጠቀሰውን "የአፍ መፍቻ ቋንቋ ሰዋሰው ስርዓት" ሲሉ የመለሱት 29 ተማሪዎች ሲሆኑ ይህ ብዛትም በመቶኛ ሲሰላ 31.9% የሆነ ነው። አማራጭ (መ) ላይ የተጠቀሰውን "ትኩረት ያለመስጠቴ" ሲሉ የመለሱት 17 ተማሪዎች ሲሆኑ ይህ ብዛትም በመቶኛ ሲሰላ 18.7% እና አማራጭ (ሰ) ላይ የተጠቀሰውን "የማስተማር ችግር" ሲሉ የመለሱት 11 ተማሪዎች ሲሆኑ ይህ ብዛትም በመቶኛ ሲሰላ 12.1% የሆነ ነው። ከተሰጡት አማራጭ ምላሾች መካከል ከፍተኛውን ቁጥር የያዘው አማራጭ "ሀ" ሲሆን ይህም 'በአማርኛ ቋንቋ ጽሁፍ ሂደት ለሚፈጠሩ ስህተቶች

የቋንቋው ስዋሰዋዊ ስርዓት ውስብስብነት' የሚል ሀሳብ የያዘ ነው። ሁልተኛውን ደረጃ የያዘው አማራጭ "ለ" ነው።

በዚህም አማራጭ ስር 'የአፍ መፍቻ ቋንቋ ሰዋሰዋዊ ስርዓት' የሚል ሀሳብ ነው። እነዚህ ሁለቱ ሀሳቦች በቅደምተከተል ከፍተኛ ቁጥር ባላቸው ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ጽህፍ ሂደት ለሚፈጸሙ ስህተቶች በምክንያትነት የተጠቀሱ ናቸው።

በአጠቃላይ ለጥያቄው ከተጠኚዎቹ ከተሰጡት ምላሾች በመነሳት በስልጥኛ ቋንቋ አፍ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የአማርኛ ቋንቋ ስዋሰዋዊ ስርዓት ውስብስብነትና የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ስዋሰዋዊ መዋቅር ጣልቃ ገብነት ተጽዕኖ የሚፈጥርባቸው መሆኑን መርዳት ይቻላል።

በጥያቄ ቁጥር (16) "በአማርኛ ቋንቋ ጽሁፍ ጊዜ ነጠላና ብዙ ቁጥሮችን ለይቶ ለመጠቀም ትቸገራለህ /ሪያለሽ/?" ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ ከአጠቃላይ 91 ተጠያቂዎች መካከል 54ቱ ወይም በመቶኛ ሲሰላ 59.3% የሚሆኑት ተማሪዎች አማራጭ (ሀ) መርጠው "አዎ! እቸገራለሁ" የሚል ሚላሽ ሲሰጡ ቀሪዎቹ 37ቱ ወይም በመቶኛ ሲሰሉ 40.7% የሚሆኑት ደግሞ አማራጭ (ለ) መርጠው "አይ! አልቸገርም" የሚል ሚላሽ የሰጡ ናቸው። ቀደም ሲል በድርሰት ጽሁፍ ስራቸው ከተመለከቱት ስህተቶች ውስጥ በጻፉዋቸው አረፍተ-ነገሮች ውስጥ የነበሩ የአረፍተ-ነገሮች መዋቅራዊ ስህተቶች ተጠቃሾች የነበሩ ሲሆን የባለቤትና የማሰሪያ አንቀጽ የቁጥር አለመጣጣም ስህተቶች ከፍተኛ እንደነበሩ ሁሉ ለዚህም መጠይቅ ከአጠቃላይ 91 ተማሪዎች ውስጥ 54ቱ ወይም 59.3% የሚሆኑት 'በአረፍተ-ነገሮች አወቃቀር ሂደት የነጠላና የብዙ ቁጥር ለይቶ መጠቀም ይቸግረናል' ሲሉ የገለጹበት መንገድ ተገቢ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል።

በጥያቄ ቁጥር (17) "በአማርኛ ቋንቋ አንድ አረፍተ-ነገር ለማዋቀር ውስብስብ የሚሆኑብህ/ሽ/ በአመዛኙ የትኛው ነው?" ተብለው ለተጠየቁት ጥያቄ ከአጠቃላይ 91 ተጠያቂዎች መካከል አማራጭ (ሀ) ላይ "የባለቤት፣ የተሳቢና የማሰሪያ አንቀጽ" ሲሉ የመለሱት 21 ተማሪዎች ሲሆኑ ይህ ብዛትም በመቶኛ ሲሰላ 23.1% የሆነ ነው። አማራጭ (ለ) ላይ የተጠቀሰውን "የአያያዥ ቃላትና የስርዓተ-ነጥቦች" ሲሉ የመለሱት 16 ተማሪዎች ሲሆኑ ይህ ብዛትም በመቶኛ ሲሰላ 17.6% የሆነ ነው። አማራጭ (መ) ላይ የተጠቀሰውን "የመስተዋድዶች" ሲሉ የመለሱት 19 ተማሪዎች ሲሆኑ ይህ ብዛትም በመቶኛ ሲሰላ 20.9% እና አማራጭ (ሰ) ላይ የተጠቀሰውን "ሁሉም" ሲሉ የመለሱት 35 ተማሪዎች ሲሆኑ ይህ ብዛትም በመቶኛ ሲሰላ 38.4% የሆነ ነው።

ከላይ የተጠቀሱት ጥያቄዎች ቀጥታ ተጠኚዎቹ ከታላሚው ቋንቋ ሰዋሰዋዊ ውስብስብነት የተነሳ ተማሪዎቹ የቋንቋውን አወቃቀር ስርዓትና አጠቃቀም በሚገባ ካለመገንዘባቸው፤ የቋንቋውን ስርዓት ከለመዱ በሁዋላ የታላሚውን ቋንቋ አጠቃላይ ህግ ጠቅላይ አድርገው

ለመጠቀም ሲፈልጉ፤ ወይም የቋንቋውን ህግ አጥርቶ ሳይዙ ህጉን ተግባራዊ ለማድረግ ሲሞክሩ የሚፈጥሩት ስህተት መሆን አለመሆኑን ለማጣራት የቀረቡ እንደመሆናቸው መጠን፤ የአማርኛ ቋንቋ ሰዋሰዋዊ ስርዓት ለይቶ ከመጠቀም አንጻር ያላቸው ብቃት ከተጠየቁት ከ91 ተማሪዎች ውስጥ ከአራቱ አማራጮች "ዝቅተኛ ብቃት" እንዳላቸው የገለጹት 35ቱ ወይም 38.4% የሚሆኑ ተማሪዎች ናቸው። ከስኬል አንጻር "እጅግ በጣም ጥሩ" 9 ተማሪዎች (9.9%) እና "በጣም ጥሩ" 19 ተማሪዎች (20.9%) ናቸው። ከነዚህ መላሾች መጠን ልንገነዘበው የሚገባን አብዛኞቹ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ስዋሰዋዊ ስርዓት ላይ የሚቸገሩ ስለመሆናቸው ነው። ከላይ የተገለጹትን መጠይቆችና ለመጠይቆቹ አተሰጡት ምልሾች በሚከተለው ሰንጠረዥ ጠቅለል ብለው እንዲቀርቡ ሆኗል።

ሰንጠረዥ ስምንት፡- የውስጠ-ቋንቋ ተጽዕኖ በተመለከተ የቀረቡ ጥያቄዎች፡-

| የመጠ-ይቁ ቁጥር | መጠይቅ | በአማራጮቹ መሰረት የመላሾች ብዛት | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ሀ | ለ | መ | ሰ |
| 10 | የአማርኛ ቋንቋን ሰዋሰዋዊ ስርዓት ለይቶ ከመጠቀም አንጻር ያልህ/ያለሽ/ ብቃት ምን ይመስላል? | 9 | 19 | 28 | 35 |
| 11 | በአማርኛ ቋንቋ ጽሁፍ በምትጽፍበት/ፊበት/ ወቅት ለተለያዩ ስህተቶች እንዲትዳረግ/ጊ/ ከሚያደርጉት ምክንያቶች በአመዛኙ የሚጠቀሰው የትኛው ሊሆን ይችላል? | 34 | 29 | 17 | 11 |
| 16 | በአማርኛ ቋንቋ ጽሁፍ ጊዜ ነጠላና ብዙ ቁጥሮችን ለይቶ ለመጠቀም ትቸገራለህ/ሪያለሽ/? | 54 | 37 | -- | -- |
| 17 | በአማርኛ ቋንቋ አንድ አረፍተ-ነገር ለማዋቀር ውስብስብ የሚሆኑብህ/ሽ/ በአመዛኙ የትኛው ነው? | 21 | 16 | 19 | 35 |

**መግለጫ፡-** በሰንጠርገዡ ውስጥ ከ(ሀ-ሰ) የተጠቀሱት የጥያቄዎች አማራጮች ናቸው። በአማራጮቹም ስር የተጠቀሱት ቁጥሮች ለጥያቄው አማራጩን የመረጡ ተማሪዎች ብዛት የሚያመለክቱ ናቸው።

*መመሪያ አራት*:- ከዚህ በታች ለቀረበው ጥያቄ የራስህን/ሽን/ መልስ በተሰጠህ/ሽ/ ባዶ ቦታ ላይ በመፃፍ መልስ/ሽ/::

1. በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ጽሁፍ ልምምድ ሂደት ላይ በተማሪዎች ለሚፈጸሙ ስህተቶች መንሴዔዎቹ ምን ምን ሊሆኑ ይችላሉ? መፍትሄዎቹስ?

ከመረጃ ማሰባሰቢያ መሳሪያዎች አንዱ የሆነው የጽሁፍ መጠይቅ በተለያዩ አጠያየቅ መንገዶች እንደሚቀርብ በተለያዩ ምሁራን ይነገራል። ከነዚህም መንገዶች ዝግ አጠያየቅና ክፍት አጠያየቅ ተጠቃሾች ናቸው። ዝግ አጠያየቅ የሚባለው ለጥያቄዎቹ ምላሽ ሊሆኑ የሚችሉትን ለመምረጥ የሚያስችሉ አማራጮች ተወስነው የሚሰጡበትና ለጥያቄው ከተሰጡት አማራጮች ውጭ ምላሽ ሊሰጥ የማይቻል ዓይነት አጠያየቅ ሲሆን ክፍት አጠያየቅ መንገድ ደግሞ ተጠያቂው ለጥያቄው ያልተገደበ ምላሽ ወይም ሀሳብ እንዲሰጥ ተደርጎ የሚዘጋጅ የአጠያየቅ መንገድ ነው። ለዚህ ጥናትም ይኸው ተግባራዊ ሆኗል። ከላይ ከጥያቄ ቁጥር (1) እስከ ጥያቄ ቁጥር (20) ድረስ ያለው በዝግ አቀራረብ የቀረበ ሲሆን በመመሪያ አራት በጥያቄ ቁጥር (1) የቀረበው አጠያየቅ ደግሞ በክፍት አጠያየቅ መንገድ የቀረበ ነው። ተጠኚ ተማሪዎች ከላይ በዝግ አጠያየቅ ከቀረበላቸው ውጭ 'ለተማሪዎች ጽሁፍ ላይ ስህተቶች በምክንያትነት ሊጠቀሱ ይችላል' ብለው የሚያስቡት ጉዳዮች ካሉዋቸው እንዲጠቅሱና 'መፍትሄዎቻቸው ሊሆኑ ይችላሉ' የሚሉት ሀሳብ ካላቸው እንዲጠቁሙ ታስቦ የቀረበ መጠይቅ ነው። መጠይቁ ከደረሳቸው ከ91 ተጠኚ ተማሪዎች ውስጥ ለክፍት ጥያቄው 80 ተማሪዎች የየራሳቸውን ሀሳብ ስሰጡ 11 ተማሪዎች ምላሽ ወይም ሀሳብ ሳይሰጡ አልፈዋል። ከ80 ተማሪዎቹ የተሰጡ ሀሳቦች ባንድም ይሁን በሌላ፤ የተማሪው መጽሀፍት እጥረት፤ አጋዥ መጽሀፍት በቤተ-መጽሀፍት አለመኖር፤ የተማሪዎች ፍላጎትና ተነሳሽነት ማጣት፤የመምህራን ክትትል ማነስና... ወዘተ ናቸው። መፍትሄዎቹ፡- በምክንያትነት የተጠቀሱትን ማሟላትና ተግባራዊ ማድረግ መፍትሄዎቹ ይሆናሉ በሚሉት ጭምቃሳብ ላይ የሚያጠነጥኑ ናቸው።

በአጠቃላይ የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች በድርሰት ጽሁፍ ውስጥ ለሚፈጽሙት ስህተቶችና መንስዔዎች መረጃ ለማግኘት ሲባል የቀረቡት የድርሰት መልመጃዎች ያስገኙትን መረጃዎች ለማረጋገጥ ሲባል ለተጠኚ ተማሪዎች የቀረቡት የጽሁፍ መጠይቆች፡- በስልጥኛ ቋንቋ አፍ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ፤ በታላሚው ቋንቋ ሰዋሰዋዊ ስርዓት ወይም በውስጠ-ቋንቋው ተጽዕኖ፤ በአፍ መፍቻ ቋንቋና በተማሪዎቹ ስነ-ልቦና ጫናዎች ምክንያት ተማሪዎቹ ለተለያዩ ስህተቶች ሊጋለጡ እንደሚችሉ የሚያስረዱ መረጃዎችን አስገኝቷል።

### 4.1.5 ከመምህራን ቃለ-መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ማብራሪያና ውጤት ትንተና፡-

ለመምህራን የቀረቡት የቃል-መጠይቆች፤ ስለተማሪው መጽሀፍ (ከያዘው ትምህርት ይዘት፤ የይዘቱ ሳብነትና መጣኝነት፤ ስለመርሀ-ትምህርቱ...አዘገጃጀት) ፤ ስለተማሪዎች የጽሁፍ ላይ ልምምድ ተነሳሽነትና ተማሪዎች ድርሰት ልምምድ ወቅት ለሚፈጽሙት ስህተቶች

እንደምክንያት ሊጠቀሱ ስለሚችሉት ጉዳዮች መረጃ ያስገኛሉ ተብለው የቀረቡ ቃለ-መጠይቆች በመሆናቸው ይህንን መረጃ አስገኝተዋሉ? ወይስ አላስገኙም? የሚለውን ለማረጋገጥ ለያንዳንዱ መጠይቅ ተጠያቂ መምህራን በሰጡት ምላሽ መሰረት ከቀረቡት መጠይቆች ውስጥ መጠይቅ፤ አንድ፣ አራት፣ አምስትና ሰባት ለአብነት በሚከተለው መልኩ ተተንትነው ቀርበዋል። የተገኘው ውጤትም ቃላዊ በሆነ መልኩ ትንታኔ ተሰጥቶበታል።

- ቃለ-መጠይቅ አንድ:- ተማሪዎችዎ እርስዎ ለሚያስተምሩት ትምህርት ያላቸው ተነሳሽነት ምን ይመስላል? ከክሂል ትምህርቶችስ አንጻር በየትኛው ላይ የተሻለ ተሳትፎ ያሳያሉ ብለው ያስባሉ?

መም 1. "እኔ በማስተምረው ትምህርት የተማሪዎቹ ተነሳሽነት ከማንሳቴ በፊት ተማሪዎቹ የወጡበት ማህበረሰብ የትምህርት ተደራሽነት በጣም ዝቅተኛ የነበረ ማህበረሰብ ስለመሆኑ የቀደመ የትምህርት ተደራሽነት አናሳ እንደሆነ ታሪክ ከሚያሳየው ማህበረሰብ የወጡ መሆናቸውና ከትምህርት ዕጦት አንጻር ወደ ተለያዩ ስራ መስክ መሰማራትን አማራጭ ካደረገ ማህበረሰብ የወጡ ናቸው:: ይህንን እውነታ ደግሞ ዛሬ ላይ በተማሪዎቹ ትምህርት ፍላጎት ላይ የሚናየው ነው:: ወዳነሳሀው ሀሳብ ስመለስ :- እኔ ለማስተምረሁ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ተማሪዎቹ ያላቸው ተነሳሽነት በጣም ዝቅተኛ ነው:: ለዚህም እንደ ምክንያት ሊታይ የሚችለው ተማሪዎቹ ከትምህርት ዘርፍ ውጭ ለሚፈልጉት ለአማራጭ ስራ ዘርፎች ሊጠቅማቸው እንደማይችል ማሰባቸው ነው:: ሌላው 'ካሉት ከክሂል ትምህርት ዓይነቶች በየትኛው ክሂል ትምህርት ላይ የተሻለ ተሳትፎ ያሳያሉ' ላልከኝ ከሌሎቹ አንጻር በንግግር ክሂል ትምህርት ላይ ነው ማለት ይቻላል:: ቀሪዎቹን ደግሞ በቅደም ተከተል አስቀምጥ ካልከኝ፤ ለማዳመጥ... ለማንበብና ለመጻፍ ነው::"

መም 2:- "የኔን ትምህርት ብቻ ሳልል እንደ ትምህርት ቤቱ አጠቃላይ ትምህርት ዓይነቶች ላይ ያላቸው ፍላጎት በጣም ጥቂት ተማሪዎች በስተቀር 'ሌሎቹ የነዚያ ገባ ወጣ አጃቢዎች ናቸው።' ብዬ ብል ማጋነን አይሆንም። በተለይ የአማርኛ ቋንቋን ፍላጎት ከሚያሳጣቸው የመጀመሪያው ያደርጉታል ብዬ አስባለሁ። 'ለየትኛው ትምህርት ክሂል ትኩረት ይሰጣሉ' ላልከኝ ለየትኛውም አይሰጡም። ምናልባት ለማዳመጥና ለንግግር ሊሆን ይችላል።"

መም 3፡-"ሁሉም ተማሪዎች ተነሳሽነት የላቸውም ማለት ባይቻልም ውስን ተማሪዎች ይኖራሉ። ለአብዛኞቹ ፍላጎትና ትነሳሽነት ያለመኖር ምክንያት የቀደመ የትምህርቱ ክህሎት ያለመኖር፤ በቀደመ ትምህርት ደረጃ መያዝ የነበረባቸውን ዕውቀት ያለመጨበጥ እንዲሁም ትምህርቱን በመማራቸው ሊያገኙ የሚችሉት ጥቅም እንደሌለ ስለሚያስቡም ጭምር ለትምህርቱ ያላቸው ተነሳሽነት አናሳ ነው። ከአራቱ ክሂሎች ውስጥ በአንጻራዊነት ትኩረት ሰጥተው የሚከታተሉትና የሚሳተፉት በተፈጥሮ ክሂሎች ላይ ነው ማለት ይቻላል።

ከላይ መምህራኑ በሰጡት ምላሽ መሰረት፤ መምህራኑ ለሚያስተምሩት ትምህርት ተማሪዎቻቸው ተነሳሽነትና ፍላጎት እንደሌላቸው፤ በጣም ዝቅተኛ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች ቢኖሩም ወደ ተፈጥሮ ክሂላት የሚያመዝኑ መሆናቸውን ገልጸዋል። ለዚህም እንደምክንያትነት የሚያነሱት፤ "ተማሪዎቹ የወጡበት ማህበረሰብ የትምህርት ተደራሽነት በጣም ዝቅተኛ የነበረ ማህበረሰብ ስለመሆኑ፤ የቀደመ የትምህርት ተደራሽነት አናሳ እንደሆነ ታሪክ ከሚያሳየው ማህበረሰብ የወጡ መሆናቸውና ከትምህርት ዕጦት አንጻር ወደ ተለያዩ ስራ መስክ መሰማራትን አማራጭ ካደረገ ማህበረሰብ የወጡ ናቸው:: ይህንን እውነታ ደግሞ ዛሬ ላይ በተማሪዎቹ ትምህርት ፍላጎት ላይ የሚናየው ነው::" በማለት መም.1 ሲገልጹ፤ ሌላው መም.3 "በቀደመ ትምህርት ክፍል ደረጃ መያዝ የሚገባቸውን የደረጃ ብቃት ሳይዙ ወደዚህ ትምህርት ደረጃ መምጣታቸው..." የሚሉትን ምክንያቶች በመጥቀስ የተማሪዎቹን የትምህርቱ ላይ ፍላጎትና ተነሳሽነት ማጣት ተጨባጭ በማድረግ አስረድተዋል።

➢ ቃለ-መጠይቅ ሁለት፡- ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ ስህተት ይሰራሉ? የሚሰሩ ከሆነ ምን ምን ዓይነት ስህተቶችን እንደሚሰሩና ከተደጋጋሚነት ስህተቶች አንጻር በቅደም ተከተል ቢነግሩን?

**መ/ር 1፡-** ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ ስህተቶችን ይፈጽማሉ። የሚጽሟቸው ስህተቶች፡- የፊደል ስህተት፤ ነጠላና ብዙ ቁጥርን ለይቶ ያለመግለጽ፤ የአንቱታ ቃላትን በአግባቡ ያለመጠቀም፤ የስርዓተ ነጥብ አጠቃቀም፤ የባለቤትና ማሰሪያ አንቀጽ አለማስማማት፤ በአማርኛ ቋንቋ ጽህፈት የራሳቸውን ቋንቋ ጣልቃ የማስገባትና የመጠቀም ችግሮች ናቸው።

**መ/ር 2፡-** ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ ስህተቶችን ይፈጽማሉ። የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ከፍተኛው የፊደላት መቀያየር ችግር ነው። ሁለተኛው የሥርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ችግር፤ ቀጥሎ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን በሚጽፉት የአማርኛ ቋንቋ ድርሰት መካከል እያስገቡ መጻፍ፤ የአረፍተነገር ባለቤትና ግስ አለማጣጣም፤ የሳልስና ሳድስ ፊደላት አጠቃቀም ችግሮች ይጠቀሳሉ።

**መ/ር 3፡-** "በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ ተማሪዎች ብዙ ስህቶችን ይሰራሉ። ከነዚህም ውስጥ፡- በቅርጻቸው ለመለየት አስቸጋሪ የሆኑ ፊደላትን የመጻፍ፤ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ቃላት መጠቀም፤ የአረፍተ-ነገሮችን ሰዋሰዋዊ መዋቅር ማፋለስና ስርዓተ-ነጥቦችን አውቀውና ቦታቸውን ለይተው ያለመጠቀም ችግሮችን መፈጸም ተጠቃሾች ናቸው።"

➢ ቃለ-መጠይቅ ሶስት:- እርስዎ በሚያስተምሩበት የዘጠነኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የቀረቡት ይዘቶችና መልመጃዎች ካሉት የቋንቋ ክህሎች መካከል ተማሪዎች የትኞቹን የበለጠ እንዲያዳብሩ የሚያስችል ይመስለዎታል?

**መ/ር 1፡-** "*መጽሀፉ ካለው ይዘትና መልመጃ አንጻር ሲታይ ተማሪዎች እንዲያዳብሩት ተፈልጎ የተዘጋጀው የንግግርና የንባብ ክህላቸው ላይ ያተኮረ ቢሆንም ለአተገባበሩ በቂ ጊዜ የሰጠ ግን አይደለም።*"

**መ/ር 2፡-** "*መጽሀፉ ሁሉንም ለማካተት የሞከረ ቢሆንም የይዘቶቹ አቀራረብ ሳቢና አናቃቂ አለመሆን እንዲሁም ለክትትልና ግብረ-መልስ የሚሆን ጊዜ ያልሰጠ ነው። ይህ ሁኔታ ደግሞ በጽሁፍ ክሂል ላይ የበለጠ ተጽዕኖ ይፈጥራል ብዬ አምናለሁ።ከትምህርት ይዘቶቹ አቀራረብ አንጻር ተማሪዎች እንዲወያዩና እንዲናገሩ በማድረግ ማቅረብን የሚያበረታታ በመሆኑ ወደ ንግግር ክሂል የሚያደላ ሆኖ ይታየኛል።*

**መ/ር 3፡-** "*መጽሀፉ ተማሪዎችን የንግግር እና የንባብ ክህላቸው እንዲዳብር ተደርጎ የተዘጋጀ ነው።*

- *ቃለ-መጠይቅ አራት*:- *ለዘጠነኛ ክፍል የተዘጋጀው የመማሪያ መጽሀፍ ተማሪዎች ድርሰት እንዲለማመዱ የማስቻል ዝግጅቱ ምን ያህል ነው ይላሉ?*

*መም*. 1. "*መጽሀፉ ተማሪዎች ድርሰት እንዲጽፉ የሚያበረታታበት ሁኔታ አይታየኝም። ምክንያቱም የድርሰት ልምምድ እንዲያደርጉ ከተፈለገ አነቃቂ የሆኑና የተማሪዎቹን ፍላጎት ያማከሉ ምንባቦች አብረው መቅረብ ነበረባቸው። ይህ አለመሆን ደግሞ በተለይ በንባብና በጽሁፍ ክሂል ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽዕኖ እየፈጠረ ያለ ጉዳይ ነው።*"

*መም*. 2. "*የመማሪያ መጽሀፉ የተወሰኑ የቃላትና ሀረጋት አልፎ አልፎ የአረፍተነገሮች ምላሽን የሚሹ ጥያቄዎችን ከመያዙ ባለፈ ድርሰት እንዲጽፉ የሚያዘው በጣም ጥቂት ቦታ ስለሆነ ይህ ድርሰት ጽሁፍን ያበረታታል ለማለት አያስደፍርም።*"

*መም*. 3. "*መጽሀፉ ስለድርሰት ጽሁፍ የሚያወራው በጣም ውስን ጊዜ ቢበዛ በአመቱ የትምህርት አጠቃላይ ይዘት ውስጥ ሁለት ጊዜ ብቻ ነው። ይህ የድርሰት ጽሁፍ ትምህርትን አያበረታታም።*" *መጠይቅ አራት የተማሪዎቹ መማሪያ መጽሀፍ የተማሪዎችን የድርሰት መለማመድን ከማበረታታት አንጻር የተጠየቁበት ነው። ለዚህም መጠየቅ የሰጡት ምላሽ፡- በመጽሀፉ ውስጥ የሚገኙት ይዘቶች የተማሪዎችን የጽሁፍ ክሂል ለደረጃው የሚያበቁ ሆነው ያልቀረቡ፤ የቀረቡት ምንባቦቹም ቢሆኑ ሳቢና አናቃቂ ያልሆኑ፤ መልመጃዎቹም ቢሆኑ ስለድርሰት ጽሁፍ የሚያዘው በጣም ጥቂት ቦታ መሆኑና ተደጋጋሚነት የጎደለው እንደሆነ በመጥቀስ በቃለ-መጠይቅ አንድ ላይ ለተሰጠው የተማሪዎች ተነሳሽነትና ፍላጎት ማጣትም ይኸው በምክንያትነት ሊጠቀስ ችላል ሲሉ ሶስቱም መመህራን በሚባል ደረጃ ምላሻቸውን ሰጥተዋል።*

*በመሆኑም የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በ*2015 *ዓ/ም በመማሪያነት እየተገለገሉበት ያለው መማሪያ መጽሀፍ የተማሪዎችን የጽሁፍ ክሂል የማያበረታታ እንደሆነ መገንዘብ ይቻላል።*

➢ *ቃለ-መጠይቅ አምስት፡- እርስዎ ተማሪዎችዎን ድርሰት እንዲለማመዱ ለማስቻል ያለዎት ተነሳሽነትና ትኩረት ምን ያህል ነው ይላሉ?*

*መም*. 1. " '*ጽድቁ ቀርቶብኝ በወጉ ኮንነኝ*...' *ነው አይደለ የሚባለው? ምን ልልህ ፈልጌ ነው፤ ቀድሞ ነገር ከታችኛው ክፍል ደረጃ የሚጠበቅባቸውን፡- የፊደል ልየታ፤ የቃላት ምስረታ፤ የአረፍተ-ነገሮች አወቃቀር … ወዘት ይዘው ያልመጡትን ተማሪዎች ስለድርሰት አጻጻፍ ማስተማርና ድርሰት ጻፉ ማለት በራሱ የሚከብድ ይሆናል። እርስዎ ተማሪዎችዎን ድርሰት እንዲለማመዱ ለማስቻል ያለዎት ተነሳሽነትና ትኩረት ምን ያህል ነው? ላልከው፤ መጽሀፉ አንዳንድ ቦታዎች ላይ ድርሰት እንዲጽፉ ያዛል። ነገር ግን ለትምህርቱ እየተሰጠ ያለው ሳምንታዊ ክፍለ-ጊዜ መጠን ሁለትና ዕለታዊ ቆይታውም* 40' *ደቂቃ መሆኑ፤ የትምህርት ቤት የስራ ቆይታ ሰዓትም ለመቀነስ ሲባል ከዚያው ከአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ-ጊዜ ላይ የሚቀነስ መሆኑ፤ እንዲሁም ለተለያዩ ደራሽ ስራዎችና ለልዩ ፕሮግሮሞች ያለችው ክፍለ-ጊዜ ስለምትሸራረፍ ተማሪዎቹን ለማለማመድ የሚያችል ጊዜ አይኖርም። ነገር ግን ባለችውም ጊዜ እንድለማመዱ ጥረት ይደረጋል።*

*መም*. 2. *ተነሳሽነቱ ቢኖርም የተፈለገውን ያህል ለማከናወን ተማሪዎቹ ወደዚህ ትምህርት ደረጃ ይዘውት የመጡት የብቃት ደረጃ በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ አሁን ላሉበት ደረጃ ለማብቃት ከፍተኛ ስራ ይጠይቃል። በዚህ ላይ የተማሪዎቹ የትምህርት ፍላጎት አናሳ መሆን ለተግባሩ የሚኖርህን ተነሳሽነትና ዝግጁነት በእጅጉ ይቀንሳል።*

*መም*. 3. *ጥረት ይደረጋል፤ ነገር ግን ጥረት የሚደረግበት አግባብና መንገድ የተማሪዎቹን የጽሁፍ ክሂል በአግባቡ የሚፈትሽ አይደለም። ምክንያቱም ለትምህርቱ ከተሰጠው የትምህርት ክፍለ-ጊዜ መጠን አንጻር ክንውኑን በክፍል ውስጥ ብቻ ለማጠናቀቅ ስለማያስችል ቤት ወሰድ እንዲያደርጉ ስለሚደረግ በተማሪዎቹ የተጻፈ ይሁን በሌላ አካል ስለማይታወቅ ተዓማንነቱ የጎደለ ስራ ይሆናልና።*

ከላይ በቀረበው ቃለ-መጠይቅ መምህራን ተማሪዎቻቸውን የድርሰት ጽሁፍ ከማለማመድ አንጻር ያላቸውን ተነሳሽነትና ጥረት ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ ለቀረበው ቃለ-መጠይቅ ከሰጡት ምላሽ መረዳት የሚቻለው፤ ባንድም ሆነ በሌላ ሶስቱም መምህራን ለተማሪዎቻቸው ለድርሰት ለምምድ ያላቸው ቁርጠኝነትና ተነሳሽነት የሌላቸው ወይም ውስን መሆኑን ሲሆን ለዚህም የተማሪዎቹ የቀደም ዕውቀት ከሚጠበቀው እጅግ በጣም ዝቅተኛ መሆን፤ የመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ይዘቶችና ለይዛቶቹ አተገባበር የተሰጠው ጊዜና ከመንግስት በኩልም ለቋንቋው የተሰጠው አናሳ ትኩረት ተደማምረው ተማሪዎቹን የድርሰት ክሂል መልመጃዎችን በተነሳሽነትና በትኩረት እንደማያለማምዱቸው መረዳት ይቻላል።

➢ *ቃለ-መጠይቅ ስድስት:- ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ ስህተት የሚፍጽሙ ከሆነ የስህተቶቻቸው ምንጮች ምን ምን ይመስለዎታል? ቢነግሩን?*

***መ/ር 1፡-*** *ተማሪዎች የድርሰት ጽህፈት ስህተት ምንጭ የሚሆናቸው የስልጥኛ ቋንቋ ተጽዕኖ ይጎላል ብዬ አስባለሁ። ተማሪዎቹ ለአጠቃላይ ትምህርት ዓይነቶች ግድ-የለሽ ናቸው። ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት*

*ደግሞ የበለጠ ነው። በአጠቃላይ ለትምህርቱ ተነሳሽ ባለመሆናቸው በቋንቋው በሚለማመዱት በድርሰት ጽሁፍ ጊዜ ከተተኳሪው ቋንቋ መዋቅራዊ ስርዓት ይወጡና የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን መዋቅራዊ ስርዓት ይቀላቅሉበታል። በዚህን ጊዜ ለስህተት ይጋለጣሉ።*

***መ/ር 2፡-*** *ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰትን በሚጽፉበት ወቅት ስህተት እንዲሰሩ የሚያደርጋቸው፤ ለትምህርቱ ያላቸው ፍላጎት አናሳ መሆንና ተነሳሽነት ማጣት፤ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጣልቃ ገብነት (አብዛኞቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ቃላት ከተተኳሪው ቋንቋ ቃላት ጋር ተቀራራቢ በመሆናቸው ሳያስቡት*

*በተተኳሪው ቋንቋ አጠቃቀም ሂደት ላይ ጣልቃ ያስገቡበታል።) ሌላው የተተኳሪውን ቋንቋ ሰዋሰዋዊ ስርዓት አጥርተው ካለማወቅ የሚመነጩ ጉድለቶች በታላሚው ቋንቋ በሚለማመዱት በድርሰት ጽሁፍ ውስጥ የተለያዩ ስህተቶችን እንዲፈጽሙ ምክንያቶች ሊሆኑ ይችላሉ።*

***መ/ር 3፡-*** *ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ ስህተት ይፈጽማሉ። እንዲፍጽሙ የሚያደርጋቸው ምክንያት፡-የቋንቋውን ስርዓታዊ መዋቅር አለመቻላቸው፤ በቋንቋው ማስተማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የሚገኙት የትምህርት ይዘቶችና የአቀራረብ ዘዴዎቹ ሳቢና አናቃቂ ያለመሆን፤ አፍ የፈቱበት የስልጥኛ ቋንቋ በንግግራቸውም ይሁን በጽሀፉቸው ጣልቃ መግባት… ወዘተ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ ስህተት እንዲፈጽሙና የፈለጉትን ሀሳብ በጽሁፍ እንዳያስተላልፉ ያደርጋቸዋል። በአጠቃላይ ተማሪዎቹ በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ ለስህተት የሚዳርጋቸው የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ተጽዕኖ፤ የታላሚውን ቋንቋ መዋቅራዊ ስርዓት አውቀውና ለይተው ካለመጠቀም፤ የሚኖሩበት አካባቢ በአንድ ቋንቋ ተናጋሪ ማህበረሰብ የታጠረ መሆንና ከትምህርት ቤት ውጭ ለቋንቋው ተጋላጭ የሚሆኑበት 'እንቫይሮሚንት' ያለመኖር፤ እንዲሁም ለቋንቋው ትምህርት ትኩረት ሰጥተው ያለመማር ሌላው ለስህተት ከሚዳርጋቸው ውስጥ ተጠቃሾች ይሆናሉ።*

- *ቃለ-መጠይቅ ሰባት፡- በስልጥኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩት የአማርኛ ቋንቋ የጽሁፍ ክሂላቸው እንዲያዳብር ምን መደረግ አለበት ይላሉ?*

*መም. 1. ለትምህርት አይነቱ ከመንግስት በኩል ያለው አናሳ ግምት መቀረፍ አለበት። ለአማርኛ ቋንቋ ብቻም ሳይሆን በየትምህርት ቤቶች ለቋንቋዎች የሚሰጡ የክፍለ-ጊዜያት ብዛት በጣም አናሳ መሆናቸው ቀርቶ ከሁሉም ትምህርት ዓይነቶች ዕኩል ሳምንታዊ ክፍለ-ጊዜያት ስርጭት ቢደረግ፤ የመማሪያ መጽሀፍት ክህሎችን ተገቢ በሆነ መልኩ ማስተማር*

እንዲችሉ ተደርገው መዘጋጀትና ተማሪዎቹ ቋንቋውን/ዎቹን/ በመማራቸው የሚያገኙት ጥቅም አጓጊ እንዲሆን ማስቻል ከተቻለ ተማሪውም ለትምህርት ዓይነቱ ትኩረት ሰጥቶ ይከታተላል፤ ይህን አደረገ ማለት ደግሞ በክሂሎች ላይ ብቁ የመሆን ዕድሉ ሰፊ ይሆናል ብዬ አስባለሁ።

መም. 2. በመጀመሪያ ተማሪዎች ለትምህርት አይነቱ ያላቸው ዝቅተኛ አመለካከት እንዲቀየር ማስቻል፤ መንግስት እንደሌሎቹ ትምህርት ዓይነቶች ሁሉ ትኩረት ሊሰጥ ይገባል። በ12ኛ የ'እንተራንስ' ፈተና እንዲሰጥ ማድረግ፤ የትምህርት ይዘቶቹም ሳቢና አናቃቂ ሆነው ለይዘቶቹ ማጠናቀቂያ የሚሆኑ በቂ የሳምንታዊ ክፍለ-ጊዜ ብዛትና የዕለታዊ ቆይታ ጊዜ በቂ ሊሆኑ ይገባል። ቋንቋው ብሄራዊ ቋንቋ እንድመሆኑ መጠን በሁሉም ቦታ ተገቢውን ትኩረት መስጠትና በቋንቋውም መማር ተገቢውን ጥቅም የሚያስገኝ መሆን አለበት።

መም. 3. በትምህርት ዓይነቱ ተማሪዎች የተሻለ ውጤት እንዲያመጡ በትምህርቱ መማር አስፍላጊነት ላይ አምነው መቀበል መቻል አለባቸው። ለዚህም ለሀገር አቀፍ ፈተና ተካታች መሆን ማለትም የ"እንተራንስ" ፍተና እንዲሰጥ ማዲረግ፤ በየትምህርት ቤቱ ለትምህርቱ የሚሰጠው የክፍለ ጊዜ መጠን በቂ መሆን መቻል እና መርሀ-ትምህርቱንና የመማሪያ መጽሀፉን ከተማሪዎቹ ዕድሜና ፍላጎት ጋር የተገናዘበ ሆኖ ተሻሽሎ የሚቀርብበት ሁኔታ ብመቻች ለጽሁፍ ክሂላቸው ብቻም ሳይሆን ለሌሎች ክሂሎችና ዕውቀት ዘርፎችም ጭምር አስተዋጽዖ ያደርጋል ብዬ አስባለሁ።

ለቃለ-መጠይቅ ሰባት መምህራኑ ከሰጡት ምላሽ መረዳት የሚቻለው፤ በስልጥኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሙትን ስህተቶች ቀርፈው አሊያም ቀንሰው ክሂሉን እንዲያዳብሩ፤ የማስተማሪያ መጽሀፍት የትምህርት ይዘቶቻቸው ሳቢና አናቃቂ መሆን፤ መንግስት በቋንቋው ትምህርት ላይ ትኩረት መስጠት፤ የቋንቋው ትምህርት አጓጊ ጥቅም ማስገኘት መቻል የተማሪዎች የጽሁፍ ክሂል ሊያዳብር እንደሚችል ነው። (አባሪ አስራ ሰባት ይመልከቱ)

በአጠቃላይ 'ለተጠኚ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ ለሚፈጽሙት ስህተቶች በምንጭነት ሊጠቀሱ ይችላሉ' ተብለው የተገመቱትና በውስጠ-ቋንቋ ስር የሆኑ የስህተት ምንጮች ስርጭት የሆኑትን፡- የመማር ማስተማር ዘዴዎችን፤ የማስተማሪያ መሳሪያዎችን እንዲሁም የተማሪዎችን ፍላጎትና ስነ-ልቦና በትክክልም ለስህተቶቹ በምንጭነት ይጠቀሳሉ? ወይስ አይጠቀሱም? የሚለውን ለማጣራት ለመምህራን በቀረበው ቃለ-መጠይቅ መሰረት ለተጠኚ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ ለሚፈጽሙት ስህተቶች ቀጥታ አስተዋጽዖ ያደረጉ ስለመሆናቸው ቃለ-መጠይቁ ከቀረበላቸው መምህራን ከተገኘው መረጃ መረዳት ተችሏል።

# ምዕራፍ አምስት

## 5.1 ማጠቃለያ፣መደምደሚያና የመፍትሄ ሃሳብ

በዚህ ምዕራፍ ስር የጥናቱ ግኝትና ተዛማጅ አስተያየቶች በቅደም ተከተል ቀርበዋል፡፡

### 5.1.1 ማጠቃለያ

ይህ ጥናት ትኩረቱ በስልጤ ዞን በምዕራብ አዘርነት በርበሬ ወረዳ በሌራ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሚገኙ በስልጥኛ ቋንቋ አፋቸውን በፈቱ በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ነው:: ጥናቱ ሁለት መሰረታዊ ጥያቄዎችን ለመመለስ የተካሄደ ነው:: ጥያቄዎቹም፡- ተተኳሪዎቹ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው የስህተት ዓይነቶች የትኞቹ ናቸው? የስህተት ምንጫቸውስ ምን ሊሆን ይችላል? የተሰኙ ናቸው፡፡ ጥናቱ ከነዚህ መሰረታዊ ጥያቄዎች ውስጥ መነሻውን ተጠኚ ተማሪዎቹ የፈጸሟቸው ስህተቶች ምን ዓይነት ናቸው? የሚለውን አድርጓል፡፡ በመቀጠልም ለፈጸሟቸው ስህተቶች የስህተት ምንጮቹ ሊሆኑ የቻሉት ጉዳዮች ምን ምን ሊሆኑ ይችላሉ? የሚለውን በመፈተሽና ትንታኔ በመስጠት የተነሳበትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ ጥረት አድርጓል፡፡ እነዚህንም በሚከተለው መልኩ በየፈርጃቸው በማስቀመጥ ማጠቃለያ ለመስጠት ተሞክሯል፡፡

**ሀ. በተማሪዎቹ የተፈጸሙ አበይት የስህተት ዓይነቶች፡-**

ጥናቱ በተጠቀመበት ስላት መሰረት የስህተት ዓይነቶች ከብዛት አንፃር ሲመደቡ፤ በቋንቋ አጠቃቀም የተከሰቱ ስህተቶች፣ በቋንቋ አውቃቀር የተከሰቱ ስህተቶች፣ በስርዓተ-ነጥቦች አጠቃቀምና መለየት የልተቻሉ ስህተቶች በቅደም ተከተል ከአንደኛ እስከ አራተኛ ደረጃ ቦታ የያዙ ናቸው: ከነዚህም ውስጥ ከአንደኛ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ላይ የተጠቀሱት አበይት የስህተት ዓይነቶች ናቸው፡፡

በአጠቃላይ ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎች በድርሰቶቹ፣ በጽህፍና በቃል መጠይቆቹ አማካይነት ተሰብስበው አስፈላጊው ትንተና ከተካሄደ በኋላ ከዚህ በታች የተገለጹት ውጤቶች ተገኝተዋል:

- በቋንቋ አጠቃቀም አቢይ ስህተት ምድብ ስር ስድስት ዓይነት ንዑሳን የስህተት ስርጭቶች ተመዝግበዋል፡፡ እነሱም፡- የሆሂያት አጻጻፍ ስህተት፣ የሳድስና የሳልስ አጻጻፍ ስህተት፣ የሆሄያት ጭመራና ግድፈት ስህተት፣ አላስፈላጊ መዋቅሮች ስህተት፣ የቃላት ምርጫና የስልጥኛ ቃላት መጠቀም ስህተቶች ናቸው፡፡ ይህ የስህተት ምድብ ከተጠቀሱት ስህተት ምድቦች ተመሪዎቹ በድርሰት መለማመጃቸው ስራ ላይ ከፈጸሟቸው ከአጠቃላይ 4558 ስህተቶች ውስጥ 80% ያህሉን የሸፈነ ነው፡፡
- በቋንቋ አወቃቀር አቢይ የሰህተት ምድብ ስር ደግሞ ሶስት ንዑሳን ስህተት ምድቦች

ተመዝግበዋል። እነሱም፡- የአረፍተ-ነገሮች ስኬት ስህተት፣ መዋቅራዊ አገባብ ስህተትና የአያያዥ ቃላት አገባብና አጠቃቀም ስህተት ናቸው።

**ለ. የስህተት ምንጮች**

በስልጥኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የስልጤ ዞን አዘርነት በርበሬ ወረዳ የሌራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ ለፈጸሟቸው ስህተቶች በምንጭነት የታለሙት፤ የአፍ መፍቻ ቋንቋ፣ የውስጠ ቋንቋ፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎች፣ የማስተማሪያ ዘዴዎችና የተማሪዎች ስነ-ልቦናዊ ተጽዕኖዎች ናቸው፡፡

ተማሪዎቹ በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሆሂያትን ቅርጽ ለይተውና ተነባቢ አድርገው ያለመጻፍ ችግር፣ ሳድስና ሳልስ ፊደላትን ያለመለያትና ለይተው ያለመጠቀም ችግር፣ በቃላት ውስጥ አላስፈላጊ የሆኑ ሆሂያትን የመጨመርና አስፈላጊ የሆኑትን ደግሞ የመግደፍ ችግር፣ አላስፈላጊ ድግግሞሽ ችግሮች፣ የቃላት ምርጫና የስልጥኛ ቃላት መጠቀም ችግሮች በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ የተፈጸሙ ስህተቶች ሊሆኑ እንደሚችሉ ተገምቷል። ከቋንቋ አወቃቀር ስህተቶች (የታላሚውን ቋንቋ ስርዓታዊ መዋቅር በወጉ ካለመረዳትና የቀደመ ቋንቋ መዋቅር ጠቅላይ አድርገው ለመጠቀም ከመሞከር አንጻር)፤ የአረፍተ-ነገሮች ስኬት ስህተት (መዋቅራዊ አገባብ፤ ባንድ ዓረፍተ-ነገር ውስጥ የንዑሳን ሀረጎች አገባብ፣ ከመስተዋድድ፣ ከባለቤትና ከማሰሪያ አንቀጽ አለማዋደድ፣ የመደብና የጾታ፣ የቁጥርና የተለያዩ አጸፋዎችን አመልካች ቅጥያዎች አጠቃቀም ችግሮች)፣ የአያያዥ ቃላት አገባብና አጠቃቀም ችግሮች በዚው በቋንቋ አወቃቀር ስህተት ምድብ ስር ተጽዕኖ የተፈጸሙ ስህተቶች ሊሆኑ እንደሚችሉ ተገምቷል።

ይሁን እንጂ በዚህ ምድብ ስር ከተፈጠሩ ስህተቶች ውስጥ ባንድ መዋቅር ውስጥ መስተዋድዳዊና ተሳቢ አጸፋዎች እንዲሁም በሁለተኛ ቋንቋ መዋቅራዊ ውስብስብነት ምክንያት ሊፈጠሩ ይችላሉ ተብለው ከሚገመቱት ውስጥ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖም ሊፈጸሙ የሚችሉት እንዳሉ መገመት የተቻለ ቢሆንም ተጨማሪ ጥልቅ ጥናት የሚያስፈልገው እንደሆነ ታምኗል።

ተጠኚ ተማሪዎቹ ለፈጸሟቸው ለተለያዩ ስህተቶች በምንጭነት ሊጠቀሱ የሚችሉት፤ የአፍ መፍቻ ቋንቋና የታላሚው ቋንቋ መዋቅራዊ ስርዓት ውስብስብነት ብቻ ሳይሆኑ የመማር ማስተማር ዘዴዎች፣ የማስተማሪያ መሳሪያዎችና የተማሪዎች የትምህርት ፍላጎትና ተነሳሽነት መጣት ጭምር በምንጭነት ሊጠቀሱ እንደሚችሉ ከተማሪዎች ጽሁፍ መጠይቅና ከመምህራን ቃለ-መጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ለዚህም ማረጋገጫ ሊሆኑ የሚችሉት መምህራን ለተማሪዎች የድርሰት መልመጃዎችን በተደጋጋሚ በመስጠት የመከታተልና ግብረ- መልስ የመስጠት ስራ እንደማይሰሩ ከመምህራንም ከተማሪዎችም ከተሰበሰቡ መረጃዎች ለማግኘት ተችሏል። የዚህንም ተጽዕኖ በተማሪዎቹ ድርሰት ስራ

ውስጥ ለማረጋገጥ ተችሏል። ለምሳሌ ያህል፤ የስርዓተ-ነጥቦች አጠቃቀም ጉድለት፤ የዓረፍተ-ነገሮች አወቃቀርና በውስጣቸው ስለሚገኙ ተዋቃሪዎች አገባብ ለይተው ያለመጠቀምና ሌሎችም ጉድለቶች በመምህራን መማር ማስተማር ሂደት ላይ በሚታዩ ጉድለቶች እንደሆኑ መረዳት ይቻላል። በሌላ መልኩ የማስተማሪያ መሳሪያዎች በይዘታቸውና አቀራረባቸው ሳቢና አናቃቂ ባለመሆናቸው በቋንቋው ክሂል ትምህርት ላይ ተማሪዎቹ ሊኖራቸው የሚገባውን ፍላጎትና ተነሳሽነት እንዲያጡ እንዳስቻላቸው፤ በዚህ ዓይነት ስነ-ልቦና ውስጥ ሆነው በሚለማመዱት ድርሰት ውስጥ የተለያዩ ስህተቶችን ሊፈጽሙ እንደቻሉ የጥናቱ ውጤት አሳይቷል። ለዚህና መሰል ስህተቶች የመማር ማስተማር ዘዴዎች ድክመትና የማስተማሪያ መሳሪያዎች አዘገጃጀት ሳቢና አናቃቂ ያለመሆን በምክንያትነት ተጠቃሾች ናቸው።

በአጠቃላይ የዚህ ጥናት ውጤት የሚያሳየው በሌራ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በስልጥኛ ቋንቋ አፍ-ፈት ተጠኚ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የተለያዩ ስህተቶችን፤ ከቋንቋ አጠቃቀም፣ ከቋንቋ አወቃቀር፣ ከስርዓተ-ነጥቦችና ለመለያት ያልተቻሉ ስህተት ምድቦች ስር ፈጽመዋል። ለዚህም፤ የአፍ መፍቻ ቋንቋ፣የውስጠ-ቋንቋ (የሁለተኛ ቋንቋ ሰዋሰዋዊ መዋቅር በቀደመ ቋንቋ መዋቅር ለመጠቀም መሞከር)፣ የመማር ማስተማርና ማስተማሪያ መሳሪያዎች እንዲሁም የተማሪዎቹ ስነ-ልቦናዊ ሁኔታዎች ተጽዕኖ አማካይነት የተፈጠሩ ስለመሆናቸው ከተማሪዎችና መምህራን ከተሰበሰቡ መረጃዎች ትንተና የተገኘው ውጤት ያመለክታል።

### 5.1.2 መደምደሚያ

ይህ ጥናት ከተነሳበት ዓላማ አንጻር የሌራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በስልጥኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎችን የድርሰት ውስጥ ስህተቶችንና ዓይነታቸውን እንዲሁም ለድርሰት ውስጥ ስህተቶቻቸው አስተዋጽዖ ያደረጉትን ጉዳዮች ፍትሿል። ለዚህም የሚሆኑ መረጃዎች በተለያዩ መንገዶች ተሰብስበው ተተንትነዋል። ከተደረጉት ትንተናዎችና ከተገኙት ውጤቶች በመነሳት የሚከተለው መደምደሚያ ተሰጥቷል። የጥናቱ ተተኳሪዎች አሁን ካሉበት ከትምህርት ደረጃ አንጻር ለደረጃቸው የሚመጥን የትምህርት ክሂል ይኖራቸዋል ተብሎ ይገመታል። በጽሁፍ ክሂልም የሚጠበቅባቸውን ጽሁፍ ይጽፋሉ ተብሎ ይጠበቃል። ነገር ግን ጥናቱ ትኩረት ባደረገበት ትምህርት ቤት በስልጥኛ ቋንቋ አፍ-ፈት የሆኑ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ ለደረጃቸው የሚመጥን ጽሁፍ መጻፍ ያልቻሉ መሆናቸውንና ጽሁፋቸው ከስህተት የጸዳ ሆኖ አለመገኘቱን ይህ ጥናት ደርሶበታል። ለዛሬው ለጽሁፍ ደረጃ ላለመብቃታቸው ከታችኛው ትምህርት ክፍል ደረጃዎች ላይ ለደረጃቸው የሚመጥን ብቃት ይዘው ያለመምጣታቸው የበለጠ ተጋላጭ እንዳደረጋቸው ከተሰበሰቡ መረጃዎች የተገኙ ውጤቶች ያሳያሉ።

### 5.1.3 የመፍትሄ ሀሳብ

የጥናቱን ውጤት መሰረት በማድረግ ወደ ፊት ምን መደረግ እንዳለበትና እንዴት መሰራትእንዳለበት አጥኚው የመፍትሄ ሀሳቦች ያላቸውን በሚከተለው መልኩ ጥቆማ ሰጥቷል።

1. በተጠኚ ተማሪዎቹ ከተፈጸሙት ስህተት ዓይነቶች በስፋት የታየው የስህተት ዓይነት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ሳቢያ የተከሰቱ ስህተቶች እንደመሆናቸው መጠን፤ ይህንን ለመቅረፍ የሚያስችል የመማር ማስተማር ሂደቱን ከታችኛው እስከ ላይኛው ክፍል ደረጃ በብቃት ሊውጡ የሚችሉ መምህራንን በብቃት ማልማት፤ የመማሪያ መጽሀፍትና መርሀ-ትምህርት አዘገጃጀት የተማሪውን ዳራ፣ የማህበረሰቡን ዕሴት ያገናዘበና ሳቢና አናቃቂ መሆን፣ ለትምህርት ይዛቱ በቂ የትምህርት ጊዜ የሰጡ ሆነው ቢዘጋጁ የተማሪዎቹን የጽሁፍ ክሂል በየደረጃው ማግኘት የሚገባቸውን ብቃት ከዛሬው በተሻለ መልኩ ከፍ ሊያደርግላቸው ይችላል።
2. አማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት ለሚማሩ ተማሪዎች የሚሆኑ በተላይ በጽሁፍ ክሂል ላይ ትኩረት ያደረጉ አጋዥ የማስተማሪያ መሳሪያዎች በበቂ ሁኔታ ማሟላትና ለዚሁ ፈጻሚ አካላት/መምህራን/ ወቅቱን የዋጁ የማስተማሪያ ዘዴዎች ትውውቅ ስልጠናዎች እየተዘጋጁ ቢሰጡ፤
3. አማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች ቋንቋውን በመማራቸው የሚያገኙት ጥቅም የሚያጓጓቸው እንዲሆን ቢደረግ፤ ይህም የተማሪዎቹን የመማር ፍላጎትና ተናሳሽነት ያሳድጋል።
4. ተተኳሪው ቋንቋ እንደሌሎቹ ትምህርት ዓይነቶች ሀገር-አቀፍ ፈተና የሚዘጋጅለትና የሚወዳደሩበት እንዲሆን ማስቻል፤ ይህ የሚሆን ከሆነ ተማሪዎች ትምህርቱን ለዓላማ ይማሩታል።
5. በአማርኛ ቋንቋ የሚያስተምሩ መምህራን የተማሪዎቻቸውን የጽሁፍ ክሂል ለማዳበር፤ ተከታታይነት ያለው ልምምድ እንዲያደርጉ ማድረግና ይህንንም የሚመዝኑበትን ዘዴዎች በማዘጋጀት ክትትልና ግብረ-መልስ በመስጠት ዕገዛ ቢያደርጉላቸው፤

በአጠቃላይ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በመንግስትና ባንዳንድ ማህበረሰብ ክፍሎች የተሰጠው አሉታዊ ግምት ተቀርፎ፤ አማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ቋንቋነት የሚማሩ ተማሪዎች በጽሁፍ ክሂል ላይ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ክሂሎች ዘርፍ ላይ የተሻለ ብቃት እንዲኖራቸው ለማስቻል ከላይ የተጠቀሱትንና መሰል የመፍትሄ ሀሳቦችን አካላትና መንግስት ትኩረት ሊሰጡበት ይገባል።

## ዋቢ መጽሃፍት


1. ለይላ እሸቱ (2003) በደብረ ብርሃንና በወሎ ዩኒቨርሲቲ በአማርኛ ትምህርት ክፍሎች የበሳል ድርሰትና የስነልሳን ትምህርቶችን (Courses) የሚያስተምሩ መምህራን የተከታታይ ምዘና አተገባበር ፍተሻ። (የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት)። (ያልታተመ)
2. ልዑልሰገድ አሰፋ (1997) "በወላይትኛ እና ሲዳምኛ ተናጋሪዎች የአማርኛ ድርሰት ውስጥ የታዩ ስህተቶች እና የስህተት ምንጭ ትንተና::" የአርትስ ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት።) አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።(ያልታተመ)
3. መሰረት ጣፋ (2003) "በሀረማያና በአዴሌ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸው ዋናዋና የስህተት አይነቶችና የስህተት ምንጮች ትንተና።" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ። ለድህረ ምረቃ መርሀ ግብር የቀረበ።
4. ማረው አለሙ (2005) በሳል ድርሰት ማስተማሪያ። አዲስ አበባ፣ አልፋ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።
5. ምህረት ሳዳሞ (1998) "በዋቻሞ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሀድይኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ
የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ትንተና"። አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ። (ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት)። (ያልታተመ)
6. በለጠ ያዕቆብ (2006 ዓ.ም.)። የበሳል ድርሰት ምዘና ውጤት አግባብነት፣ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ተተኳሪነት። (የሶስተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት)። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ። (ያልታተመ)
7. ባየ ይማም (2010) አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው። (አራተኛ እትም)፣ አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች።
8. ተመስገን ፈቀደ (2001) "የ11ኛ ክፍል መምህራን የጽህፈት ክሂል ማስተማሪያ ዘዴ እና የተማሪዎች ድርሰት የመፃፍ ብልሀት ተዛምዶ።" አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ። ለድህረ ምረቃ መርሀ ግብር የቀረበ።
9. ተገኝ አህመድ (2000) "አፋቸውን በከፍኛ ቋንቋ የፈቱ የቦንጋ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ሰልጣኝ መምህራን በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈፅሟቸው ስህተቶች ትንተና።" አዲስ አበባ ዩንቨርስቲ። (ያልታተመ)

10. ኃይሉ ዲንቃ እና አላምሮዉ ቁሚላቸዉ (2003፣21-26) "የጥናትና ምርምር ማኑዋል።" አዲስ አበባ፣ (አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቤቶች ውስጥ ለሚያስተምሩ መምህራን የተዘጋጀ)

11. ኃይላይ ተስፋዬ፤ ማረው ዓለሙ እና ሙሉጌታ ተካ (2009) "የአማራጭ ምዘናዎች የተማሪዎችን ድርሰት የመፃፍ ችሎታ የማሻሻል ሚና::" ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ:: (ያልታተመ)

12. ገነት ከበደ (2011) "በደቡብ ክልል ካፋ ዞን በተመረጡ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የ9ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈፅሟቸው ስህተቶች ትንተና።" (ለማስተርስ ዲግሪ ማሟያነት የተዘጋጀ ጥናት)። ጅማ ዩንቨርስቲ። (ያልታተመ)

13. አማረ ሰውነት (1996) "በትግርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስነ-ልሳናዊ ስህተቶች።" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ። (ያልታተመ)

14. አማረ ተሾመ (2010) "ተግባር ተኮር የቋንቋ ማስተማር ዘዴ የተማሪዎችን የመጻፍ ክሂል እና ተነሳሽነት ለማሻሻል ያለው ተጽዕኖ።" (ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት) ። አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ። (ያልታተመ)

15. አዲስዓለም ዘሪሁን (2012) "የኦሮምኛ ቋንቋ አፈ-ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ በሚጽፉት ድርሰት ላይ የሚስተዋሉ አሉታዊ የሰዋስው ተጽዕኖዎች እና የግድፈት ምንጮች ፍተሻ።" ባህርዳር ዩኒቨርስቲ። (ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት)። (ያልታተመ)

16. ኤፍሬም ጥሩነህ (2000) "የመፃፍ ክሂልን በማስተማር ሂደት የግልና የቢጤ እርማት ያላቸው ሚና።" ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፣ ድህረ ምረቃ ፕሮግራም (ያልታተመ የኤም.ኤ. ቴሰስ) ።

17. እስጢፋኖስ ተረፈ (2012) "በኮንሰኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ሰዋሰዋዊ ስህተቶች እና የስህተት ምንጮች ትንተና።" በደብረ ብርሃን ዩኒቨርሲቲ ማህበራዊ ሳይንስ እና ስነ-ሰብ ኮሌጅ :: (ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት)። (ያልታተመ)

18. ደብሬ ተሰማ (1990) "በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸው ዋና ዋና የስህተት ዓይነቶችና ምንጮች" አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ። (ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት)። (ያልታተመ)

19. ግርማ ሀይሉ (2000) "በጌድኦኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች እና የስህተት ምንጮች ትንተና።" የአርትስ ማስተርስ ዲግሪ ማሟያ ጥናት) ። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ። (ያልታተመ)

20. Asres Nigus (2005) “An Exploration of the Written Error Treatment Practices of the Intermediate Writing Skills Instructors of Bahir Dar University.”A.A.U: Unpublished MA thesis.

21. Brown H,Douglas (1994) Principle of language learning and teaching. London: prentice. Hall regents.

22. (2004) Language Assessment Principle Classroom Practices. San Francisco; Longman.

23. Charles Owu-Ewie et al (2017) Grammatical and Lexical Errors in Students’ English Composition Writing: University of Winneba, Ghana.

24. Chen, L.L (2006) “The effect of L1 and CA1 on grammar learning: An Error Analysis of Taiwanese beginning EFL learners’ English essays.” Asian EFL Journal, 9(2), 1-19.

25. Chokwe, J. M (2013) Factors Impacting Academic Writing Skills of English Second Language Students. Rome-Italy, University of South Africa v4p377.

26. Corder s.p (1967) The significance of learners error International Review of applied linguistics in language teaching. Retrived from https;//www degruyter.

27. Dubin, Fraid A and Olshtain, Elite (1986) Course design: Developing programes and materials for language Learning. U. S. A: Cambridge University Press.

28. Dulay,H. et al (1982) Language Two. Oxford: Oxford Univer it Press.

29. Fareed.M. et al (2016) ESL Learners’ Writting Skills; Problems, Factors and Suggestions. ለkarachi. University of Engineering Technology.

30. Ferris, D. R (2003) Response to Student Writing Implications for Second Language Students. Mahwah, Lawrance Elbaum Associates.
31. James, C (1998) Errors in language learning and use: Exploring Error Analysis. London: Longman.
32. Jang, Y.C (1995) Teaching English Verb tenses to Chinese EFL students.'' Journal of Kuen-Shan institute of Technology, 2, 119-123,
33. Lee, E (1997) "Evaluating Student Writing." College Compostion and Communication. 30:370-374.
34. Littlewood, W.T (1986) Foreign and Second Language Acquisition Research And its Implication for the Classroom. Cambridge: Cambridge University Press
35. Liu, C.K. Sung, C.S. and Chien, S. C (1998) "The process of generating notes when the EFL Students write English." Humanity and Socity Teaching Newsletter. 8(6). 132-150
36. Lott, D. (1983) "Analysing and Counteracting Interferenc Errors." ELT, Vol 37,No3, pp 256-261.
37. Mohammed.T (2008) An Analysis of the Common Grammatical Errors in the English Writing, Dubai. UAE British University
